# የአምስት ዓመት ስትራቴጂያዊ ዕቅድ

# 2014-2018

ነጻና ገለልተኛ ፍርድ ቤት፤ ለህግ የበላይነት !

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

## ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

# የአምስት ዓመት ስትራቴጂያዊ ዕቅድ

## 2014-2018

ነጻና ገለልተኛ ፍርድ ቤት፤ ለህግ የበላይነት !

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

**ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት**

በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በቀጠረ
አድቫንስ አሶሺየትስ እና አፕፍሮንት አማካሪ ድርጅት የተዘጋጀ

በስትራቴጂያዊ ዕቅድ ዝግጅት ሂደት አማካሪ ድርጅቱን እንዲከታተልና በሃሳብ እንዲደግፍ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝደንት የተቋቋሙ ዓብይና ቴክኒክ ኮሚቴ አባላት

ዓብይ ኮሚቴ

አቶ ተኽሊት ይመስል የፌ/ከ/ፍ/ቤት ም/ፕሬዝደንት (ሰብሳቢ)

አቶ ተስፋዮ ነዋይ የፌ/መጀ/ደ/ፍ/ቤት ም/ፕሬዝደንት (ም/ሰብሳቢ)

አቶ ቦጃ ታደሰ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ፕሬዝደንት ጽ/ቤት ኃላፊ

ደ/ር ጌታሁን አለማየሁ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ም/ፕሬዝደንት ጽ/ቤት ኃላፊ

አቶ ነሞ አዱኛ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ኮርት ማናጀር

ወ/ሮ ፍቅሬ አያሌው የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ስትራቴጂክ ስራ አመራር ዳይሬክተር

አቶ ሰለሞን እጅጉ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክተር

አቶ ደሳለኝ ከበደ በፌ/ጠ/ፍ/ቤት የተከላካይ ጠበቃ ጽ/ቤት ኃላፊ

ቴክኒክ ኮሚቴ

አቶ ደሳለኝ ከበደ - በፌ/ጠ/ፍ/ቤት የተከላካይ ጠበቃ ጽ/ቤት ኃላፊ (ሰብሳቢ)

አቶ አቤል ጌትነት -በፌ/ጠ/ፍ/ ቤት የዕቅድ ዝግጅት ባለሙያ

ወ/ሮ ረቢአት ኢብራሂም - በፌ/ጠ/ፍ/ ቤት የዕቅድ ዝግጅት ባለሙያ

አቶ ደረጀ ተስፋዬ -በፌ/ጠ/ፍ/ ቤት የዕቅድ ዝግጅት ባለሙያ

አቶ እሸቱ መሐመድ - የፌ/ከ/ፍ/ቤት የዕቅድ ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ ዳይሬክተር

አቶ ኽሊል ነጋሽ - የፌ/መጀ/ደ/ፍ/ቤት የዕቅድ ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ ዳይሬክተር

አርታኢ

ወ/ሮ ፍቅሬ አያሌው

አቶ ደሳለኝ ከበደ

አቶ ሰለሞን እጅጉ

አቶ አቤል ጌትነት

© 2014 ዓ.ም.፤ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

# ማውጫ


መልዕክት iii

ጭምቅ ሐሳብ v

መግቢያ 1

I. የፌዴራል ፍርድ ቤቶችስትራቴጂያዊ ዕቅድ አስፈላጊነትና ዓላማዎች 1

II.የፌደራል ፍርድ ቤቶች ስትራቴጂያዊ ዕቅድ  አፈጻጸምና የተገኙ ልምዶች 2

III.የሶስተኛው ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ዝግጅት ሂደት 5

ክፍል አንድ 7

1. የሁኔታዎች ትንተና 7

1.1. የፌደራል ፍርድ ቤቶች አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር 7

1.2. የፌደራል ፍርድ ቤቶች አሁን ያሉበት ሁኔታ (ጥንካሬና ድክመት) ዳሰሳና ትንተና 12

1.2.1. የዳኝነት ነጻነት፣ ገለልተኝነት፣ ግልጽነት እና ተጠያቂነት 12

1.2.2. የዳኝነት አገልግሎት ቅልጥፍና እና ጥራት 20

1.2.3. የዳኝነት አገልግሎት ተደራሽነት 31

1.2.4. የህዝብ አመኔታ እና ተቀባይነት 36

1.2.5. የፌደራል ፍርድ ቤቶች የአቅም ሁኔታ 38

1.3. የፖለቲካ፣ ኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ፣ ቴክኖሎጂያዊ፣ አካባቢያዊና ህጋዊ ሁኔታዎች ትንተና 44

1.4. አስቻይና ፈታኝ ሁኔታዎች 52

1.5. የተገልጋዮችና የባለድርሻ አካላት ፍላጎት ትንተና 54

ክፍል ሁለት 63

2. ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች 63

2.1. ራዕይ፣ ተልዕኮ እና እሴቶች 63

2.2. ቁልፍ የውጤት መስኮች፣ ግቦች፣ ስትራቴጂዎች ፣ ውጤቶች እና ውጤት አመልካቾች 64

2.2.1. ቁልፍ የውጤት መስኮች 64

2.2.2. የቁልፍ የውጤት መስክ ማብራሪያዎች 65

ክፍል ሦስት 74

3. የትግበራ መርሐ-ግብር እና ስልቶች 74

3.1. የስትራቴጂያዊ ዕቅድ አተገባበርን የመምራትና የማስተባበር ኃላፊነቶች 74

3.2. ስትራቴጂያዊ ዕቅዱን ወደ እያንዳንዱ ፍርድ ቤትና የስራ ክፍል ማውረድ (cascading) 74

3.3. የፍርድ ቤቱን ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል ስምሪት ማሻሻ 75

3.4. የሀብት ማሰባሰብና ውጤታማ አጠቃቀም 75

3.5. ስትራቴጂያዊ ዕቅዱን ማስተዋወቅና ግንዛቤ መፍጠር 76

ክፍል አራት 77

4. የክትትልና ግምገማ ዕቅድ 77

4.1. የስትራቴጂያዊ ዕቅድ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ዕቅድ ዓላማዎች 77

4.2. የስትራቴጂያዊ ዕቅድ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ መዋቅርና ኃላፊነት 78

4.3. የስትራቴጂያዊ ዕቅድ አፈጻጸም ክትትል ግምገማና ሪፖርት አደራረግ 78

አባሪ 1፡- የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የ2014- 2018 ስትቴጂያዊ ዕቅድ የትግበራ መርሃግብር ሰንጠረዥ 81

አባሪ 2፡- የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የ2014-2018 ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ክትትልና ግምገማ ዕቅድ 127

# መልዕክት

በፌዴራል መንግስት የስልጣን መዋቅር ህግን በመተርጎም ነጻ እና ገለልተኛ ዳኝነት እንዲሰጡ በህገ መንግስት የተቋቋሙት የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ባለፉት ሶስት ዓመታት የዳኝነት አገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል የመሰረት ድንጋይ የሚያስቀምጡ ዓብይ የማሻሻያ ስራዎችን ሲያከናውኑ ቆይተዋል፡፡ በዚህም ቀደም ሲል ስራ ላይ የነበሩትን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች እና የፌዴራል ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ አዋጅን በማሻሻል የዳኝነት ዘርፉ ከማንኛውም ውስጣዊም ሆነ ውጫዊ አካል ተጽዕኖ ነጻነቱን መጠበቅ የሚያስችል የዳኝነት አስተዳደር እንዲዋቀር ተደርጓል፡፡ የአገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል የሚያግዙም የፍርድ ቤቶች አደረጃጀቶች፣ የአሰራር ስርዓቶች፣ ተጨማሪ ስልጣንና ተግባራትን የሚሰጡ ድንጋጌዎች የተካተቱበት የአዋጅ ማሻሻያዎች መተግበር ጀምረዋል፡፡

የፌደራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣናቸውን በስራ ላይ ለማዋል በዕቅድ መመራት ከጀመሩበት ጊዜ አንስቶ ባለፉት አስርት ዓመታት ሁለት የአምስት ዓመት ስትራቴጂያዊ ዕቅዶችን አዘጋጅተው ተግብረዋል፤ የዕቅዶቹ አተገባበር ፍርድ ቤቶች ለበርካታ ዓመታት የተከማቹባቸውን ተቋማዊ፤ አስተዳደራዊ እና የአሰራር ችግሮች መጠን በመጠን መቀነስ እና ማሻሻል ያስቻሉ ነበሩ ማለት የሚያስችል ውጤት አምጥተዋል፡፡ በአተገባበር ሂደቱ የተገኙ መልካም ውጤቶችን በማስቀጠል፤ መሻሻል እና መለወጥ ያለባቸውን የአደረጃጀት እና የአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ደግሞ ቀጣይ የማሻሻያ ተግባራትን በጥናትና ዕቅድ ላይ ተመስርቶ የዳኝነት ስራን ማከናወን አስፈላጊነት ተምኖበታል፡፡ በዚህም መሰረት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ከ2014-2018 ዓ.ም የሚተገብሯቸውን ግቦች፣ ስትራቴጂጂዎችና ዋና ተግባራት የሚያመላክት ሶስተኛውን የአምስት ዓመት ስትራቴጂያዊ ዕቅድ በአማካሪ ድርጅት በመታገዝ አዘጋጅቷል፡፡

ይህ ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ቀደም ብለው የተተገበሩትን ስትራቴጂያዊ ዕቅዶች እና በፍርድ ቤት ውስጥ የተጀመሩትን የለውጥ ስራዎች ለመምራት በ2011 ዓ.ም መጨረሻ የተዘጋጀውን የሶስት ዓመት ፕሮጀክቶች ዕቅድ ግምት ውስጥ አስገብቷል፡፡ ዕቅዱ የተዘጋጀው የሕዝብን ነፃና ገለልተኛ፤ ቀልጣፋና ጥራት ያለው የዳኝነት አገልግሎት የማግኘት መብት ለማረጋገጥ ሲሆን በእነዚህ መሰረታዊ መርሆች ላይ የተመሰረት ዕቅድ አዘጋጅቶ መተግበር የሕዝብ አመኔታ ለማግኘት ያስችላል ተብሎ ይታመናል፡፡ የፍርድ ቤቶችን ሃብት በአግባቡ ተጠቅሞ ለታለመለት ዓላማ እንዲውል ለማድረግም ያግዛል፡፡ የስትራቴጂክ ዕቅዱ ዋና ዓላማ የፍርድ ቤቶችን ስትራቴጂያዊ አቅጣጫዎች አመላክቶና ተልዕኮን መወጣት የሚያስችሉ ተግባራትን አከናውኖ መልካም እሴቶችን በመከተል በስትራቴጂያዊ ዘመኑ የሚደረስበትን “የሕዝብ አመኔታ ያተረፈ የዳኝነት ተቋም ሆኖ ማየት” ራዕይ ማሳካት ነው፡፡

የስትራቴጂያዊ ዕቅዱ ፍርድ ቤቶች በኢትዮጵያ የሕግ ስርዓት ውስጥ ሕገ መንግስታዊ ሚናቸውን በአግባቡ እንዲወጡ፤ የዳኝነት ነፃነትን ያስከበረ፣ ቀልጣፋና ጥራት ያለው የዳኝነት አገልግሎት እንዲሰጡ ማስቻል ዓላማ ያደረገ ነው። ከዚህ ጎን ለጎን ፍርድ ቤቶች ተልዕኳቸውን ከተሻሻሉ ሕጎች እና ከሀገሪቱ የአስር ዓመት የልማት ዕቅድ ጋር እንዲያጣጥሙ፤ የበላይ አመራር አካላት ስትራቴጂያዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ አተኩረው እንዲሰሩ፤ ከባለድርሻ አካላት ጋር የሚኖረውን መስተጋብር በዕቅድና በእውቀት በመምራት፣ ሕግና መርህን መሰረት ያደረገ ቅንጅታዊ አሰራር እንዲያጎለብቱ ዓላማ ስቀምጧል። በተጨማሪም ፍርድ ቤቶች ሃብት ከፍተኛ እሴት በሚጨምሩና ቅድሚያ በሚሰጧቸው ጉዳዮች ላይ እንዲያወጡ፤ የዳኝነት ነፃነትና ተጠያቂነት መርሆች ሚዛኑን በጠበቀ አግባብ እንዲተገበሩ፤ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያላቸውን መርሆዎችና አሰራሮች በመጠቀም ወደ ልህቀት ደረጃ እንዲሻገሩ ማስቻልን ዓላማው ያደረገ ነው።

በስትራቴጂያዊ ዕቅዱ የተቀመጡ ዓላማዎችን ለማሳካት በሚደረግ ጥረት የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ከፍተኛ አመራሮች፣ ዳኞች እና የአስተዳደር ሰራተኞች የአንበሳውን ድርሻ የሚወስዱ ሲሆን መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ የፍትህ ተቋማት ድጋፍም አጠያያቂ አይሆንም። ከበጀት እና ከውስን ሃብት የተነሳም የልማትና አጋር ድርጅቶች ፍርድ ቤቶች በሚያቀርቧቸው ተቋማዊ እና የሰው ኃይል ዓቅም ግንባታ ስራዎች ላይ አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ሁኔታዎች የሚመቻች ይሆናል። የስትራቴጂያዊ ዕቅድ ዘመኑ ጠንካራ እና ህዝብ የሚተማመንበት የዳኝነት ተቋም ለመገንባት የሚያስችሉ የማዕዘን ዓምድ መትከል የሚያስችሉ ስትራቴጂያዊ ተግባራት የምናከናውንበት እንደሚሆን እምነቴ እና ተስፋዬ ከፍ ያለ ነው፡ ፡ ነጻና ገለልተኛ፤ ቀልጣፋና ጥራት ያለው የዳኝነት አካል መኖር በሃገራችን ማህበረሰቡ የሚኖረው ማህበራዊ፤ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ መስተጋብር ጤናማና ሰላማዊ እንዲሆን ካለው ትሩፋት ጎን ለጎን ቀጣነት ያለው የልማትና ምጣኔ ሃብታዊ እድገት እንዲመጣ ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር በመሆኑ ለዚህ ዕቅድ መተግበር ድርሻ ያላቸው አካላት በሙሉ የሚጠበቅባቸውን አወንታዊ ሚና እንዲጫወቱ ጥሪ አቀርባለሁ። አመሰግናለሁ ! !

መዓዛ አሸናፊ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝደንት

# ጭምቅ ሐሳብ

## 1. የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስትራቴጂያዊ ዕቅድ አስፈላጊነትና ዓላማ

የፌደራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን ከሕገ መንግስቱና በተዋረድ ከወጡ ሌሎች ሕጎች የሚመነጭ ሲሆን ነጻ፣ ግልጽነት እና ተጠያቂነት ያለው ዳኝነት እንዲሰጡ የሕገ መንግስቱ ድንጋጌዎች ያስገድዷቸዋል፡፡ የፌደራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣናቸውን በስራ ላይ ለማዋል በዕቅድ መመራት ከጀመሩበት ጊዜ አንስቶ ሁለት ስትራቴጂያዊ ዕቅዶችን አዘጋጅተው የተገበሩ ሲሆን ሶስተኛውንና ከ2014-2018 የሚተገብሩ ግቦችን፣ ስትራቴጂዎችንና ዋና ዋና ተግባራትን የሚያመላክት የአምስት ዓመት ስትራቴጂያዊ ዕቅድ አዘጋጅተዋል። የዕቅዱ ማዕከላዊ ትኩረት የሕዝብን ነፃ፣ ቀልጣፋና ጥራት ያለው የዳኝነት አገልግሎት የማግኘት መብትን ማስከበር ነው። በእነዚህ መሰረታዊ መርሆዎች ላይ ተመስርቶ የተዘጋጀ ዕቅድን መተግበር የሕዝብ አመኔታ ለማግኘት ከማስቻሉ ጎን ለጎን የፍርድ ቤቶችን ሃብት በአግባቡ ተጠቅሞ ለታለመለት ዓላማ እንዲውል ለማድረግም ያግዛል።

የስትራቴጂያዊ ዕቅዱ ዋና ዓላማ የፍርድ ቤቶችን ስትራቴጂያዊ አቅጣጫዎች አመላክቶና ተልዕኮን መወጣት የሚያስችሉ ተግባራትን አከናውኖ መልካም እሴቶችን በመከተል በስትራቴጂክ ዘመኑ የሚደረስበትን ራዕይ ማሳካት ሲሆን ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ነፃነትን ያስከበረ፣ ቀልጣፋና ጥራት ያለው የዳኝነት አገልግሎት እንዲሰጡ በማድረግ የተገልጋዮችን ዕርካታ እና የህብረተሰቡን አመኔታ ማሳደግ ነው። የዳኝነት ነፃነትና ተጠያቂነት መርሆች ሚዛን በጠበቀ አግባብ እንዲተገበሩ፤ ከባለድርሻ አካላት ጋር የሚኖራቸውን መስተጋብር በዕቅድና በእውቀት እንዲመሩ እና ሕግና መርህን መሰረት ያደረገ ቅንጅታዊ አሰራር እንዲያጎለብቱ ማድረግና ቁልፍ የውጤት መስኮችን ማስቀመጥ እንደ ዝርዝር ዓላማዎች የሚጠቀሱ ናቸው።

## 2. በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ዕቅድ አፈጻጸምና የተገኙ ውጤቶች

ከ2008-2012 እንዲተገበር ተዘጋጅቶ የነበረው ስትራቴጂያዊ ዕቅድ እስከ 2010 ዓ.ም ሲተገበር ከቆየ በኋላ በ2011 ዓ.ም የተደረገውን የፍርድ ቤት አመራር ለውጥ ተከትሎ በመሸጋገሪያ ዕቅዶች እንዲተካ ተደርጓል። በ2012 እና 2013 በጀት ዓመት ተዘጋጅተው ሲተገበሩ በቆዩ በእነዚህ ዓመታዊ ዕቅዶች የዳኝነት ነጻነት፣ ገለልተኝነትና ተጠያቂነትን ማጠናከር፤ የዳኝነት አገልግሎት ጥራትን ማሳደግ፤ የዳኝነት አገልግሎት ቅልጥፍና ማሻሻል እና አስተዳደራዊ ድጋፎችን ማጠናከር የሚሉና በዳኝነት አገልግሎት ላይ ያተኮሩ ግቦች ከስትራቴጂክ ዕቅዱ ተመርጠው ለመለካት አመች የሆኑ መስፈርቶችን በመያዝ ሲተገበሩ ቆይተዋል። ለግቦቹ ስኬታማነት የሚያግዙ ከ36 በላይ ፕሮጀክቶችን ይዞ ከ2011-2014 ዓ.ም እንዲተገበር የተዘጋጀው የሶስት ዓመት ፕሮጀክት ዕቅድም በመተግበር ላይ ይገኛል።

በሁለተኛው ስትራቴጂያዊ ዘመን (2008-2012) ዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ የችሎት አዳራሾችና የቢሮ

ዕጥረቶችን ተቋቁሞ እና በ2011 በጀት ዓመት የተጀመሩ ሁሉን አቀፍ የፍርድ ቤቶች ማሻሻያ ሥራዎችን አጠናክሮ በመቀጠል ከፍተኛ ለውጦች የታዩባቸው ውጤቶች መገኘታቸውን አመላክቷል። ከእነዚህ ውጤቶች መካከል ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትና ለጋሽ ድርጅቶች ጋር ተቀራርቦ በመሥራት ለዳኝነት አገልግሎት እንቅፋት የሆኑና የተሸሻለ የዳኝነት አገልግሎት ለመስጠት የሚያግዙ የሕግ ማዕቀፍ ማሻሻያ ሥራዎች መጀመራቸውን ለምሳሌ በሳል የሕግ ምሁራን በሚሳተፉበት የፍርድ ቤቶች አማካሪ ጉባዔ የተሻሻሉ የፌዴራል ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ እና የፌዴራል ፍርድ ቤት አዋጆች መዘጋጀታቸውን፣ የዳኞች ሥነ ምግባርና ዲስፕሊን ደንብ መሻሻሉን፣ የዳኞች ሥራ አፈጻጸም ምዘና መመሪያ መዘጋጀቱን፣ የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር መመሪያ መውጣቱን....አብነት ማድረግ ይቻላል፡ ፡ የፍርድ ቤቶችን ሕገመንግስታዊ ነጻነት ለማስከበር የበጀት ፍላጎትን ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በቀጥታ አቅርቦ አንጻራዊ መሻሻል የታየበት በጀት ማስፈቀድና ውጤታማ አጠቃቀምን ማጎልበት መቻሉም ለእነዚህ ውጤቶች ማሳያ ለማድረግ ይቻላል። በሌላ በኩል ምቹ የአገልግሎት መስጫ ከባቢን ከመፍጠርና በግልት ችሎት መስጠት ሚቻልባቸውን ሁኔታዎች ለማመቻቸት በኪራይ ህንጻ ምድብ ችሎቶች እና ጽ/ቤቶች መደራጀታቸውን በመልካም አፈጻጸም ግምገማው አንስቷቸዋል።

## 3. ሶስተኛው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስትራቴጂያዊ ዕቅድ (2014-2018)ዝግጅት ሂደት

ሶስተኛው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስትራቴጂያዊ ዕቅድ (2014-2018) በአድቫንስድ አሶሺየትስ እና አፕፍሮንት አማካሪ ድርጅት የተዘጋጀ ነው። በዕቅዱ ዝግጅት ሂደት ከሶስቱም ፍርድ ቤቶች የተውጣጡ የበላይ አመራሮች፣ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች የተሳተፉባቸው ዓብይ እና ቴክኒክ ኮሚቴዎች ተደራጅተው በአማካሪዎች የሚቀርቡ ረቂቆችን ተከታትለው በመገምገም፣ በማረምና ማሻሻያ ሀሳቦችን በመስጠት ከፍተኛ ሚና ሲጫወቱ ቆይተዋል። ለስትራቴጂያዊ ዕቅድ ዝግጅቱ መሰረት የሆኑ ህጎች፣ አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና የፍርድ ቤት ሪፖርቶች ላይ ጥናቶችና ትንተናዎች የተከናወኑ ሲሆን በሶስቱም ፍርድ ቤቶች ካሉ አመራሮች፣ ከተመረጡ ዳኞችና የአስተዳደር ሰራተኞች በቃለ መጠይቆች እና በአትኩሮት የቡድን ውይይቶች በማድረግ የፍርድ ቤቶችን ጥንካሬና ድክመቶች የሚያሳዩ መረጃዎች ተሰብስበዋል። ለቀጣዮቹ ስትራቴጂክ ዓመታት ለፍርድ ቤቶች መልካም አጋጣሚ እና ስጋት የሚሆኑ ጉዳዮችን መለየት ያስቻሉ ውጫዊ ዳሰሳዎችና ትንተናዎች ተካሂደዋል። የባድርሻ አካላት የአገልግሎት ፍላጎት ትንተናም ተሰርቷል። በእነዚህ መረጃዎችና ትንተናዎች ግኝቶች ላይ ተመስርቶ ለተቋሙ ዕቅድ መሳካት አስቻይና ፈተኝ የሆኑ ሁኔታዎችን በመለየት ረቂቅ ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ተዘጋጅቷል። በረቂቁ ላይ በየደረጃው የሚገኙ የፍርድ ቤት አመራሮች፤ ዳኞችና የአሰተዳደር ሰራተኞች እንዲወያዩበት በማድረግ የተገኙ ተጨማሪ ግብዓቶችም ለረቂቁ ማዳበሪያ እንዲሆኑ ተደርጓል።

## 4. ራዕይ፣ ተልዕኮ እና እሴቶች

በዚህ ስትራቴጂክ ዕቅድ የፌደራል ፍርድ ቤቶች በቀጣዮቹ አምስት ዓመታት ለማከናወን ያቀዱትን ስትራቴጂካዊ ዕቅድ ለማሳካት የጋራ ስምምነት የተደረገባቸው የተቋም ራዕይ፣ ተልዕኮና ዕሴቶች ከመዘጋጀታቸውም ሌላ ሊተኮሩባቸው የሚገቡ ስትራቴጂያዊ ጉዳዮችን መሰረት ያደረጉ ቁልፍ የውጤት መስኮች ተቀርጸዋል። የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ራዕይ "የህዝብ አመኔታ ያተረፈ የዳኝት ተቋም ሆኖ

ማየት" ሲሆን ተልዕኳቸው ደግሞ "ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ተደራሽ የዳኝነት አገልግሎት በመስጠት የህግ የበላይነትን ማረጋገጥ" እንዲሆን ተደርጓል። ይህን ተልዕኮ ለማሳካት ነጻነትና ተጠያቂነት፣ ገለልተኝነት፣ ግልጽነት፣ ሙያዊ ብቃት፣ የቴክኖሎጂ ተጠቃሚነት፣ ሕዝብ ያማከለ፣ እና ሀቀኝነት የሚሉ እሴቶች የተቀረጹ ሲሆን በልዩ ትኩረት ይፈጸማሉ ።

## 5 . ቁልፍ የትኩረት መስኮች እና ስትራቴጂዎች

ስትራቴጂያዊ ዕቅዱ የዳኝነት ነፃነት፣ ገለልተኛነት፣ ግልጽነት እና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ፤ የዳኝነት ቅልጥፍና እና ጥራትን ማሳደግ፤ የዳኝነት ተደራሽነት ማጠናከር፤ ስትራቴጂያዊ አጋርነት እና ውጤታማ ኮሚዩኒኬሽን ማጎልበት፤ ተቋማዊ ለውጥና ብቃት ማሳደግ እና የላቀ የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ማጎልበት የሚሉት ስድስት ቁልፍ የውጤት መስኮችን የያዘ ሲሆን ለውጤት መስኮች መሳካት የሚያግዙ 13 ግቦች እና 59 ስትራቴጂዎች ተቀርጸው የዕቅዱ አካል እንዲሆኑ ተደርገዋል። ከግቦቹ የሚጠበቁ ውጤቶችና መለኪያዎቻቸውም ተቀምጠውላቸዋል።

የዳኝነት ነጻነትና ገለልተኝነትን ለማረጋገጥ እንቅፋት የሆኑ ህጎችና አሰራሮችን ለማሻሻል የግንዛቤና የአተገባበር ችግሮች መፍትሄ እንዲያገኙ ለማድረግ የዳኘነት ዘርፉን በተመለከተ ረቂቅ ህጎችን ለህግ አውጪው ያቀርባል።  በሌሎች ህጎች ላይ ከመጽደቃቸው በፊት ፍርድ ቤቶች አስተያየታቸውን የሚሰጡበት አሰራርም ይዘረጋል።  ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት እና ለአስፈጻሚው ከፍተኛ ባለስልጣናት በፍርድ ቤቶች ነጻነትና ገለልተኝት መርህ ላይ ግንዛቤ እንዲጨብጡ ተደጋጋሚ ስልጠናዎች ይሰጣሉ። ፍርድ ቤቶች የበጀትና የሰው ሃይል አስተዳደር ነጻነትን ማጎናጸፍ የሚስችሉ ደንቦችና መመሪያዎች ይወጣሉ።  ለተግባራዊነታቸውም ተገቢው አደረጃጀት ይፈጠራል፤ የአሰራር ስርዓትም ይዘረጋል።

ግልጽ አሰራርና የስነምግባር መርሆዎችን መሠረት ያደረገ የተጠያቂነት ስርዓት መዘርጋት በስትራቴጂያዊ ዕቅድ ዘመኑ ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራ ይሆናል። በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የሚተገበሩ ግልጽ የጉዳዮች አደላደል እና ችሎት አደረጃጀት ስታንዳርዶች ተዘጋጅተው ተግባራዊ ይደረጋሉ። የተመረጡ የፍርድ ቤት ውሳኔዎች እና ሕብረተሰቡ ሊያውቃቸው የሚገቡ መረጃዎች ለሕዝብ ተደራሽ የሚደረጉበትን ስርዓት፣ የኮሚዩኒኬሽን አቅምን አጎልብቶ ተቋማዊ የገጽታ ግንባታ የሚጠበቅበትን ሚና እንዲጫዎት የማድረግ፣ የዳኝነት አገልግሎቶችን በግልጽ ችሎት ለመስጠት የሚያስችሉ የችሎትና ቢሮ አቅርቦቶችን የማሟላት፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ የቅሬታ/ጥቆማ እና አቤቱታ አቀራረብ ስርዓት ዘርግቶ የተጠያቂነት መርህን በአግባቡ መተግበር፣ በአጠቃላይ የዳኝነት አገልግሎቶችን ለማሻሻል የተጀመሩ የሪፎርም ሥራዎች አጠናክሮ በመቀጠል ከዕቅዱ የሚጠበቁ ውጤቶች እንዲገኙ ይደረጋል።  በሁሉም ምድብ ችሎቶች በኢኮቴ የታገዘ የተገልጋይ አስተያየት መቀበያ ስርዓት የሚዘረጋ ሲሆን የዳኞች የአፈጻጸም ምዘና ስርዓት እና የተገልጋይ እርካታ ደረጃ መለያ ዳሰሳ ጥናት ይካሄዳል። የድህረ ፍርድና ውሳኔ ምርመራን በቋሚነት በመስራት ለተጠያቂነት እና ለፍርድ ጥራት ማስጠበቂያ ስርዓት ግብአት  የሚደደረግ ይሆናል።

የዳኞችን ትጋትና ውጤታማነት የሚጨምሩ ስርዓቶችን በመዘርጋት የዳኝነት ቅልጥፍናን ለማስሳደግ

በፍትሐ ብሔር ጉዮች ፍሰት አስተዳደር መመሪያ በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ዕልባት የሚያገኙ መዛግብትን አሁን ካለበት 87% ወደ 95% ለማድረስ ዒላማ ተቀምጧል። የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በ2013 በጀት ዓመት ከቀረቡላቸው መዛግብት መካከል እልባት የሰጡባቸውን 171,276 መዛግብት በስትራቴጂክ ዘመኑ መጨረሻ ወደ 264,276 ለማድረስ ታቅዷል። በዚህም የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን 101.7% መዛብግትን የማጥራት ዓቅም አስጠብቆ ከ100% እንዳይወርዱ በማድረግ የመዛግብት ክምችት ምጣኔን ከ0.12 ወደ 0 ለመቀነስና የመዛግብት መጨናነቅን ለማስቀረት ታቅዷል።

የውሳኔ ጥራትን ለማሻሻልም በስትራቴጂያዊ ዘመኑ ወጥ የህግ አተረጓጎም ስርዓት መመሪያ የሚዘጋጅ ሲሆን የውሳኔ ምክንያታዊነትን ለማሳደግ በናሙና ፍርዶች ይዘትና ቅርጽ እንዲሁም የውሳኔ አጻጻፍ ላይ ጥናት ይካሄዳል፤ ትምህርታዊ ጉባዔዎችም ይካሄዳሉ። ከዚህ ጎን ለጎን የዳኝነት፣ የሬጂስትራር እና የፍርድ አፈጻጸም አገልግሎት አሰጣጥ ጥራት ስታንዳርዶች ይወጣሉ። ለአተገባበሩም የዳኞችና የአስተዳደር ሰራቶኞን ግንዛቤ ከማሳደግ በተጨማሪም ደጋፊ የሆኑ የአሰራርና የአደረጃጀት ለውጦች ይደረጋሉ።

ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም የዳኝነት አገልግሎትና መረጃዎች ተደራሽነትን ለማስፋት እንዲሁም የዲጂታል መረጃ በተደራጀ ሁኔታ ለማከማቸት የሚያግዙ የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት የመዘርጋት ተግባራት ይከናወናሉ። የአገልግሎት አሰጣጥን የሚያዘምኑ እና ቅልጥፍናን ለማሳደግ የሚረዱ መተግበሪያዎች በማልማት ጥቅም ላይ ይወላሉ። የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ምድብ ችሎቶች እርስ በእርስ የሚስተሳሰርና ግንኙነታቸውን የሚያሳልጥ ኔትወርክ የሚዘረጋ ይሆናል።

በስትራቴጂክ ዕቅድ ዘመኑ ትኩረት የተሰጠው ሌላው ጉዳይ ስትራቴጂያዊ አጋርነትና ውጤታማ ኮሚዩኒኬሽን ሲሆን አገራዊና ዓለም አቀፋዊ አጋርነትና ድጋፍን የሚያጎለብቱ ስራዎች በስፋት ይሰራሉ። የየፍርድ ቤቶችን ዓለም አቀፍ ግንኙነትና ትብብር ለማጠናከር የሚያስችል ስርዓት ተዘርግቶ ይተገበራል፡ ፡ ፍርድ ቤቶች ከተመረጡ የትምህርት፣ ሥልጠና እና ምርምር ተቋማት ጋር የሚኖራቸውን ትስስርና ትብብር፤ ከፌዴራልና ከክልል የፍትህ አካላት ጋር በመርህ ላይ የተመሠረተ አጋርነትና ግንኙነትን፤ እና ከህግ ባለሙያ/ ጠበቆች ማህበሮች ጋር የሚኖር አጋርነትን ለማሳደግ የሚያስችሉ ሥርዓቶች በመዘርታት ተግባራዊ ይደረጋሉ። የኮሚዩኒኬሽን ክፍሎችን አደረጃጀትና አሰራር በማጠናከርም ህዝቡን ማዕከል ያደረጉ ቋሚ የግንዛቤ ማስጨበጫ እና መረጃ መስጫ መርሐ-ግብሮች ይዘጋጃሉ።

## 6. የትግበራ መርሃግብርና ስልቶች

የስትራቴጂያዊ ዕቅዱን አተገባበር ውጤታማ ለማድረግ ተያያዥነት ያላቸው የትግብራ ስልቶች ጥቅም ላይ ይውላሉ። በትግበራው ሂደት በየደረጃው የሚገኑ አመራሮች ኃላፊነቶች ተለይተው የተገለጹ ሲሆን በሶስቱም የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሚኖረውን የስትራቴጂያዊ እቅዱ አተገባበር የመምራትና የማስተባበር ሃላፊነት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝደንት ተሰጥቷል። በከፍተኛና በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች ደረጃ የሚኖረውን የስትራቴጂያዊ ዕቅድ አተገባበር በዋናነት የየፍርድ ቤቶቹ ፕሬዝዳንቶች ይመራሉ፤ ይከታተላሉ። የየዕለቱን አተገባበር የማስተባበር፣ የመምራት፣ የመከታተልና የመገምገም

ስራ በስትራቴጂክ ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት በኩል የሚከናወን ሲሆን የተሻሻሉ የአሰራር ሰርዓቶችን መዘርጋት እና የስራ ክፍሎቹን አፈጻጸም ማጠናከር የበላይ አመራሩ ቁልፍ ተግባር ይሆናል፡፡

የስትራቴጂያዊ ዕቅዱን ወደ እያንዳንዱ ፍርድ ቤትና የስራ ክፍል ማውረድ ሌላው የስትራቴጂያዊ ዕቅዱ ማስፈጸሚያ ስልት ሲሆን ከስትራቴጂክ ዕቅዱ የወረደ የተቋም ዕቅድ እንዲዘጋጅና በሶስቱም ደረጃዎች በሚገኙ ፍርድ ቤቶች እንዲወርድ ይደረጋል፡፡ በሦስቱም ፍርድ ቤቶች የሚገኙ ሁሉም ችሎቶች፣ ዳኞች፣ ዳይሬክቶሬቶች፣ ቡድኖችና ግለሰብ ፈጻሚዎች በየደረጃው ያላቸውን ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችል እና ከተቋም ዕቅድ ጋር የተሳሰረ ዓመታዊ ዕቅድ ያዘጋጃሉ፡፡

## 7. አፈጻጸም ክትትል፣ ግምገማና ሪፖርት

የስትራቴጂያዊ ዕቅዱን የተሟላና ውጤታማ አተገባበር ለማረጋገጥ የክትትልና ግምገማ መርኃግብር የተዘጋጀ ሲሆን ከተሻሻሉ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጆችና የለውጥ ሂደቶች ጋር የተጣጣመ ተቋማዊ አደረጃጀት ተዘጋጅቶ የሰው ሃይል ስምሪት ማሻሻያ ይደረጋል፡፡ ስትራቴጂውን ለማስፈጸም የሚያስፈልገውን ሃብት የማሰባሰብና ውጤታማ አጠቃቀምን ማጎልበትም የዕቅዱ አካል እንዲሆን ተደርጓል፡፡ በዚህም በዋናነት ከመንግስት በቂ በጀት የሚገኝበትና መንግስታዊ ካልሆኑ አጋር ድርጅቶች የገንዘብ፣ የአገልግሎና የሙያ ድጋፍ የሚገኝበትን ስልት በመንደፍ ለመተግበር ጥረት ይደረጋል፡፡ በመጨረሻም የውስጥና የውጭ ባለድርሻ አካላት ስለ ፍርድ ቤቱ ስትራቴጂያዊ ዕቅድ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው በስትራቴጂያዊ ዕቅዱና በማስፈጸሚያ ስልቶቹ ላይ ስልጠናዎች ይዘጋጃሉ፡፡ የተለያዩ የማሰራጫ መንገዶችን በመጠቀምም ስትቴጂያዊ ዕቅዱ ለባለድርሻ አካላት ተደራሽ ይሆናል፡፡

የስትራቴጂያዊ ዕቅድ ሥራ አመራር ሥርዓት ምሰሶ የሆነው የስትራቴጂያዊ ዕቅድ ክትትልና ግምገማ ሥርዓት በመዘርጋት መንፈቅ ዓመት፣ በየበጀት ዓመቱ፣ በዕቅዱ ትግበራ ዘመን (2014-2018 ዓ.ም) አጋማሽ፣ እና በስትራቴጂክ ዘመኑ መጨረሻ (በአምስት ዓመት) ይካሄዳል፡፡ የዕቅድ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ዓላማ ተጨባጭ የአፈጻጸም መረጃን መሰረት ያደረገ ውሳኔ እንዲሰጥ ማድረግ፣ ቀጣይት ያለው የአፈጻጸም መሻሻልን ማረጋገጥ እና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የተጠያቂነት ሥርዓትን ማጠናከር ነው፡፡ የክትትል፣ ግምገማ እና ሪፖርት ስራ በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች በሚገኙ አመራሮችና ይህንኑ ተግባር ለማከናወን በተደራጁ የስራ ክፍሎች የሚከናወን ይሆናል፡፡ በየትኛውም የዕቅድ አፈጻጸም ዘመን የሚካሄድ ግምገማ የተከናወኑ ዋና ተግባራትን አግባብነት፣ ውጤታማነት፣ ቅልጥፍና፣ ጥራት.... ማረጋገጥ በሚያስች ለመልኩ የሚካሄድ ሲሆን የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን ሃገራዊ ድርሻ ወይም በፍትህ ዘርፉ የሚኖራቸውን አስተዋጽዖ እና ቀጣይነትን ያመላክታል፡፡ ተጨባጭ የአፈጻጸም መረጃዎችን መሠረት ያደረጉ የማስተካከያ እርምጃዎችም ይወሰዳል፡፡

# መግቢያ

## I የፌዴራል ፍርድ ቤቶችስትራቴጂያዊ ዕቅድ አስፈላጊነትና ዓላማዎች

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት ኢትዮጵያን የፌደራል ስር. ዓት የምትከተል ሀገር በማድረግ የፌደራልና የክልል መንግስታትን አዋቅሯል። ሕገ መንግስቱ በስልጣን ክፍፍል መርህ የሚመራ በመሆኑ በፌደራልም ሆነ በክልል መንግስታት የሕግ አውጪ፣ የሕግ አስፈፃሚና የዳኝነት አካላት ተደራጅተዋል። በፌደራልም ሆነ በክልል የተደራጁት ፍርድ ቤቶች የየራሳቸው አወቃቀር፣ አደረጃጀትና ስልጣን ያላቸው ሲሆን የሀገሪቱ የዳኝነት ስልጣን የእነዚሁ ፍርድ ቤቶች ብቻ ነው። የፌደራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን ከሕገ መንግስቱና በተዋረድ ከወጡ ሌሎች ሕጎች የሚመነጭ ሲሆን ነጻ፣ ግልጽና ተጠያቂነት ያለው ዳኝነት እንዲሰጡ የሕገ መንግስቱ ድንጋጌዎች ያስገድዷቸዋል።

የፌደራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣኑን በስራ ላይ ለማዋል በዕቅድ መመራት ከጀመሩበት ጊዜ አንስቶ ሁለት ስትራቴጂያዊ ዕቅዶችን ያዘጋጁ ሲሆን ሶስተኛውንና ከ2014-2018 የሚተገብሩ ግቦችን፣ ስትራቴጂዎችንና ተግባራትን የሚያመላክት የአምስት ዓመት ስትራቴጂያዊ ዕቅድ አዘጋጅተዋል። ይህ ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ቀደም ብለው የተተገበሩትን ስትራቴጂያዊ ዕቅዶች ተከትሎ የተዘጋጀ ሲሆን በፍርድ ቤት ውስጥ የተጀመሩትን የለውጥ ስራዎች ለማሳካት በ2011 ዓ.ም መጨረሻ የተዘጋጀውን የሶስት ዓመት ፕሮጀክቶች ዕቅድ ግምት ውስጥ አስገብቷል። ዕቅዱ የተዘጋጀው የሕዝብን ነፃ፣ ቀልጣፋና ጥራት ያለው የዳኝነት አገልግሎት የማግኘት መብት ለማስከበር ሲሆን በእነዚህ መሰረታዊ መርሆዎች ላይ የተመሰረተ ዕቅድ አዘጋጅቶ መተግበር የሕዝብ አመኔታ ለማግኘት ያስችላል ተብሎ ይታመናል። የፍርድ ቤቶችን ሃብት በአግባቡ ተጠቅሞ ለታለመለት ዓላማ እንዲውል ለማድረግም ያግዛል። የስትራቴጂክ ዕቅዱ ዋና ዓላማ የፍርድ ቤቶችን ስትራቴጂያዊ አቅጣጫዎች አመላክቶና ተልዕኮን መወጣት የሚያስችሉ ተግባራትን አከናውኖ መልካም እሴቶችን በመከተል በስትራቴጂክ ዘመኑ የሚደረስበትን ራዕይ ማሳካት ሲሆን ዝርዝር ዓላማዎቹ ፍርድ ቤቶች ፡-

- በኢትዮጵያ የሕግ ስርዓት ውስጥ ሕገ መንግስታዊ ሚናቸውን በአግባቡ እንዲወጡ፤
- የዳኝነት ነፃነትን ያስከበረ፣ ቀልጣፋና ጥራት ያለው የዳኝነት አገልግሎት እንዲሰጡ፤
- ተልዕኳቸውን ከተሻሻሉ ሕጎች እና ከሀገሪቱ የአስር ዓመት የልማት ዕቅድ ጋር እንዲያጣጥሙ፤
- የበላይ አመራር አካላት ስትራቴጂያዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ አተኩረው እንዲሰሩ፤
- ከባለድርሻ አካላት ጋር የሚኖረውን መስተጋብር በዕቅድና በእውቀት በመምራት፣ ሕግና መርህን መሰረት ያደረገ ቅንጅታዊ አሰራር እንዲያጎለብቱ፤

- ሃብት ከፍተኛ እሴት በሚጨምሩና ቅድሚያ በሚሰጣቸው ጉዳዮች ላይ እንዲወጣ፤
- የዳኝነት ነፃነትና ተጠያቂነት መርሆች ሚዛን በጠበቀ አግባብ እንዲተገበሩ፤ እና
- በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያላቸውን መርሆዎችና አሰራሮች በመጠቀም ወደ ልህቀት ደረጃ እንዲሻገሩ

ማድረግ ነው፡፡

# II የፌደራል ፍርድ ቤቶች ስትራቴጂያዊ ዕቅድ አፈጻጸምና የተገኙ ልምዶች

የፌደራል ፍርድ ቤቶች ሀገራዊ የእድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድን መሰረት ያደረጉ ሁለት ተከታታይ (2003-2007 እና 2008-2012) ስትራቴጂያዊ ዕቅዶችን አዘጋጅተው ሲተገብሩ ቆይተዋል፡፡ ከ2008-2012 እንዲተገበር ተዘጋጅቶ የነበረው ስትራቴጂያዊ ዕቅድ እስከ 2010 ዓ.ም ሲተገበር ቢቆይም በ2011 ዓ.ም የተደረገውን የፍርድ ቤት አመራር ለውጥ ተከትሎ የዳኝነት ነጻነት፣ ገለልተኝነትና ተጠያቂነትን ማጠናከር፤ የዳኝነት አገልግሎት ጥራትን ማሳደግ፤ የዳኝነት አገልግሎት ቅልጥፍና ማሻሻል እና አስተዳደራዊ ድጋፎችን ማጠናከር የሚሉ አራት ግቦች ተመርጠውና ግቦችን ለመለካት የሚያስችሉ መለኪያዎች ተቀምጠው የተዘጋጁ ሁለት ዓመታዊ ዕቅዶች ሲተገበሩ ቆይተዋል፡፡ ከዚህም በላይ ለእነዚህ ግቦች ስኬት የሚያግዙ ከ36 በላይ ፕሮጀክቶችን የያዘና ከ2011-2014 ዓ.ም የሚተገበር የሶስት ዓመት ፕሮጀክት ዕቅድ ተዘጋጅቶ በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡

ከ2008-2012 የነበረው የፌደራል ፍርድ ቤቶች ስትራቴጂያዊ ዕቅድ የ2012 በጀት ዓመት ዕቅድ ለማዘጋጀት በተካሄደ የባለሙያዎች ግምገማ የተገኙ ውጤቶች፣ የታዩ ጥንካሬና ድክመቶችን ተመላክተዋል፡፡ ከዚህ ግምገማ ግኝቶች መካከል በዋናነት የሚጠቀሱት ቀጥሎ በቀረበው ሰንጠረዥ እንዲቀርቡ ተደርጓል፡፡

## የፌደራል ፍርድ ቤቶች ስትራቴጂያዊ ዕቅድ (2008-2012) አፈጻጸም ግምገማ ግኝቶች

የፌዴራል ፍድ ቤቶች ስትቴጂያዊ ዕቅድ (2008-2012) አፈጻጸም ግምገማ በእንዳንዱ ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች የተገኙ ውጤቶች የአፈጻጸም ጥንካሬዎች እና ድክመቶችን ለይቷል፡፡ የአመራር ዳኞችና ሰራተኞችን የሙ ብቃትና የለውጥ አመለካከት ማሳደግ ስትራቴጂያዊ ጉዳይ አንጻር በተበታተነ ሁኔታም ቢሆን የአቅም ግንባታ ተግባራትን በማከናወን የትምህርት መርኃግብር ተጀምሯል፤ በርካታ የስልጠናዎችም ሲሰጡ ቆይተዋል፡፡ በአገር ውስጥና በውጭ አገር በተዘጋጁ ስልጠናዎች የተወሰኑ አመራሮችና ዳኞች መሳተፋቸው እና ሌሎች ባዘጋጁዋቸው ስልጠናዎች በርካታ ሠራተኞች እንዲሳተፉ መደረጉ እንደ ጥንካሬ የታዩ ሲሆን በየበጀት ዓመቱ የትምህርት ዕድል ለማመቻቸት ቢታቀድም እስከ 2011 ዓ.ም ይህ አለመፈጸሙ እና ስልጠናዎች በተያዘላቸው ዕቅድ መሰረት አለመሰጠታቸው በደካማ አፈጻጸም ተለይተዋል፡፡

የዳኝነት ነጻነት፣ ገለልተንነትና ተጠያቂነትን የተመለከቱ ስትራቴጂያዊ ጉዳዮችን ለማሳካት በተከናወኑ ተግባራት በስትራቴጂክ ዘመኑ መጨረሻ የ2012 በህገመንግስቱ ላይ በተደነገገው መሰረት ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የበጀት ዓመቱን በጀት በምክር ቤት አጸድቆ የዳኝነት ነጻነትን ማስከበር ጀምሯል፡፡ በመርሆች አፈጻጸም ዙሪያ ግንዛቤ እንዲኖር የሚያደርጉ የተወሰኑ መድረኮች መዘጋጀታቸው፤ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ተጠያቂነትን ተግባራዊ ለማድረግ የሚከናወኑ ተግባራት መኖራቸው፣ እና የመርሆችን አፈጻጸም ደረጃ ለመለየት የሚያግዙ የተወሰኑ የኢንስፔክሽን ሪፖርቶች መዘጋጀታቸው በግምገማው እንደጠንካራ ጎን የተወሰዱ ሲሆን የዳኝነት ነጻነትን ለማስከበር ገፍቶ መሄድ ያስቻሉ ዕርምጃዎች አለመወሰዳቸው፤ የፍርድ ስራ ምርመራ እና ኢንስፔክሽን ክፍል በጉባዔው ጽ/ቤት አደረጃጀት ይካተታል በሚል ተቋርጦ መቆየቱ፤ እና በጀትን ከአስፈጻሚው አካል ተጽዕኖ ማላቀቅ ሳይቻል መቆየቱ የአፈጻጸም ድክመቶች መሆናቸውን አመልክቷል፡፡

የአገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነትን ማለትም (ቅልጥፍና፣ ጥራት፣ ተደራሽነት፣ ግልጽነት እና ምቹ የስራ ከባቢዎችን ማሻሻል) ማሳደግን ግብ በማድረግ በተከናወኑ ተግባራት የተገኙ ውጤቶችን ለመለየት በተደረገ የአፈጻጸም ግምገማ ዕልባት ያገኙ መዛግብት መጠን ጨምሯል፡፡ በኢኮቴ (ቪዲዮ ኮንፈረንስ እና ኢፋይሊግ) የተደገፈ አገልገሎት በመስጠቱ የክልል ተገልጋዮች ከፍተኛ ወጭ ቀንሷል፡፡ ለጠቅላይ ፍ/ቤት ጊዚያዊ መፍትሔ የሰጡ ሕንጻዎች ተገንብተዋል፡፡ የጠ/ፍ/ቤት የግንባታ ቦታ ተመልሶ ቢወሰድም ለከፍተኛ ፍ/ቤት ሕንጻ ለመገንባት ቦታ ተገኝቷል፡፡ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን በማዕከል ደረጃ ለዳኞች፣ ሠራተኞችና ተገልጋዮች መጸዳጃ ቤቶች፣ ካፍቴሪያዎች... ተዘጋጅተዋል፡፡

በዚህ ረገድ ቅልጥፍናን አሻሽሎ ዕልባት የሚያገኙ መዛግብትን መጠን ለማሳደግ ጥረት መደረጉ፤ ተደራሽነትን ለማሳደግ የሚያስችሉ የኢኮቴ ስርዓቶች መጠናከራቸው፤ ግልጽ ችሎት ለማካሄድ እንቅፋት ለሆኑ ችግሮች ጊዜያዊና ዘላቂ መፍትሔ ለመስጠት መሞከሩ፤ አበረታች ቢሆንም፤ የአገልግሎት ቅልጥፍና እና ተደራሽነትን ለማሳደግ የተደረጉ ጥረቶችን ያህል ጥራትን ለማሳደግ አለመቻሉ፣ ተደራሽነትን የሚያጎለብቱ አዳዲስ የኢኮቴ ሥርዓቶች አለመልማታቸው፣ ለከፍተኛ ፍ/ቤት የችሎትና ቢሮ ችግሮች ጊዜያዊ መፍትሔ ለመስጠት ሊገነቡ የታቀዱ ሕንጻዎች ሳይጀመሩ ረጅም ጊዜ መውሰዱ እና በየምድብ ችሎቶች ምቹ ከባቢ ለመፍጠር ተመሳሳይ ዕርምጃ አለመወሰዱ በውስንነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

የገጽታ ግንባታ እና የመረጃ ስርጭት ስራዎች እየተሻሻሉ መምጣታቸውን በውጤታማነት ያመላከተው ግምገማ የሚዲያ እና ኮሚዩኒኬሽን ስራ የፍርድ ቤቶቹን ገጽታ መገንባትና መጠበቅ በሚያስችልበት ሁኔታ ላይ አለመሆኑ እና የስራ ክፍሉ በአግባቡ አለመደራጀቱ እንደችግር ተጠቁሟል፡፡

የሠራተኞች ደመወዝ በመስተካከሉ የሰው ሃብት ፍልሰቱን መቀነስ መቻሉ፤ የበጀትና ንብረት አጠቃቀምን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ መደገፍ መቻሉ፤ ለሶስቱም ፍርድ ቤቶች የተፈቀደው በጀት ባልተማከለና ዕቅድን መሰረት ባደረገ ሁኔታ ጥቅም ላይ እንዲውል መደረጉ በሃብት አጠቃቀምና ውጤታማነት የትኩረት መስክ የተገኙ መልካም ውጤቶች ናቸው፡፡ ነገር ግን የገንዘብ ሚ/ር በየበጀት ርዕሱ የሸነሸነውን በጀት ይሁንታ ሳይገኝ አዘዋውሮ መጠቀምና ለሚፈለገበት ዓላማ ማዋልም ሆነ ማስተዳደር አለመቻሉ ዕቅድን መሰረት ያደረጉ አቅርቦቶች እንዳይሟሉ አድርጓል፡፡ በመጨረሻም የተገልጋይ እርካታና የህዝብ

አመኔታ ከማሳደግ ጋር ተያይዞ ከውስን ተገልጋዮች የተገኙ አስተያየቶችን መነሻ በማድረግ የማስተካከያ እርምጃዎች መወሰዳቸው አወንታዊ ውጤት የተገኘበት ቢሆንም በየዓመቱ መደበኛና ተቋማዊ ይዘት ባለው መልኩ የተገልጋይ አስተያየት መሰብሰብና እርካታን መለካት የሚያስችል የዳሰሳ ጥናት አለመደረጉ የህዝብ አመኔ ደረጃን ለመለየት አለመቻሉ ተገምግሟል፡፡

በሁለተኛው ስትራቴጂክ ዘመን ዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ ከለይ የተለዩ ግኝቶች የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሚሰጡዋቸውን አገልግሎቶች በዕቅድ ለመምራትና ለማሻሻል ባደረጉዋቸው ጥረቶች የተወሰኑ ውጤቶች ማግኘታቸውን ያመልክቱ እንጂ ያጋጠሙዋቸው ችግሮች መፍትሔ እንዲያገኙ ባለመደረጋቸው የሚፈለገውን ውጤት ለማግኘት አልቻሉም፡፡ በአጠቃላይ ያለፉት ዓመታት የፌደራል ፍርድ ቤቶች ስትራቴጂክ ዕቅድ ዝግጅቶች ሚዛናዊ የዕቅድ አፈጻጸም ምዘና ሥርዓትን ተከትለው በተሟላ መልኩ የተዘጋጁ መሆናቸውን ያመላከቱ መረጃዎች ቢገኙም አፈጻጸማቸውን ተከታትሎ በመገምገምና ክፍተቶችን እየሞሉ በመሄድ ለተገኙ ውጤቶች መረጃዎችን መሰረት ያደረገ ተገቢ ዕውቅና በመስጠት ረገድ ክፍተቶች ታይተዋል፡፡

የየትኛውም ተቋም ስትራቴጂያዊ ዕቅድ በዝግጅትም ሆነ በትግበራ ሂደቱ የበላይ አመራሩን ግንባር ቀደም ተሳትፎ ይፈልጋል፡፡ ስትራቴጂያዊ ዕቅድንም ሆነ ሌሎች የለውጥ ፕሮግራሞችን በበላይ አመራር ባለቤትነት ተግባራዊ ማድረግ የሚፈለጉ ውጤቶችን ለማግኘት ከማስቻሉም በላይ የተቋሙን ማህበረሰብ በንቃት አሳትፎ ሁሉን አቀፍ ለውጥ ለማምጣት ያስችላል፡፡ ከዚህ አንጻር ላለፉት ሶስት አመታት እንዲያገለግል በተዘጋጀው የፕሮጀክት ዕቅድ ዝግጅት እና አፈጻጸም ሂደት የበላይ አመራሩ የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ባለመለየቱ ካለፉት ዓመታት ስትራቴጂክ ዕቅዶች የተሻለ ውጤት ለማግኘት መቻሉን ማሳያ ማድረግ ይቻላል፡፡ በሌላም በኩል ከእነዚህ ዕቅዶች ዝግጅትና አፈጻጸም የሀገሪቱ የፖለቲካ ፍላጎት በፍርድ ቤቶች ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ዝግጅትና አፈጻጸም ነጻነት ላይ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድር መሆኑን መረዳት አስችሏል፡፡

የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሥራ በቀጠሮ (በአጀንዳ) እንጂ በዕቅድ አይመራም ከሚለው የረዥም ጊዜ ብሂል ወጥተው በዕቅድ መምራት መጀመራቸው የሚበረታታ ቢሆንም በአቅም ውሱንነት፣ በቁርጠኝነት መጓደልና በተጠያቂነት አለመኖር የተነሳ የዕቅድ ዝግጅት፣ ክትትልና ምዘና ደረጃውን በጠበቀና ወጥነት ባለው አግባብ እየተገመገመ ተገቢው እርምጃ አለመወሰዱ ከፍተኛ ጉድለት ተደርጎ ተወስዷል፡ በመሆኑም የአፈጻጸም ምዘና ሥርዓት ሲዘረጋ አፈጻጸምን በፍርድ ቤት፣ በሥራ ክፍል፣ በቡድንና በግለሰብ ፈጻሚ ደረጃ ሊታይና ከአስፈላጊው የአቅም ግንባታና ተጠያቂነት ሥርዓት ጋር ሊፈጸም ይገባል፡፡

በየደረጃው የሚገኙ የአመራር አካላት ሚናም የዕቅድ ዝግጅትን ተከታትሎ የአፈጻጸም አመራር ሥርዓትን ማጠናከርና አፈጻጸሙን በጥብቅ ዲሲፕሊን መምራት ላይ ማተኮር ይገባዋል፡፡

- በዚህ ረገድ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የአፈጻጸም ምዘና ሥርዓት ዘርግተው ሲተገብሩ ቢቆዩም ተገቢው ክትትልና ግምገማ ባለመደረጉና የተጠያቂነት ሥርዓት ባለመጠናከሩ ለሁሉም ፈጻሚዎች ተቀራራቢና ከፍተኛ ውጤት በመስጠት ሥርዓቱን በተገቢው መንገድ መፈጸም ሳይቻል ቀርቷል፡፡ የፈጻሚዎች፣ የሥራ ክፍሎችም ሆነ የተቋሙ የጋሸበ የምዘና ውጤት

በፍርድ ቤቶቹ ተገልጋዮች ዕርካታ ዕድገት ላይ ያሳየው ለውጥ በሌለበት ሁኔታ የተሰጠው ውጤት ትርጉም አልባ ይሆናል፡፡ የየሩብ ዓመቱንም ሆነ ዓመታዊ የዕቅድ አፈጻጸምን ተከታትሎ መገምገም ወቅታዊ ለውጦችን ለማምጣት ቢያስችልም የስትራቴጂያዊ ግቦችን ውጤታማነት መለየት ያስቻለ ግምገማ ማካሄድና ማስተካከያዎችን ማድረግ ካልተቻለ የስትራቴጂክ ዕቅዱን ትክክለኛነትና አግባብነት ለማረጋገጥና ከተለዋዋጭ ሁኔታዎች ጋር እያዛመዱ ለመፈጸም አያስችልም፡፡ ይህም የስትራቴጂያዊ ግቦች አፈጻጸም ከኦፕሬሽን ዕቅድ አፈጻጸም ጋር ተሳስሮ መገምገም የሚያስፈልገው መሆኑን አመላክቷል፡፡

- የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስትራቴጂክ ዕቅድ ሌላው ክፍተት በኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ አለመደገፉ ነው፡፡ማንኛውም የስትራቴጂያዊ አፈጻጸም ሥራ አመራር መረጃ ማሰባሰብና ትንተና በኢኮቴ መታገዝ ይኖርበታል፡፡ ኢኮቴ የአፈጻጸም መረጃዎች በጥራትና በቅልጥፍና እንዲደራጁ፣ እንዲተነተኑና ሪፖርት እንዲደረጉ ያግዛል፡፡ የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ሥራው በበቂ ሁኔታ በኢኮቴ ባለመደገፉ ምክንያት የአፈጻጸም መረጃ ጥራት፣ አግባብነትና ተደራሽነት በሚፈለገው ደረጃ አልዳበረም፡፡ ለስትራቴጂክ ዕቅድ ውጤታማነት የአቅም ግንባታ ሥራዎች ተገቢ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ የሰው ኃይል አቅምን ማጎልበት፣ የአሠራርና የአደረጃጀት ማሻሻያዎችን ማድረግ ባልተቻለበት ሁኔታ ከስትራቴጂክ ዕቅድ የሚፈለገውን ውጤት ማግኘት አዳጋች ይሆናል፡፡ የአቅም ግንባታ ሥራዎች የሰው ኃይሉን የመፈጸም ዝግጁነት ለማረጋገጥ ሲባል የሚከናወኑ በመሆኑ ከስትራቴጂያዊ ዕቅድ ዝግጅት ትግበራና ግምገማ ጎን ለጎን የፈጻሚዎችን አቅም መገንባት ይኖርበታል፡፡ ተሰጥኦ ያለውን አመራርና ሙያተኛ የመሳብ፣ የማቆየት፣ የማልማትና የመጠቀም አቅም መገንባት ባልተቻለበት ሁኔታ የለውጥ ሥራዎችን ማሳካትም አለመቻሉን ካለፉት ዕቅዶች አፈጻጸም ልምድ ማግኘት ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል የአቅም ግንባታ ሥራዎች ተቋማዊ ፋይዳ በአግባቡ ሊገመገምና ውጤታማነቱ እየተለየ ቀጣይነት እንዲኖረው ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

# III የሶስተኛው ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ዝግጅት ሂደት

የስትራቴጂያዊ ዕቅድ ዝግጅት ሂደት አሳታፊ እና በርካታ የምክክር ሂደቶችን ያለፈ ሲሆን ይህም ዕቅዱን በአመራር፣ በዳኞች እና በሠራተኞች ዘንድ ተገቢው ግንዛቤ እንዲኖርና በባለቤትነት ስሜት እንዲፈጸም ለማድረግ ያስችላል፡፡ በዕቅድ ዝግጅቱ ሂደት ከሶስቱም ፍርድ ቤቶች የተውጣጡ የበላይ አመራሮች፣ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች የተሳተፉባቸው ዓብይ እና ቴክኒክ ኮሚቴዎች ተደራጅተው በአማካሪዎች የሚቀርቡ ረቂቆችን ተከታትለው በመገምገም፣ በማረምና ማሻሻያ ሀሳቦችን በመስጠት ከፍተኛ ሚና ሲጫወቱ ቆይተዋል፡፡

በዚህ አካሄድ ለስትራቴጂያዊ ዕቅድ ዝግጅቱ መሰረት የሆኑ ጥናቶችና ትንተናዎች የተከናወኑ ሲሆን በሶስቱም ፍርድ ቤቶች ካሉ አመራሮች፣ ከተመረጡ ዳኞችና የአስተዳደር ሰራተኞች ጋር በርካታ ቃለ መጠይቆች ተካሂደዋል። ከቁልፍ መረጃ ሰጪዎች እና በየደረጃው ከሚገኙ ዳኞች እና ሌሎች የአስተዳደር ሰራተኞች ጋር የአትኩሮት ቡድን ውይይቶች ተደርጓል። ከውይይቶቹ የተገኙት አስተያየቶች በግብአትነት በመጠቀም በየደረጃው የተዘጋጁ ረቂቆች ተቋሙን ወክለው ለሚከታተሉና ለሚገመግሙ ኮሚቴዎች ቀርበው ከመዳበራቸውም ሌላ የፍርድ ቤቶቹን የበላይ አመራሮች ጨምሮ ከሶስቱም ፍርድ ቤቶች የተወከሉ ዳኞች፣ የአስተዳደር ክፍል ኃላፊዎች፣ ሠራተኞች፣ ከፌዴራልና ከክልል የተጋበዙ ባለድርሻ አካላት የተሳተፉባቸው የውይይት መድረኮች ተዘጋጅተው ተጨማሪ ሃሳቦች ተሰባስበዋል። ከዚህም ባሻገር በዝግጅቱ ሂደት የቀደሙት ዕቅዶች በግብአትነት ከማገልገላቸውም በላይ ሕገ መንግስቱ፣ ከፍርድ ቤት ተግባር ጋር ተዛማጅ የሆኑ ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ልዩ ልዩ ጥናቶች፣ የፍርድ ቤት ሪፖርቶች፣ ዓለም አቀፍ ስታንዳርዶች፣ የውጪ ሀገር ልምዶች እና ሌሎች ሰነዶችም ተዳሰዋል። በአጠቃላይ በዝግጅቱ ሂደት ከውስጥ ባለድርሻ አካላት ባሻገር የውጪ ባለድርሻ አካላት በመረጃ ሰጪነትና በውይይት መድረኮች እንዲሳተፉና ሀሳባቸውን እንዲሰጡ ተደርገዋል።

# ክፍል አንድ

## 1 የሁኔታዎች ትንተና

### 1.1. የፌደራል ፍርድ ቤቶች አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር

ኢትዮጵያ ከ2013-2022 የሚፈጸም የልማት ዕቅድ አውጥታለች። ዕቅዱ ጠንካራ ተቋማትን ለመገንባት እንዲቻል የፍትሕ አካላት እና የፍርድ ቤቶች አደረጃጀት መስተካከሉን የሚያመለክት ሲሆን ለሰብአዊ መብት መከበር፤ ለዲሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ የሚያግዙ አዳዲስ ሕጎች መውጣታቸውን እና ነባር ሕጎችም መሻሻላቸውን ያመለክታል። የወጡ ሕጎች ተግባራዊ እንዲሆኑ እንዲሁም ወጥ የሆነ የሕግ አተገባበር እንዲኖር የሚያደርጉ የአደረጃጀትና የአሠራር ሥርዓቶች መዘርጋታቸውን ዕቅዱ የሚያመለክት ሲሆን የፍትህ ተደራሽነትና የመልካም አስተዳደር ጉዳዮች የዕቅዱ ምሰሶዎች መሆናቸውን አመላክቷል። እነዚህ ምሰሶዎች ደግሞ በዋናነት የዳኝነት አካሉ ከሚያከናውናቸው ተግባራት የሚጠበቁ ውጤቶች ናቸው።

በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 50 በግልፅ እንደተደነገገው በፌደራል እና በክልሎች የተዋቀረው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ መንግስት የፌዴራልም ሆነ የክልል መንግሥታት የህግ የማውጣት፣ የህግ የማስፈጸም እና ዳኝነት የመስጠት ስልጣን እንዲኖራቸውና የስልጣን ክፍፍላቸው በግልጽ እንዲቀመጥ ተደርጓል። በዚህ የስልጣን ክፍፍል የፌደራል እና የክልል ፍርድ ቤቶች ራሳቸውን ችለው እንዲዋቀሩ እና የመዳኘት ስልጣን እንዲኖራቸው ተደርጓል። በፌደራልም ሆነ በክልል ደረጃ የዳኝነት ስልጣን የፍርድ ቤቶች ብቻ ከመሆኑም በላይ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 79 የተቋቋመው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፌደራል መንግስቱ ከፍተኛ፣ የበላይና የመጨረሻ የዳኝነት አካል መሆኑን የሕገ መንግስቱ አንቀጽ 78(2) በግልጽ አስቀምጧል።

በሶስት ደረጃ የተደራጁ የፌደራል ፍርድ ቤቶች ዋና መቀመጫቸው አዲስ አበባ ሲሆን የፌደራል ከፍተኛ እና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በሁለት ሶስተኛ ድምጽ ውሳኔ በሃገሪቱ በሙሉ ወይም በከፊል ሊደራጁ ይችላሉ። ሆኖም የተወካዮች ምክር ቤት ፍርድ ቤቶቹ እንዲደራጁ እስኪወስን ድረስ ስልጣናቸውን ለክልል ፍርድ ቤቶች በውክልና ሰጥተው ያሠራሉ። በአሁኑ ወቅት ፍርድ ቤቶቹ በአዲስ አበባ እና በድሬዳዋ ምድብ ችሎቶች ተደራጅተው አገልግሎት እየሰጡ ሲሆን ሁሉም ፍርድ ቤቶች በመንግስት የስራ ሰዓት ተጠቅመው ተገልጋዮቻቸውን ያስተናግዳሉ። አጣዳፊ ጉዳዮችን ለማየት ከሚሰየሙ የተወሰኑ ችሎቶች በስተቀር የሁሉም ፌዴራል ፍርድ ቤት ችሎቶች ከነሐሴ 01 እስከ መስከረም 30 ዝግ ቢሆኑም ፈቃደኛ የሆኑ የተወሰኑ ዳኞች ውዝፍ መዛግብትን የማጥራት ተግባር ያከናውናሉ።

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ አንድ ፕሬዝዳንት እና አንድ ምክትል ፕሬዝዳንት የሚኖረው ሲሆን የዳኞች

ቁጥር በሕጉ የተወሰነ አይደለም። ፕሬዚዳንቱና ምክትል ፕሬዚዳንቱ በጠቅላይ ሚኒስቴሩ አቅራቢነት በምክር ቤት የሚሾሙ ሲሆን በዳኞች አስተዳደር ጉባዔ የተመለመሉ ዳኞች በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሾማሉ። የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት በሕግ መሰረት የፌደራል ፍርድ ቤቶችን የማስተዳደር ኃላፊነት አለበት። ፍርድ ቤቱ የወንጀል እና የፍትሐብሄር ችሎቶች የሚኖሩት ሲሆን የክስ ይዛወርልኝ፣ የይግባኝ፣ የምርጫ እና የሰበር ጉዳይ ላይ እና በሌሎች ሕጎች በተጠቀሱ ጉዳዮች ላይ የዳኝነት ስልጣን አለው። ሀገራዊ ስልጣን ያለው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በአዲስ አበባ ተቀማጭ ሆኖ መሰረታዊ የሕግ ስሕተትን ለማረም በሚያስችለው የሰበር ችሎት የሚሰጠው የሕግ ትርጉም ከተሰጠበት ቀን አንስቶ በየትኛውም ደረጃ በሚገኙ የፌደራልና የክልል ፍርድ ቤቶች አስገዳጅ ይሆናል። አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የተሰጠባቸውን የሰበር ውሳኔዎች ፍርድ ቤቱ በተቻለ ፍጥነት በኤሌክትሮኒክስ ወይም በህትመት ሚዲያዎች የማሳተም ግዴታ ተጥሎበታል።

በተሻሻለው አዋጅ መሰረት የከፍተኛ እና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች አንድ ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንቶች፣ በምድብ ችሎቶች ልክ የሚወሰን የምድብ ችሎት ተጠሪ ዳኛ፣ እንደየችሎቱ ሁኔታ ሰብሳቢ ዳኛ፣ ለስራው የሚያስፈልጉ ዳኞች እና ሌሎች ሰራተኞች ይኖራቸዋል። ፕሬዚዳንቶቹ በየፍርድ ቤታቸው ችሎቶች ሰብሳቢ ሆነው ያስችላሉ። የፌደራል ፍርድ ቤቶችን በአጠቃላይ የማስተዳደር ስልጣን እንዲሁም የየፍርድ ቤቶች ሰብሳቢ ዳኞችን የመደልደል ስልጣን የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ኃላፊነት ነው። አዋጁ እንደሚደነግገውም የየፍርድ ቤቶቹ ፕሬዚዳንቶች፣ ም/ፕሬዚዳንቶች፣ ምድብ ችሎት ተጠሪ ዳኞች ከዳኝነት ስራቸው በተጨማሪ አስተዳደራዊ ኃላፊነት (ስልጣንና ተግባር) ያላቸው ሲሆን ሰብሳቢ ዳኞችም ከዳኝነት ስራቸው በተጨማሪ የተወሰነ አስተዳደራዊ ተግባርና ኃላፊነት አላቸው፡፡ ፕሬዚዳንቶቹ ይህንን ኃላፊነት የሚወጡት በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት አመራር እና ክትትል ስር በመሆን ነው።

አዋጁ የፌደራል ፍርድ ቤቶች ተጠያቂነት ባለው ሁኔታ ውጤታማ፣ ተገማችና ቀልጣፋ በሆነ አሠራር የዳኝነት ተግባራቸውን አከናውነው የሕግ የበላይነት እና የሰብአዊ መብቶችን በማክበርና በማስከበር የበኩላቸውን አስተዋጽዖ እንዲያበረክቱ ደንግጓል። የፌደራል ፍርድ ቤቶችን እና የፕሬዝደንቶችን ስልጣንና አደረጃጀት፣ የፌደራል ፍርድ ቤቶች ጉባዔን፣ የፍርድ ቤት መር አስማሚነትን፣ የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር እና መሰል ጉዳዮችን በተመለከተ ዝርዝር ድንጋጌዎችን አካትቷል።

የፌደራል ፍርድ ቤቶች ሕገ መንግስትን፣ የፌደራል ሕጎችን ወይም ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን መሠረት በማድረግ በሚነሱ ክርክሮች፣ በፌደራል ሕግ በተገለጹ ጉዳዮች ወይም ቦታዎች በሚነሱ ጉዳዮች ላይ የወንጀልና የፍትሐብሔር ዳኝነት ስልጣን አላቸው። የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ጉዳዮችን የሚመለከት ቢሆንም በሕግ በግልጽ በተደነገገ ጊዜ የይግባኝ ዳኝነት ስልጣንም ይኖረዋል፡፡፡ ከፍተኛው ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ክስ እና የይግባኝ ስልጣን ያለው ሲሆን በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ስልጣኑ ከብር አስር ሚሊዮን በላይ በሆኑ የተለያዩ የፍትሐብሔር ጉዳዮች እና በቅርቡ በጸደቁ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 11(3-4) እንደተገለጸው በሕገመንግሥቱ ምዕራፍ ሶስት የተመለከቱ መሰረታዊ መብቶችና ነጻነቶች ጥሰትን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ የዳኝነት ስልጣን አለው። የአስተዳደር ሥነ ሥርአት አዋጅ

ቁጥር 1183/2012 በበኩሉ የአስተዳደር አካላት ውሳኔ ሊሰጡ እንደሚችሉ፣ በውሳኔያቸው ላይ ቅሬታ ሊቀርብበት እንደሚችል እና በዚህ ውሳኔ ቅሬታ ያለው አካል ጉዳዩ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በክለሳ እንዲታይ ማቅረብ የሚቻል መሆኑን ደንግጓል። ይህ ስርዓት የዳኝነት ስልጣንን ከማስጠበቅ አንጻር ከፍተኛ ትርጉም የሚሰጠው ሆኖ ታይቷል።

ከመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በይግባኝ የሚመጡ ጉዳዮችን በተመለከተ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያልተገደበ የይግባኝ ስልጣን አለው። ፍርድ ቤቱ የሕገ መንግስትና የሽብር ወንጀል፣ ውንብድና፣ ጸረ ሙስና ወ.ዘ.ተ. ጉዳዮች የሚታዩባቸው የወንጀል ችሎቶች ሲኖሩት በፍትሐብሄር የቤተሰብ፣ የኮንስትራክሽን፣ የስራ ክርክር፣ የንግድ፣ የውል ወ.ዘ.ተ. ችሎቶች አሉት። የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተመሳሳይ በተለያዩ ችሎቶች የተደራጀ ሲሆን ፍርድ ቤቶቹ ከዳኞች ውጪ ያሉ ሰራተኞችን የመመልመል፣ የመቅጠር፣ የመመደብ፣ የዲሲፕሊን ጉዳዮችን የመከታተል እና በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚወጣ ደንብ መሰረት እርምጃ የመውሰድ ስልጣን ተሰጥቷቸዋል።

አዋጅ ቁጥር 322/1995 በአፋር፣ ቤኒሻንጉል፣ ጋምቤላ፣ ሶማሌ እና ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የፌደራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት እንዲደራጅ ቢደነገግም በሕጉ መሰረት ያልተደራጀ በመሆኑ በእነዚህ ክልሎች የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዳኝነት አገልግሎት የሚሰጠው ተዘዋዋሪ ችሎቶችን በማደራጀት ሲሆን በቅርቡም በሃዋሳ ከተማ ቋሚ ችሎትን በማቋቋም ስራውን በቋሚነት ማከናወን ጀምሯል። በሌሎች ክልሎች ማለትም አማራ፣ ኦሮሚያ፣ ትግራይ፣ እና ሃረሪ ክልሎች ግን ስልጣኑ ለክልል ፍርድ ቤቶች የተሰጠ ነው። አዋጁ በመግቢያው ላይ በአምስቱ ክልሎች የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትን "ማደራጀት ስለማስፈለጉ" ገልጿል። በሁሉም ክልሎች የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስልጣን ለክልሎቹ የተሰጠ ነው።

በተሰጠው የስልጣን ወሰን ውስጥ የፍርድ ቤቶችን አሠራር ለማሻሻል የሚያግዙ ድጋፎችን እንዲያደርግ ኃላፊነት የተሰጠው የፌደራል ፍርድ ቤቶች ጉባኤ የተደራጀ ሲሆን የፌደራል ፍርድ ቤቶችን ፕሬዚዳንቶችና ም/ፕሬዝደንቶች፣ የክልልና ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንቶች፣ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች እና ከፌደራል ከፍተኛና መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተወከሉ ሁለት ዳኞች አባል የሆኑበት ጉባዔ ሲሆን ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ እና ሌሎች በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሚጋበዙ ግለሰቦች ያለ ድምጽ ይሳተፉበታል። ጉባኤው በፍርድ ቤቶች የገጠሙ ችግሮችን መፍትሔ የመስጠት፣ የፌደራል ፍርድ ቤቶችን የዳኝነት አሰራር ለማሻሻል የሚረዱ መመሪያዎችን የማውጣት፣ ሕጎች እንዲሻሻሉ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሃሳብ የማቅረብና ሌሎች የዳኝነት ስራን ለማቀላጠፍ የሚረዱ ተግባራትን የማከናወን ኃላፊነት ተጥሎበታል። በሌላ በኩል የዳኞችን፣ የጽህፈት ቤት ኃላፊዎችን፣ ሬጂስትራሮችን፣ ረዳት ዳኞችን፣ ሌሎች የፍርድ ቤት የስራ ኃላፊዎችን ምልመላ፣ ዲሲፕሊን፣ ዕድገት፣ ደመወዝ፣ ዝውውርና ጥቅማ ጥቅምን የመወሰን ስልጣን የተሰጠው የፌደራል ዳኝነት አስተዳደር ጉባዔም ተቋቁሟል። የዳኝነት አስተዳደር ጉባዔው የራሱ ጽህፈት ቤት ያለው ሲሆን ጽህፈት ቤቱ ዳኞች ሙያቸውን እንዲያዳብሩ የተለያዩ ስልጠናዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት ተሰጥቶታል።

ሌላው በፍርድ ቤቶች አዋጅ ዕውቅና የተሰጠው የፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት ነው። ዳይሬክቶሬቱ ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ሲሆን በሁሉም ደረጃ በሚገኙ የፌደራል ፍርድ ቤቶች

በፍትሐብሔር ጉዳዮች ላይ የሚሰጡ ፍርዶችን የማስፈጸም ኃላፊነት ተሰጥቶታል። ዳይሬክቶሬቱ በየዓመቱም በርካታ ፍርዶችን የሚያስፈፅም ቢሆንም ቀላል የማይባሉ ችግሮች ያሉበት መሆኑን መረዳት ተችሏል። እነዚህ ችግሮቹ በዝርዝር ተለይተው ካልተፈቱ ለፍትህ አስተዳደር ከፍተኛ ማነቆ ሆነው ይቆያሉ። በአጠቃላይ ዳይሬክቶሬቱ የሚመራበት የህግ ማዕቀፍ፣ አደረጃጀት፣ አሰራሩና የፋይናንስ አስተዳደር እንደገና መፈተሽና መስተካከል ያለበት ሲሆን ለፍርድ አፈጻጸም ፋይል ከተከፈተበት ጊዜ አንስቶ አሰራሩን አውቶሜት በማድረግ ስርአቱን አስተማማኝ ማድረግ ጠቃሚ ይሆናል። ለዚህም የሚሰራበትን መመሪያ ማውጣት፣ ከተወሰኑ የስራ መደቦች በላይ የሚገኙ መደቦችን በሹመት የማስያዝ አስፈላጊነትን አጥንቶ መወሰን፣ በጀትንና ሰራተኛን በማስተዳደር ረገድ ሊኖረው ስለሚገባው ነፃነት መለየት፣ በአሰራሩ ለተደጋጋሚ ቀጠሮዎች የሚዳርጉ ነገሮችን ለይቶ መፍታት፣ ከበርካታ ተቋማት ጋር በመገናኘት ስራውን የሚያከናውን በመሆኑም ቅንጅታዊ አሰራርን መፍጠርና ማዳበር፣ በውስጡ የሚመደቡ ሰራተኞች ለፍርድ አፈፃፀም ስራ በሚመች መስፈርት እንዲመረጡ ማድረግ፣ ስራዎቹ በጊዜ መመዘን የሚቻልበትን ስታንዳርድ ማውጣት፣ ለስራ ክፍሉ የተመቸ የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር ማውጣት...ለውጤታማነቱ አጋዥ ስለሚሆን በዕቅዱ ትኩረት ተሰጥቶት ሊታይ ይገባል።

የፍርድ ቤት መር አስማሚነት ስርአት በፍርድ ቤት ተግባራዊ እንዲሆን የፍርድ ቤቶቹ አዋጅ ይደነግጋል፡ ፡ ከዚሁ ጎን ለጎን አዲሱ የፍርድ ቤቶች አዋጅ ለጉዳዮች ፍሰት አስተዳደርም እውቅና የሰጠ ሲሆን የግልግል ዳኝነትን የተመለከቱ እንዲሁም የውጪ አገር ግልግል ጉዳዮች በፍርድ ቤቶች ሊፈጸሙ የሚችሉበትን ዕድል ፈጥሯል። የዚህ አሠራር ዋና ዓላማ ጉዳዮች በስምምነት እንዲቋጩ ለማድረግ፣ ጉዳዮች የሚስተናገዱበትን የጊዜ ሰሌዳ ገደብ በማስቀመጥ የፍትህ አሰጣጥ ስርአቱን ማሳለጥና ጥራቱን መጠበቅ ነው። በሌላ በኩል የዳኝነቱን ስርአት ለማሻሻል የሚያግዙ አስገዳጅ ያልሆኑ ሃሳቦች የሚያመነጩና ሌሎች የተሰጡትን ስራዎች የሚያከናውን የውጪ አማካሪ ምክር ቤት በፍርድ ቤቶቹ አዋጅ መሰረት ተቋቁሟል። የምክር ቤቱ አባላት ከቀድሞ ዳኞች፣ ከፍተኛ ልምድና ብቃት ካላቸው የህግ ባለሙያዎች እና ከዩኒቨርሲቲ ምሁራን የተውጣጡና ያለክፍያ የሚሰሩ ናቸው።

የሀገሪቱ የሕግ ስርአት ከመደበኛው የዳኝነት ስርአት በተጨማሪ በሕግ እውቅና ያላቸውን ከፊል የዳኝነት አካላት ወይንም አስተዳደራዊ ፍርድ ቤቶች የሕግ እውቅና ይሰጣል። ፍርድ ቤቶች ደግሞ በሕግ ብቻ ተመርተው ውሳኔ ወይም ፍርድ እንዲሰጡ ይጠበቃል። በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 37 ስር እንደተመለከተው ፍትህ ማግኘት ለማንኛውም ሰው የተሰጠ መብት ሲሆን መብቱ የሚረጋገጠውም ውሳኔ ወይም ፍርድ በማግኘት ነው። በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 37 መሰረት ውሳኔ ወይም ፍርድ የሚሰጡት አንድም ፍርድ ቤት አለዚያም በሕግ የዳኝነት ስልጣን የተሰጣቸው ሌሎች አካላት ሊሆኑ ይችላሉ ። ከመደበኛ የፌደራል ፍርድ ቤቶች ጎን ለጎን ሌሎች የዳኝነት ስልጣን የተሰጣቸው ፍርድ ቤቶች ሊቋቋሙ እንደሚችሉ እንዲሁም ለባህልና ለሃይማኖት ፍርድ ቤቶች እውቅና ሊሰጥ እንደሚችል ሕገ መንግስቱ በአንቀጽ 34(5) ደንግጓል። በዚህ መሰረት ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ ሌሎች ፍርድ ቤቶች ወይም ውሳኔ ሰጪ አካላት በተለያዩ አዋጆች ተቋቁመዋል። ለምሳሌም ሶስት ደረጃ ያላቸውና በተከራካሪዎች ፈቃድ ላይ ተመስርቶ የመዳኘት ስልጣን የተሰጣቸው የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች በአዋጅ ቁጥር 188/99 ተቋቁመው በስራ ላይ ይገኛሉ። የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የሸሪዓ ሕግን መሰረት በማድረግ የሚሰሩ ሲሆን መደበኛውን የሥነ ሥርዓት ሕግ የሚከተሉና በመንግስት በጀት የሚተዳደሩ ናቸው። ውሳኔያቸው ለመደበኛ ፍርድ

ቤት ይግባኝ የማይባልበት ነገር ግን ለሰበር አቤቱታ ሊቀርብበት የሚችል ነው። በተመሳሳይ በአዋጅ ቁጥር 1100/2011 በወንጀል ጉዳዮች ላይ የቀዳሚ እና የይግባኝ ስልጣን ያለው ወታደራዊ ፍርድ ቤት የተቋቋመ ሲሆን በዚህ ፍርድ ቤት በሚሰጡ ውሳኔዎች ላይ የሚፈጸም የሕግ ስህተት ቢኖር የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር ችሎት የማየት ስልጣን አለው። ውሳኔዎችን በሰበር ችሎት ከማስተካከል በተጨማሪ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከሸሪዓም ሆነ ከወታደራዊ ፍርድ ቤቶች ጋር የመተባበር፣ በአቅም ግንባታና በልዩ ልዩ የፍትህ ስርዓቱ ማሻሻያ መርሐ ግብሮች የመደገፍ እና የማሳተፍ ኃላፊነት አለበት።

የአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተማ ቻርተር ላይ እንደተመለከተው በከተማ ጉዳይ ላይ ስልጣን የተሰጣቸው በሁለት ደረጃ የተቋቋሙ የከተማ ፍርድ ቤቶች የሚገኙ ሲሆን ፍርድ ቤቶቹም በፍትሐብሔር እና በደንብ መተላለፍ ጉዳዮች ላይ ስልጣን የተሰጣቸው ናቸው። የመጀመሪያ ደረጃ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች እስከ ብር አምስት መቶ ሺህ በሚደርሱ የገንዘብ እና ብድር ክርክሮችን የመዳኘት ስልጣን አላቸው። ቻርተሩ በቀበሌ (በወረዳ) የሚነሱና ግምታቸው እስከ ብር 5,000.00 የሆኑ የፍትሐብሄር ጉዳዮችን የሚዳኙ የማህበራዊ ፍርድ ቤቶችን ያቋቁሙ ሲሆን በውሳኔያቸው ላይ ለከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሊቀርብ፣ በመሰረታዊ የሕግ ስህተት ላይ ለከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ብሎም ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ ሊታይ እንደሚችል ደንግጓል።

ከፊል የዳኝነት ስልጣን የተሰጣቸው በርካታ ሌሎች ውሳኔ ሰጪ አካላት በስርዓቱ ውስጥ ተካተዋል፡ ፡ ለምሳሌ የአሰሪና ሰራተኛ፣ የቦታ ማስለቀቅ፣ የጡረታ እና ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር፣ የመንግስት ሰራተኛ፣ የግብር፣ የጉምሩክ ሰራተኛ ዲሲፕሊን ውሳኔ፣ የመንግስት ቤቶችን የማስለቀቅ ፣ የፎርክሎዠር፣ የሸማቾች፣ የአዕምሮ እና ተዛማጅ መብቶች .... ጉዳዮች በእነዚህ አካላት ውሳኔ የሚያገኙባቸው ሕጎች ወጥተዋል። በተመሳሳይ የግልግል ዳኝነት ስርአትን ጨምሮ ሌሎች አማራጭ ክርክር መፍቻ መንገዶች እውቅና አግኝተዋል። በዳኝነት ሥርዓቱ ውስጥ ራሱን የቻለ ስልጣን የተሰጣቸው እንደ ፌደሬሽን ምክር ቤት ያሉ አካላት የሕገ መንግስታዊ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ እንዲሰጡ ስልጣን ተሰጥቷቸዋል። ይህን ስልጣን ተግባራዊ በማድረግ በርካታ ባለጉዳዮች በፍርድ ቤቶቹ ያለቁ ጉዳዮችን ለፌደሬሽን ምክር የሚያቀርቡበት አሠራር በመኖሩ ጥቂት የፍርድ ቤት ውሳኔዎች ይሻራሉ።

በሌላ በኩል በሕገ መንግስቱ ከፊል የዳኝነት ስልጣን የተሰጣቸው ሌሎች አካላት በምን ላይ የተመሰረተ የዳኝነት ስልጣን እንደሚኖራቸው የደነገገው ነገር የለም። እነዚህ አካላት መቋቋማቸው የተለመደና የማይቀር ቢሆንም ሊቋቋሙ ይገባል የሚባልበት ምክንያት በየማቋቋሚያ አዋጆቻቸው በሚያሳምን ሁኔታ ካልተቀመጠ የዳኝነት ስልጣን ትርጉም ያጣል። ማቋቋሚያ አዋጆቹ እነዚህ ውሳኔ ሰጪ አካላት ከመደበኛው (ፌደራል) ፍርድ ቤት ጋር ስለሚኖሩዋቸው ግንኙነቶች የደነገጉት ነገር ብዙ አይደለም። በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ከፊል የዳኝነት ስልጣን የተሰጣቸው አካላትን ያቋቁሙ አዋጆች በእነዚህ አካላት የሚሰጡ ውሳኔዎች የመጨረሻና ፍርድ ቤት በክለሳ የማያያቸው መሆናቸውን በመደንገጋቸው የዳኝነት ስልጣን አረዳድ የፍርድ ቤት እና የሌሎች ውሳኔ ሰጪ አካላት ግንኙነት ግልጽ አለመሆኑን ያሳያል። [1] ከዚህ በመነሳት ከሚያመለክተው የሕጉ ድንጋጌ አንጻር ፍርድ ቤቶች በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣

1 በዚህ ጉዳይ ላይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 18342 ላይ በዚህ መልክ ከተደነገገ ፍርድ ቤቶች ውሳኔዎቹን የመከለስ ስልጣን የላቸውም በማለት ትርጉም መስጠቱ ይታወሳል።

መሰል ጉዳዮች እና መብቶች ላይ ያላቸው ስልጣን የተገደበ ነው የሚል ክርክር የሚነሳ ሲሆን በሌላ በኩል ሕገ መንግስት የመተርጎም ስልጣን ለፌደሬሽን ምክር ቤት (ለሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ) የተሰጠ ስልጣን ከመሆኑ አንጻር ተመሳሳይ ክርክር ሲያስነሳ ይታያል፡

## 1.2. የፌደራል ፍርድ ቤቶች አሁን ያሉበት ሁኔታ (ጥንካሬና ድክመት) ዳሰሳና ትንተና

### 1.2.1. የዳኝነት ነጻነት፣ ገለልተኝነት፣ ግልጽነት እና ተጠያቂነት

#### የዳኝነት ነጻነት እና ገለልተኝነት

የኢ.ፌዲሪ ሕገ መንግሥት በአንቀጽ 78(1) "ነፃ የዳኝነት አካል በዚህ ሕገ መንግሥት ተቋቁሟል" በማለት የዳኝነት አካል ነፃ እና ገለልተኛ መሆኑን በግልጽ ደንግጓል። በዚህ መሰረት ዳኞች ከአስፈጻሚው፣ ከሕግ አውጪው ወይም ከማናቸውም አካል ተጽዕኖ እና ጫና ነጻ ሆነው ተግባራቸውን ማከናወን አለባቸው። በፌደራልም ሆነ በክልል የዳኝነት ስልጣን የፍርድ ቤቶች ብቻ መሆኑን የደነገገው ህገመንግሥት በአንቀጽ 79(1) ማንኛውም ዳኛ የጡረታ ዕድሜ ከመድረሱ በፊት በዲሲፕሊን ግድፈት፣ በሥራ ችሎታ ማነስ እና በህመም ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ከዳኝነት ስራው አይነሳም ብሎ መደንገጉ ለዳኝነት ነጻነት ማረጋገጫ ነው።

#### የዳኝነት ነጻነት እና ገለልተኝነት አተገባበሮችን በማሻሻል ረገድ ውጤት የታየባቸው እርምጃዎች

የዳኝነት ነጻነት እና ገለልተኝነትን በተግባር ለማረጋገጥ የፌደራል ፍርድ ቤቶች ትኩረት ሰጥተው ሲሰሩ የቆዩ ሲሆን በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የፍርድ ቤቶቹ አመራሮች ከፍተኛ ትኩረትና ቁርጠኝነት ታክሎበት አበረታች ውጤቶች በመመዝገብ ላይ ይገኛሉ። ለዚህም ቀጥለው በዝርዝር የቀረቡ ውጤቶችን አብነት ማድረግ ይቻላል።

- **የተሻሻሉ አዋጆች እና ደንቦች፦** የዳኝነት ነፃነት ከሚለካባቸው መስፈርቶች አንዱ ለዳኝነት ነጻነት በሕግ የተሰጠ ጥበቃ ሲሆን ባለፉት ሶስት አመታት የዳኝነት ነጻነትን የሚያረጋግጡ አዋጆችና ደንቦች ወጥተዋል። ከእነዚህ የሕግ ማዕቀፎች መካከል የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ፣ የፌደራል ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ አዋጅ፣ የፌደራል ዳኞች ሥነ ምግባርና የዲሲፕሊን ክስ ሥነ-ሥርአት ደንብ፣ የአስተዳደር አካላትን ውሳኔ በክለሳ የመመልከት ስልጣን የሰጡ ሌሎች ሕጎች … በማሳያነት ሊጠቀሱ ይችላሉ።

- **የፌደራል ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ አወቃቀር፦** በስራ ላይ በነበረው የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ አወቃቀር ከዳኝነት አካል ውጪ የሆኑ የጉባዔው ተወካዮች አብላጫውን ቁጥር ይዘው የነበሩ ሲሆን በተሻሻለው የዳኝነት አስተዳደር አዋጅ መሰረት የዳኝነት አካል ተወካዮች አብላጫውን ቁጥር ይዘዋል። የተሻሻለው አዋጅ በጉባዔው የሚወከሉ ዳኞች በየደረጃው ከሚገኙ ፍርድ

ቤቶች እንዲመረጡ ያደረገ ሲሆኑ የፆታ ምጣኔ ሚዛናዊነት መጠበቅ የሚያስችል ድንጋጌ በማካተቱ የጉባዔው አደረጃጀት ሴቶችን ያማከለ እንዲሆን ተደርጓል። ከዚህ በተጨማሪ የጉባዔውን ጽሕፈት ቤት ለማጠናከር በራሱ በጀት እንዲተዳደር ተደርጓል።

- **የዳኞች ነጻነት አተገባበር፦** የዳኝነት ነጻነት ዋና ችግር ትግበራው መሆኑን የተረዱ የፍርድ ቤት አመራሮች ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥተው በመከታተልና ነጻነትን ለማስከበር የሚያግዙ ተግበራትን በማከናወን እና ዳኞች ተግባራቸውን በነጻነት ማከናወን የሚያስችሉዋቸውን ሁኔታዎች በማመቻቸት በነጻነት የሚሰጡ ውሳኔዎች ዕድገት በማሳየት ላይ ይገኛሉ። ውሳኔዎች በነጻነት ተሰጥተዋል የሚባለው ውሳኔ በተሰጠባቸው አካላት አስተያየት ላይ በመመስረት ብቻ ሳይሆን ዳኞች ከመንግስትም ሆነ ከማናቸውም አካል ተጽዕኖ ሳይደረግባቸው እና ነጻ ሆነው ውሳኔ መስጠት የሚችሉበት ሁኔታ መኖሩ ሲረጋገጥ ብቻ ነው። ከዚህ አንጻር ዳኞች ህግና ማስረጃን ብቻ መሠረት ያደረጉ ውሳኔዎችን ከመስጠት አኳያ መሻሻሎችን በማሳየት ላይ ይገኛሉ። ሆኖም የዳኝነት ነጻነትን ለማረጋገጥ ከዳኞች፣ ከተገልጋዮች፣ ከባለድርሻ አካላትና ከሌሎች በተሰበሰቡ ስተያየቶች መሰረት ከአሠራርና አደረጃጀት አኳያ ማስተካከያዎች የሚያስፈልጉዋቸው በርካታ ክፍተቶች ታይተዋል ።
- **የአስተዳደር ሰራተኞችን ማስተዳደር፦** የዳኝነት ነጻነትን ለማስከበር የተደረጉ ጥረቶችን ተከትሎ በተሻሻለው የፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 መሰረት ፍርድ ቤቶች ዳኞችን ብቻ ሳይሆን የአስተዳደር ሰራተኞቻቸውንም የማስተዳደር ስልጣን ተሰጥቷቸዋል። ይህም የፍርድ ቤቶችን የስራ ባህሪ መሰረት ያደረገ የአስተዳደር ሥርዓት እንዲኖር ለማድረግ ከማስቻሉም በላይ ለዳኝነት ነጻነት መረጋገጥ ከፍተኛ ድርሻ ይኖረዋል። በአስፈጻሚ አካል ሥር የነበረውን የአስተዳደር ሠራተኞች ስምሪት ወደ ፍርድ ቤት ለማምጣት ያስቻለውን አዋጅ ተግባራዊ ለማድረግ የሚረዱ የሕግ ማዕቀፍ ዝግጅቶች የተጀመሩ ሲሆን የሠራተኞች አስተዳደር ደንብ ረቂቅ ዝግጅት ተጠናቅቆ በሕዝብ ተወካዮች እንዲጸድቅ ተልኳል። የሌሎች ማስፈጸሚያ መመሪያዎች ዝግጅትም ተጠናክሮ ቀጥሏል።
- **የበጀት አፈቃቀድ፦** በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 79 (6) የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፌደራል ፍርድ ቤቶች የሚተዳደሩበትን በጀት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ የማጸደቅና የተፈቀደውን በጀት የማስተዳደር ስልጣን ቢሰጠውም እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ይህን ስልጣን ተግባራዊ ሳያደርግ ቆይቷል። በዚህም የተነሳ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስፈልጋቸው በጀት በአስፈጻሚው አካል ይሁንታ ሲወሰን ቆይቶ ባለፉት ሁለት ዓመታት ለዳኝነት አገልግሎት የሚያስፈልገውን የበጀት ዕቅድ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የበጀትና ፋይናንስ ቋሚ ኮሚቴ በማቅረብ አንጻራዊ በሆነ መልኩ የተሻለ የበጀት መጠን ማስፈቀድ ተችሏል።
- **የዳኞች አሿሿም፦** ቀደም ሲል በነበረው አሰራር የዳኞች አሿሿም በአብዛኛው ግልጽነት የጎደለው፣ ከአስፈጻሚው አካል ተጽዕኖ ያልተላቀቀ፣ ሕግን ያለመከተል ችግርና ተመሳሳይ ክፍተቶች የነበሩበት መሆኑን ይህን ዕቅድ ለማዘጋጀት በተካሄደ ዳሰሳ መለየት ተችሏል። ካለፉት

ሶስት ዓመታት ወዲህ የእጩ ዳኞች ምልመላና ሹመት በሕግ የተቀመጡ ግልጽ መመዘኛዎችን እንዲከተል እና ገለልተኛ በሆኑ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተዘጋጀ የጽሁፍ ፈተና እንዲሰጥ በማድረግ ብቃትን ያገናዘበና የጾታ ተዋጽዖን ታሳቢ ያደረገ ሥርዓትን ተግባራዊ እንዲሆን ለማድረግ ያስቻሉ የማሻሻያ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡

- **የዳኞች የሥራ ዋስትና እና የስራ ሁኔታዎች፦** 60 ዓመት የነበረው የዳኞች የስራ ዘመን በተሻሻለው የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ወደ 65 ዓመት ከፍ እንዲል የተደረገ ሲሆን በጥናት ላይ የተመሰረተ የደመወዝ እና ጥቅማ ጥቅም ማስተካከያ ተደርጓል፡፡ ዘመናትን ያስቆጠረው የዳኞች መኖሪያ ሕንጻ ግንባታ በከፊል ተጠናቅቆ ግልጽ አሠራርን የተከተለ የቤቶች ድልድል በማድረግ የተወሰኑ ዳኞች ይገጥማቸው የነበረውን የመኖሪያ ቤት ችግር ማቃለል ተችሏል፡፡
- **የዳኞች ሥልጠናና ሙያዊ ልማት፦** የዳኞችን የሙያ ብቃት ለማጎልበት በየጊዜው ከሚዘጋጁ የአጭር ጊዜ ስልጠናዎችና የግንዛቤ ማጎልበቻ ውይይቶች በተጨማሪ ለመጀመሪያ ጊዜ ዳኞች እና የተወሰኑ የአስተዳደር ሠራተኞች በሥራቸው ላይ እያሉ በተለያዩ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት (ለምሳሌ በአምስተርዳም፣ በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ...) የድህረምረቃ ትምህርት መከታተል የሚችሉበትን መርኃግብር ተግባራዊ ማድረግ ተጀምሯል፡፡ የዳኝነት አገልግሎቶችን ለማሻሻል በተዘጋጁ ስልጠናዎች ዳኞች ብቻ ሳይሆኑ በ2013 በጀት ዓመት ብቻ ለአገልግሎቱ ቀጥተኛ ድጋፍ የሚያደርጉ ከ 726 ያላነሱ ረዳት ዳኞች፣ ሬጅስትራሮችና በሥራቸው የሚገኙ የችሎት አገልግሎት ሠራተኞች ከሙያቸው ጋር የተያያዙ ስልጠናዎችን እንዲወስዱ ተደርገዋል፡፡

## በዳኝነት ነጻነት እና ገለልተኝነት አተገባበር ረገድ የታዩ ክፍተቶች እና ተግዳሮቶች

የዳኝነት ነፃነት እና ገለልተኝነት ለማረጋገጥ በርካታ ተግባራት መከናወናቸውን ለማየት ቢቻልም መፍትሔ የሚያስፈልጋቸው በርካታ ተግዳሮቶች እና ክፍተቶች መኖራቸውን መገንዘብ ተችሏል፡፡ ከእነዚህ መፍትሔ ከሚሹ ጉዳዮች መካከል፡-

## በዳኝነት ነፃነት እና ገለልተኝነት መርሆች ላይ የሚታዩ የአረዳድ ችግሮች

- **የአስፈጻሚው እና የሕግ አውጪው አረዳድ፦** የዳኝነት ነጻነትን ከማረጋገጥ አኳያ የሕግ አውጪ እና አስፈጻሚ አካላት ፍላጎት መሻሻል ቢታይም አተገባበሩ በየደረጃው በሚገኙ የመንግስት አካላት ግንዛቤ ደረጃ የተወሰነ ነው፡፡ ይህም በጀትን በማስተዳደር ነጻነት፣ በውሳኔዎች አፈጻጸም፣ ለፍርድ ቤቶች የሚያስፈልጉ አገልግሎቶችን (ለምሳሌ ተገቢ ምላሽ ሳያገኝ ዓመታትን ያስቆጠረው የጠ/ፍርድ ቤት ሕንጻ ግንባታ ቦታ ጥያቄ ) እንደ አንድ የመንግሥት አካል ተቀብሎ በማስተናገድ፣ ለዳኝነት ነጻነት ተጽዕኖ የሚፈጥሩ የህግ ማዕቀፎችን (ለምሳሌ የተሻሻለው የፌዴራል የሥነ ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን አዋጅ) በማውጣት እና በመሰል ጉዳዮች ጎልቶ ይታያል፡፡
- **የኃላፊዎችና የዳኞች አረዳድ፦** የዳኝነት ነጻነት ወሰን እና አተገባበር ላይ በዳኞች መካከል

ግልጽና የጋራ አረዳድ አለመኖሩን የሚያመላክቱ ፍንጮች ይታያሉ። ለምሳሌም እልባት ባላገኙ መዛግብት አፈጻጸም ዙሪያ በየደረጃው የሚገኙ የፍርድ ቤት ፕሬዝደንቶች አስተዳደራዊ ኃላፊነት እስከምን ሊደርስ እንደሚችል በግልጽ የሚታወቅና የጋራ የተደረገ አመለካከት የለም። የዳኝነት ነጻነትን ከተጠያቂነት ጋር አያይዞ የመተግበር ክፍተቶችም ይታያሉ።

- **የይግባኝ/የክለሳ ስርዐት የሚገድቡ ህጎች፦** በሀገራችን የዳኝነት ስርአት ውስጥ ከፊል የዳኝነት ስልጣን ያላቸው በርካታ ተቋማት መኖራቸው በራሱ እንደችግር ባይቆጠርም እነዚህ ተቋማት የሚቋቋሙበት መርህ በግልፅ አለመታወቁ፣ አጠራጣሪ ስልጣን ሲኖር ፍርድ ቤቶች ሊከተሉት የሚገባ ስርአት ግልፅ አለመደረጉ፣ የተወሰኑ ቢሆኑም ሕጎች የይግባኝ/ክለሳ መብትን በሚገድቡበት ጊዜ ፍርድ ቤቶች ሊከተሉት የሚገባ የትርጉም ሥርዓት በግልጽ አለመቀመጡ.... የሚሉትና ሌሎች ተመሳሳይ ተግዳሮቶች በዳኝነት ነጻነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ በመሆናቸው ሊስተካከሉ የሚገባቸው መሆኑን መረዳት ተችሏል።

- **በቂ በጀት የማግኘት ችግሮች፦** የበጀት ነጻነትን ለማስከበር በተደረጉ ጥረቶች ካለፉት ዓመታት አንጻር የተሻለ በጀት ለማግኘት ቢቻልም ፍርድ ቤቶች ለረጅም ዓመታት ትኩረት ተነፍጓቸው በመቆየታቸው የተከማቹ ችግሮችን ለመፍታት እና የዳኝነት አገልግሎቶችን ለመስጠት የሚያስፈልጉ አቅርቦቶችን ለማሟላት የሚፈቀድላቸው በጀት በቂ ሆኖ አልተገኘም። ለዚህም የፍርድ ቤቶች የሥራ ሥፋትና ጫና በአግባቡ አለመታዎቁ፣ እንደ አንድ የመንግሥት አካል ታይተው ከአገሪቱ በጀት ሊኖራቸው የሚገባው ድርሻ ከግምት አለመግባቱ፣ የበጀት ውሳኔ ሰጪ አካላት በፍርድ ቤቶች የመፈጸም አቅም ላይ ሙሉ እምነት ማጣታቸው፣ የሚቀርቡ የበጀት ዕቅዶች የጥራትና የአሳማኝነት ችግር አለባቸው መባሉ ... በምክንያትነት ከሚነሱ ችግሮች ጥቂቶቹ ናቸው።

- **በጀትን የማስተዳደር ነጻነት ዕጥረቶች፦** ለፍርድ ቤት የሚመደበው በጀት የፕሮግራም በጀት ሥርዓትን ተከትሎ በአምስት ርዕሶች የተከፋፈለ ሲሆን የበጀት አስተዳደሩ ሙሉ በሙሉ የመንግስትን የፋይናንስ ስርዓት የተከተለ ነው። ፍርድ ቤቶች ሥራዎቻቸውን ሳይሆን ርዕሶችን ተከትሎ የተመደበውን በጀት ከአንድ የበጀት ርዕስ ወደ ሌላ የበጀት ርዕስ አዛውረው መጠቀም ቢፈልጉ የገንዘብ ሚንስቴርን ይሁንታ ለማግኘት ይገደዳሉ። ይህም በጀታቸውን በተቀላጠፈና በነጻነት እንዳይጠቀሙ የሚገድብ በመሆኑ መሰረታዊ ክፍተት ሆኖ ታይቷል። የአገሪቱን የፋይናንስና ተያያዥ ህጎች አክብረው የመስራት አስፈላጊነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ፍርድ ቤቶቹ በቀጣዮቹ የስትራቴጂክ ዘመናት የሚሰጡዋቸውን አገልግሎቶች ለማሻሻል የሚያስፈልጋቸውን በቂ በጀት ማግኘትና በራሳቸው ማስተዳደር ይኖርባቸዋል።

- **የዳኞች ደመወዝ፣ ጥቅማ ጥቅምና የስራ ሁኔታ ክፍተቶች፦** በቅርቡ በዳኞች ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም ላይ ማስተካከያ ቢደረግም በተመሳሳይ ደረጃ የሚገኙ ዳኞች ተመሳሳይ ደመወዝ ማገኘታቸው የበርካታ ዳኞች ቅሬታ መንስዔ መሆኑ ታይቷል። እንዲህ ዓይነት ቅሬታዎችን ለመፍታት የዳኞች ደመወዝ እና ጥቅማ ጥቅም የሚመራበት ራሱን የቻለና ወቅቱን ተከትሎ የሚሻሻል ፓኬጅ ማዘጋጀት የሚያስፈልግ ሲሆን በዚህ ረገድ ሊሞሉ የሚገባቸው ክፍተቶች

ትኩረት የሚፈልጉ ናቸው። የዳኞች የመኖሪያ ቤት ግንባታ በከፊል ተጠናቆ ስራ ቢጀምርም የጋራ ደህንነት ዋስትና ጥያቄ ማስነሳት ጀምሯል። ዳኞች ሥራቸውን በነፃነት እንዲያከናውኑ የሥራ ቦታዎች ከስጋት ነጻ መሆን አለባቸው። በዚህ ረገድ ሊኖሩ የሚችሉ ስጋቶችን ዓይነትና ስፋት በጥናት ለይቶ መፍትሄ እንዲበጅላቸው ማድረግ ደግሞ በስትራቴጂክ ዘመኑ ትኩረት አግኝተው መከናወን ከሚገባቸው ጉዳዮች ጋር የሚታይ ሆኖ ተገኝቷል። የአስተዳደር ሰራተኞችም በእነዚህ የደህንነት ክፍተቶች ዙሪያ የሚያነሷቸው ጥያቄዎች ለዳኝነት ነጻነቱ እንቅፋት በመሆናቸው በጥናት ተለይተው ሊፈቱ ይገባቸዋል።

- **የዳኝነት ስልጠና ሥርዓት ጉድለቶች፡-** የዳኞች ሥልጠና መመሪያ ቢኖርም አጠቃላይ የስልጠናና ሙያዊ ልማት ላይ ግልጽ የሆነ ፖሊሲ እና ዕቅድ ባለመኖሩ የዳኞች ስልጠና ዓላማ፣ ዓይነት፣ አካሄድ፣ ጊዜና የአሰልጣኞችን ማንነት በተመለከተ የሚነሱ ጥያቄዎች ሥርዓትን ተከትለው የተመለሱ አይደሉም። እነዚህን ጥያቄዎች በጥቅሉም ቢሆን የሚመልሰው አዋጅ ቁጥር 1071/2010 ቢሆንም ዳኞችን የሚያሰለጥነው ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስቴሩ የሆነው የፌደራል የፍትህና የሕግ ምርምር እና ስልጠና ኢንስቲቲዩት በመሆኑ ከአስፈጻሚው ተጽዕኖ ነፃ ነው ለማለት አይቻልም። ሆኖም በተሻሻሉ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች እና በዳኞች አስተዳደር ጉባዔ አዋጆች ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት የዳኞችን የስልጠና መመሪያ የማውጣት እና የፌደራል ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ለዳኞች ስልጠና የመስጠት ኃላፊነት የሰጣቸው በመሆኑ በዚህ የስትራቴጂክ ዕቅድ ዘመን እነዚህ ጥያቄዎች ተገቢ ምላሽ ያገኛሉ ተብሎ ይጠበቃል። ዳኞችም ሆኑ የአስተዳደር ሠራተኞች ሌሎች አጋር ድርጅቶች እና አስፈጻሚ አካላት በሚያዘጋጁዋቸው ስልጠናዎች እንዲሳተፉ ማድረግ የተለመደ መሆኑ ይታወቃል። ለዳኝነት አገልግሎት የሚያስፈልገውን አቅም ከመገንባት አንፃር በብዙ አገሮች እንደሚደረገው ፍርድ ቤቶች የራሳቸውን የዳኝነት ሥርዓት ማሰልጠኛ ተቋም በተሟላ መልኩ ማደራጀትና በሚፈልጉዋቸው ጉዳዮች ላይ ስልጠና የሚሰጡባቸውን አሠራሮች ማመቻቸት ይኖርባቸዋል።

## የዳኝነት ተጠያቂነት

ማንኛውም የመንግስት አካል ለሚያከናውነው ተግባር ተጠያቂ መሆኑን ከሚደነግገው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንጻር ዳኞች ከሕግ/ከሥነ ምግባር ድንጋጌዎች ተጻራሪ በሆነ አሠራር በሚሰጡዋቸው የዳኝነት አገልግሎቶች ተጠያቂ ይሆናሉ። ይህን የተጠያቂነት መርህ ተግባራዊ ለማድረግ ጉዳዮችን በግልጽ ችሎት የማስተናገድ፣ የተሰጡ ውሳኔዎችን ምክንያት የመግለጽ፣ በስር ፍርድ ቤት የተሰጡ ውሳኔዎችን በይግባኝ የማረም፣ የዳኝነት አገልግሎቶችን ለህዝብ ግልጽና ተደራሽ የማድረግ.... ዘዴታዎች ሊኖሩ ይገባል። የፌደራል ፍርድ ቤቶች በተለያዩ የሕጎች እና የአሠራር ማሻሻያዎች እነዚህን ዘዴታዎች ለመወጣጥ የሚያስችሉ ተግባራትን በማከናወን ላይ ይገኛሉ። ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ተጠያቂነት ሥርዓትን ለመተግበር ባከናወኑዋቸው ተግባራት ከተገኙ ውጤቶች መካከል ማሳያ የሚሆኑት እንደሚከተለው ተመልክተዋል።

## የዳኝነት ተጠያቂነትን በማረጋገጥ ረገድ ውጤት የታየባቸው እርምጃዎች

- **የአመራር ቁርጠኝነት፦** የፌደራል ፍርድ ቤቶች ተቋማዊና ግለሰባዊ ተጠያቂነትን ከዳኝነት ነፃነት ጋር አመዛዝኖ ለመተግበር የሚያስችሉ የሕግ ማዕቀፎች እንዲዘጋጁና እንዲሻሻሉ የተለያዩ ጥረቶችን በማድረግ ላይ ይገኛሉ። ለዚህም የተሻሻለው የዳኞች የሥነ ምግባርና የዲስፕሊን ደንብ እና የፍትሐብሔር ጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር መመሪያ ጸድቆ ወደ ትግበራ እንዲገባ መደረጉን፣ የዳኞች የምዘና መመሪያ ዝግጅት ተጠናቅቆ የመጨረሻ መልክ መያዙን፣ የግልጽ ችሎት ሥርዓትን ለማጠናከር በመወሰድ ላይ የሚገኙ ዕርምጃዎችን… አብነት ማድረግ ይቻላል።

- **የኢንስፔክሽን ክፍልን በአዲስ መልክ ማደራጀትና ማጠናከር፦** በችሎት የሚሰጡ አገልግሎቶችን አግባብነትና የተሰጡ ውሳኔዎችን ጥራት ተከታትሎ የማስተካከያ ምክረ ሀሳቦችን የማቅረብ ዓላማ ያለው የዳኝነት አገልግሎት ኢንስፔክሽን ክፍል በጠቅላይ ፍርድ ቤት በዳይሬክቶሬት ደረጃ በአዲስ መልክ ተደራጅቶ ወደ ሥራ ገብቷል። ዳይሬክቶሬቱ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችል የሰው ኃይል ባይሟላለትም በ2013 ዓ.ም ብቻ ከቀረቡት 282 የቃል እና 245 የጽሁፍ በአጠቃላይ 527 የዳኝነት አገልግሎት አቤቱታዎች/ቅሬታዎች ውስጥ 526 ቅሬታዎች በተለያዩ አካላት መፍትሄ እንዲያገኙ አደርጓል። በከፍተኛ እና በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም በጊዜያዊነት የተመደቡ ባለሙያዎችን የያዘ የዳኝነት ኢንስፔክሽን ክፍል የተደራጀ ሲሆን ከተገልጋይ የሚቀርቡ አቤቱታዎች በመስተናገድ ላይ ይገኛሉ።

- **የአቤቱታ ማቅረቢያ ሥነ ሥርዓት፦** በኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት ከሚስተናገዱ ቅሬታዎች/ አቤቱታዎች በተጨማሪ በሬጅስትራሮች የተሰጡ አገልግሎቶችን አስመልክቶ ተገልጋዮች ሀሳባቸውን የሚገልጹባቸው ሳጥኖች እና ደብተሮች ተዘጋጅተው አስተያየቶችን መሰረት ያደረጉ ማስተካከያዎች በመደረግ ላይ ይገኛሉ። ለዚህም በሶስቱም ፍርድ ቤቶች በተዘጋጁ የአስተያየት ማሰባሰቢያ ሳጥኖች/ደብተሮች የተሰጡ አስተያየቶችን በግብዓትነት ተጠቅሞ የተወሰዱ የማስተካከያ ዕርምጃዎችን መመልከት ይቻላል። ከእነዚህ ጥረቶች ባሻገር ዳኞች በሚሰጡዋቸው አገልግሎቶች ዙሪያ ከተገልጋይ የሚቀርቡ የሥነ ምግባርና የዲስፕሊን ጥሰቶችን አስመልክቶ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን መርምሮ ውሳኔ ለመስጠት ቀደም ሲል የተጀመረውንና በመጠናከር ላይ የሚገኘውን የዳኝነት ቅሬታ ማስተናገጃ ሥርዓት ማሳያ ማድረግ ይቻላል። የተሻሻለው የፌዴራል ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ አዋጅ ቁጥር 1233/2013 ይህን ሥርዓት በማጠናከር የዳኞች አስተዳር ጉባዔ በዳኞች ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን እየመረመረ የዲሲፕሊን እርምጃ የመውሰዱ ስልጣን ከመስጡም ሌላ ቅሬታ ወይም አቤቱታ የቀረበበት ዳኛ የመሰማት እና የይግባኝ መብት እንዲኖረው አድርጎታል። በዚህ መሰረት ካለፈው በጀት ዓመት የተሻገሩና በ2013 በጀት ዓመት አዲስ ተከፍተው ከቀረቡ 111 አቤቱታዎች የ77 ዳኞች ጉዳዮች ተጣርተው በጉባዔው ውሳኔ እንዲሰጥባቸው ተደርጓል።

- **የአስተዳደር ሰራተኞች ተጠያቂነት፦** በሶስቱም ፍርድ ቤቶች የሥነ ምግባር መከታተያ ክፍሎች ተደራጅተው በሰው ሀይልና በግብዓት በማሟላት ላይ ሲሆኑ በተለይ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/

ቤት የሠራተኞች የሥነ ምግባር ደንብ ታትሞና ተሰራጭቶ ተግባራዊ በመደረግ ላይ ይገኛል። ሙስናን ለመከላከል በሶስቱም ፍርድ ቤቶች የበላይ አመራሮች፣ ዳኞች፣ በየደረጃው የሚገኙ የሥራ ክፍል ኃላፊዎችና ሠራተኞች አዲስ የሃብት ምዝገባና እድሳት ተካሂዷል። አስተዳደራዊ ችግሮችን ለመከላከል የሚያስችሉ የእርምት እርምጃዎችንም አጠናክሮ በመቀጠል ከሶስቱም ፍርድ ቤቶች ከቀረቡ 33 የዲስፕሊንና የፍትሐብሔር ክሶች አስሩ ውሳኔ እንዲያገኙ ተደርጓል።

- ***የብዙኃን መገናኛዎች አጠቃቀም፦*** የፍርድ ቤት ማህበራዊ ሚዲያና ድረገጽ መጠቀምን ጨምሮ ፍርድ ቤቶቹ ከብዙኃን መገናኛ ዘርፎች ጋር በጋራ መስራት በመጀመራቸው ሥራዎቻቸውን በተሻለ መልኩ ለሕዝብ ግልጽ በማድረግና መረጃዎችን በማሰራጨት ረገድ መሻሻሎችን አሳይተዋል።

- ***የበጀት/ፋይናንስ አፈጻጸም ሪፖርት፦*** የተሻሻለው የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለፌደራል ፍርድ ቤቶች የተፈቀደውን በጀት አጠቃቀም አስመልክቶ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሪፖርት የሚያቀርቡ መሆኑን መደንገጉ የሕዝብ ተጠያቂነቱን ያጠናክራል ተብሎ ይታመናል።

## የዳኝነት ተጠያቂነትን በመተግበር ረገድ የታዩ ክፍተቶችና ተግዳሮቶች

ሕግን መሰረት ያደረገ የተጠያቂነት ስርአትን ለመዘርጋት የተጀመሩ ጥረቶች አበረታች ቢሆንም የሚፈለጉ ውጤቶችን ለማግኘት ክፍተቶች ተለይተው መሞላት ይኖርባቸዋል። የተጠያቂነት ሥርዓትን ለመተግበር በዋናነት ከታዩ ክፍተቶች መካከል፡-

- ***የበጀትና አጠቃቀም ውጤታማነት ግምገማ፦*** ፍርድ ቤቶች የበጀት አጠቃቀማቸውን የሚገልጽ ሪፖርት ቀደም ሲል ለገንዘብ ሚኒስቴር፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚያቀርቡበት ሥርዓት ቢኖርም የበጀት ዕቅድንም ሆነ አፈጻጸምን ለውጪ አካላት አቅርቦ ግምገማን ማካሄድ እና ለተገኙ ግብረ-መልሶች ተግባራዊ ምላሽ መስጠት የተለመደ አለመሆኑ ተጠያቂነትን ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ ሌላው ክፍተት ተደርጎ ተወስዷል።

- ***የፍርድ ቤቶች እና የመገናኛ ብዙኃን ግንኙነቶች፦*** በፍርድ ቤቶች ውስጥ የኮሙኒኬሽን ስትራቴጂ በማዘጋጀት፣ ከመገናኛ ብዙኃን ጋር የሚኖርን ግንኙነት የሚመራ መመሪያ በማውጣት፣ የፍርድ ቤት ጉዳዮችን በሚዲያ በማስተላለፍና በሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች ዙሪያ ክፍተቶች ታይተዋል። የሚዲያ አጠቃቀምን በተመለከተ ግልፅ ስትራቴጂ እና አሰራር ባለመኖሩ የፍርድ ቤቶች እና የመገናኛ ብዙኃን ግንኙነቶችን፣ የፍርድ ቤት መረጃዎች ለሕዝብ የሚደርሱባቸው አሠራሮችን፣ ፌስቡክን ጨምሮ የማህበራዊ ሚዲያና የድረ-ገጽ አጠቃቀም ፖሊሲዎችን የሚያመላክቱ ሰነዶችን ማግኘት አልተቻለም። እነዚህ ሥርዓቶች ባልተጠናከሩበት ሁኔታ ሕብረተሰቡ ስለ ፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማዎቅ የሚገባቸውን መረጃዎች ለማድረስ አዳጋች በመሆኑ ክፍተቱን ሊሞሉ የሚገባቸው ስትራቴጂዎች የዕቅዱ አካል እንዲሆኑ ተደርገዋል።

- ***የአፈጻጸም ምዘና ክፍተቶች፦*** የዳኞችን አፈጻጸም ጥራትና ቅልጥፍና ለመመዘን የሚያግዙና የጉዳዮችን ባህሪ መሰረት ያደረጉ ስታንደርዶች ተዘጋጅተው ቅልጥፍናን በመለካት ላይ

ያተኮሩ ክትትሎች ሲደረጉ ቢቆዩም የጥራት ደረጃዎችን መለካት አዳጋች በመሆኑ የምዘና ሥርዓቱን ተግባራዊ ማድረግ አለመቻሉን መረዳት ተችሏል፡፡ ክፍተቱን ለመሙላት በአዲስ መልክ የተዘጋጀው የዳኞች አፈጻጸም ምዘና መመሪያ የጥራት መስፈርቶችን በተሻለ መልኩ ቢያካትትም በሚመለከተው አካል ባለመጽደቁ ተግባራዊ አልተደረገም፡፡ ለምዘና በሚያስፈልጉ የመረጃ ምንጮችም ተመሳሳይ ክፍተቶች ታይተዋል፡፡ ከተገልጋይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን በማስተናገድና የችሎት ቅኝቶችን በማካሄድ ለዳኝነት ጥራት መሻሻል የሚያግዙ መረጃዎችን እንዲያዘጋጅ በአዲስ መልክ በተደራጀው የኢንስፔክሽን ክፍል የተጀመሩ ተግባራት ቢኖሩም የድህረ ዳኝነት/ውሳኔ ኦዲት በተሟላ መልኩ ባለመካሄድ (post-judgment audit) ችግሮችን ለይቶ ማስተካከያዎችን ለማድረግ ያስቻሉ መረጃዎችን ማግኘት አልተቻለም፡፡

- **የኢንስፔክሽን ክፍል፦** የኢንስፔክሽን ክፍል በተሻለ ሁኔታ ማደራጀት እና አሰራሩን ማጠናከር የዳኝነት ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ ከሚያስፈልጉ አሰራሮች አንዱ ነው፡፡ ክፍሉ በጠቅላይ ፍርድ ቤት በዳይሬክቶሬት ደረጃ የተደራጀ ቢሆንም ኃላፊነቱን በሚገባ መወጣት በሚያስችለው ደረጃ ጠንካራ አሰራር አለማዳበሩና በበቂ የሰው ኃይል አለመደራጀቱ ክፍተት ሲሆን በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና በከፍተኛ ፍርድ ቤት በኩልም ስራውን የሚሰራው በተወካይ (focal person) ባለሙያ አማካኝነት መሆኑ የስራ ክፍሉን እንዳይጠናከር ያደርገዋል፡፡ እንዲሁም በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተወካይ የተመደበው በልደታ ምድብ ችሎት ብቻ ነው፤ በመሆኑም ከስራው ክብደት እና አስፈላጊነት አንጻር ተገቢው ትኩረት አለማግኘቱ እንደ ክፍተት የሚወሰድ ነው፡፡
- **የፌደራል ፍርድ ቤቶች የዲሲፕሊን ደንብ እና አተገባበር፦** ሙስናን እና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል በቂ ትኩረት የተሰጣቸው የውይይት መርሐ-ግብሮች በተሟላ እና ቀጣይነት ባለው መልኩ አለመኖራቸው፣ በዳኞች አስተዳደር ጉባዔ የሚታዩ ጉዳዮች ረጅም ጊዜ መውሰዳቸው፣ ሕብረተሰቡ በፍርድ ቤቶች ላይ ሙስናን ጨምሮ በርካታ ቅሬታዎችን ማሰማቱ፣በዲሲፕሊን የሚታዩ ጉዳዮች መራዘማቸው፣ የተሻሻለ የዲሲፕሊን ደንብ ቢኖርም ለውሳኔ ሰጪዎች ሰፊ ስልጣን መስጠቱ ተጠያቂነትን ተግባራዊ ለማድረግ በስጋትነት የሚታዩ ክፍተቶች ሆነው ተገኝተዋል፡፡
- **የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ አሰራር፦** ጉባኤው በፍርድ ቤቶች አሠራር ላይ መሰረታዊ ለውጥ በሚያመጡ ጉዳዮች ላይ አትኩሮ አለመሥራቱ፣ ከዳኞችና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎችም ሆነ ባለሙያዎች ጋር የሚታወቅ ሥርዓትን የተከተለ መደበኛ ውይይት አለማካሄዱ፣ በዲሲፕሊን አቤቱታ የሚቀርቡ ጉዳዮችን አስመልክቶ የጉባኤው አባላት እኩል ግንዛቤ አለመያዛቸው ክፍተት ሆነው ከታዩ ጉዳዮች ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

## 1.2.2. የዳኝነት አገልግሎት ቅልጥፍና እና ጥራት

### 1.2.2.1. የዳኝነት ቅልጥፍና

ፍርድ ወይም ውሳኔ በተገቢው አጭር ጊዜ ውስጥ ማግኘት (speedy trial) ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ጉዳይ መሆኑ በሕገ መንግስት የተረጋገጠ መብት ነው። ለፍርድ ቤት ከቀረቡ ጉዳዮች ዕልባት የሚያገኙት መጠን እየጨመረ መምጣቱን የሚያመላክቱ መረጃዎች ቢኖሩም በርካታ ጉዳዮች በቀጠሮ የሚሸጋገሩበት ሁኔታ በመኖሩ ችግሩን ለይቶ መፍትሔ በመስጠት የዳኝነት ቅልጥፍና ማሳደግ የሚያስችሉ ዕርምጃዎችን መውሰድ በስትራቴጂክ ዘመኑ ሊተኮርበት የሚገባው ጉዳይ ሆኖ ተገኝቷል። ቅልጥፍናን ለማሻሻል በተግዳሮትነት ከሚጠቀሱ ጉዳዮች መካከል ያለበቂ ምክንያት ተደጋጋሚ ቀጠሮዎችን መስጠት፣ በዚህም የተነሳ ጉዳዮች በተገቢው አጭር ጊዜ ውሳኔ አለማግኘት፣ በተሰጡ ፍርዶች አፈጻጸም ዙሪያ በርካታ ችግሮች መከሰት የሚሉትን ለመጥቀስ ይቻላል። የፌደራል ፍርድ ቤቶች ቅልጥፍናን ለማሳደግ ባደረጉዋቸው ጥረቶች የመዛግብትን አፈጻጸም ማሳደግ ከመቻሉም ሌላ የዳኝነት ቅልጥፍናን ለማሳደግ የተዘረጋውን የሕግ ዕውቅና የተሰጠው የጉዳዮች ፍሰት አመራር ሥርዓት ጨምሮ በተጀመሩ ዘርፈ ብዙ የማሻሻያ ሥራዎች ከፍተኛ ለውጦች በመታየት ላይ ይገኛሉ። ለዚህም የጸደቁ አዋጆችን ጨምሮ የተለያዩ የህግ ማዕቀፍ ዝግጅቶችን፣ አዋጆችን ተከትሎ በአስተዳደር ሠራተኞች ሥምሪት የተጀመሩ ለውጦችን፣ የበጀት ነጻነትን ለማስከበር የተገኙ ውጤቶችን፣ ለዳኝነት ሥራ አጋዥ ከሆኑ ባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶና ተባብሮ በመሥራት የተገኙ የማሻሻያ ሥራ ድጋፎችን ማሳያ ማድረግ ይቻላል።

ጉዳዮችን በተገቢው አጭር ጊዜ ለማጠናቀቅ በተደረጉ ጥረቶች ዕልባት የሚያገኙ መዛግብትን መጠን ለመጨመር፣ የማጥራት ምጣኔን ለማሳደግና ውዝፍ መዛግብትን ለመቀነስ የተቻለባቸው ውጤቶች የተገኙ ሲሆን ባለፈው ስትራቴጂክ ዘመን (2008 እስከ 2012) የነበሩ የመዛግብት አፈጻጸምሞችን ከሚከተሉት መረጃዎች ለማየት ይቻላል።

#### ከ2008 እስከ 2012 ዕልባት ያገኙ መዛግብት እና የማጥራት ምጣኔ

ከ2008-2012 ዓ.ም በነበሩ ዓመታት ከየበጀት ዓመቱ ተሻግረው፣ አዲስ እና እንደገና ተከፍተው ለችሎቶች የቀረቡ መዛግብት መጠን በጠቅላይ እና ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች የጎላ ለውጥ ባይታይባቸውም በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በ2012 ዓ.ም የቀረቡት በ2008 ዓ.ም ከቀረቡት መዛግብት በከፍተኛ መጠን ቀንሰው ታይተዋል። ከ2008 ዓ.ም እስከ 2010 ዓ.ም የነበረው የመዛግብት አቀራረብ አጠቃለይ ሁኔታ ወጥነት ባለው ሁኔታ የመጨመር አዝማሚያ የታየበት ሲሆን በ2012 ዓ.ም የቀረቡት መዝገቦች በኮቪድ ወረርሽኝ ምክንያት በ2011 ዓ.ም ከቀረቡት በከፍተኛ መጠን ቀንሰው ታይተዋል። የእነዚህ መዛግብት አፈጻጸም እስከ 2011 በጀት ዓመት በሁሉም ፍርድ ቤቶች በሚባል ደረጃ ተከታታይነት ያለው ዕድገት የታየበት ሲሆን በ2012 ዓ.ም ዕልባት ያገኙ መዛግብት ቀንሰዋል። (ዝርዝሩን ከሚከተሉት ሰንጠረዦች ይመልከቱ)

## ከ2008 እስከ 2012 ዕልባት ያገኙ መዛግብት መጠን በየደረጃው ባሉ የፌደራል ፍርድ ቤቶች

| ፍርድ ቤቶች | 2008 | | 2009 | | 2010 | | 2011 | | 2012 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ውዝፍ መዝገቦችን ጨምሮ አጠቃላይ የቀረቡ | ዕልባት ያገኙ | ውዝፍ መዝገቦችን ጨምሮ አጠቃላይ የቀረቡ | ዕልባት ያገኙ | ውዝፍ መዝገቦችን ጨምሮ አጠቃላይ የቀረቡ | ዕልባት ያገኙ | ውዝፍ መዝገቦችን ጨምሮ አጠቃላይ የቀረቡ | ዕልባት ያገኙ | ውዝፍ መዝገቦችን ጨምሮ አጠቃላይ የቀረቡ | ዕልባት ያገኙ |
| ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት | 19,185 | 12,716 | 20,831 | 16,829 | 20,521 | 17,698 | 22,375 | 16,238 | 18,928 | 15,576 |
| ፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት | 32,524 | 17,790 | 33,071 | 19,361 | 36,761 | 21,195 | 40,732 | 26,233 | 32,417 | 17,049 |
| ፌደራል መጀመሪያ ፍርድ ቤት | 218,662 | 133,125 | 199,814 | 143,553 | 179867 | 151,978 | 188,091 | 161,759 | 128,132 | 100,834 |
| የሶስቱም ፍርድ ቤቶች | 270,371 | 163,631 | 253,716 | 179,743 | 237,149 | 190,871 | 251,198 | 204,230 | 179,477 | 133,459 |

ምንጭ፦ የፌደራል ፍርድ ቤቶች ሪፖርት (2008 - 2012 ዓ.ም)

## ዕልባት ያገኙ መዛግብት የቆይታ ጊዜ

ዕልባት ያገኙ መዛግብት የቆይታ ጊዜ ለየፍርድ ቤቶች እንደሚቀርቡ ጉዳዮች ባህሪ ቢለያይም በአብዛኛው ከ1-3 ዓመት ቆይታ የነበራቸው መሆኑን መረዳት ተችሏል። ለምሳሌ የ2013 በጀት ዓመት የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሪፖርት  እንደሚያመለክተው በበጀት ዓመቱ ዕልባት ካገኙ መዛግብት ውስጥ በጠቅላይ ፍርድ ቤት እስከ ሶስት ዓመት ቆይታ የነበራቸው 1,295፣ በከፍተኛ ፍርድ ቤት 5,154 እና በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት 3,862 ሲሆኑ በከፍተኛ እና በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከሶስት እስከ ስድስት ዓመት ቆይተው እልባት ያገኙ መዝገቦች እንደቅደም ተከተላቸው 256 እና 725 ናቸው። ይህም በ2008 ዓ.ም ከሶስት እስከ ስድስት ዓመት ቆይተው እልባት ያገኙት በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት 522 እንዲሁም በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት 1,588 መዝገቦች ከመሆናቸው አንጻር መሻሻል ታይቷል። በሪፖርት ዘመኑ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ደረጃ ከሶስት ዓመት በላይ መዛግብት ባይኖሩም በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት 307 እና በከፍተኛ ፍርድ ቤት 15 መዝገቦች ከስድስት ዓመታት በላይ ቆይታ የነበራቸው መሆኑን ከርፖርቱ መረዳት ተችሏል።

### በ2013 በጀት ዓመት ዕልባት ያገኙ መዛግብት ቆይታ ጊዜ




ምንጭ፦ የፌደራል ፍርድ ቤት የ2013 የዘጠኝ ወር አፈጻጸም ሪፖርት

ውዝፍ መዛግብትን ሳጨምር በየበጀት ዓመቱ አዲስና እንደገና ተከፍተው ለችሎቶች ከቀረቡ መዛግብት ዕልባት ያገኙት እየጨመሩ በመምጣታቸው ያለፈውን ስትራቴጂክ ዘመን የፍርድ ቤቶች የማጥራት አቅም እስከ እስከ 2011 ዓ.ም  አሳድጎታል። ለምሳሌ የፌደራል ፍርድ ቤቶች የ2012 ዓ.ም ሪፖርት እንደሚያሳየው ከሐምሌ 01 - ሰኔ 30 ቀን 2012 ዓ.ም አዲስና እንደገና ተከፍተው ለችሎት የቀረቡ መዛግብት የማጥራት ምጣኔ በበጀት ዓመቱ 98.27% የነበረ ሲሆን በ2008 (94.6%) ከነበረው በመጨመሩ ባለፉት አራት ዓመታት እያደገ መምጣቱን ያመለክታል። በ2012 ዓ.ም ግን የቀረቡትም ሆነ ዕልባት ያገኙ መዛግብት በመቀነሳቸው የማጥራት አቅምም ዝቅ ብሎ ታይቷል። (ዝርዝሩን ከሚከተለው ግራፍ ይመልከቱ)

## ከ2008-2012 ዓ.ም ያለው የፌደራል ፍርድ ቤቶች የማጥራት ምጣኔ




ምንጭ፦ የፌደራል ፍርድ ቤቶች ሪፖርት (ከ2008 – 2012 ዓ.ም)

## ተሻጋሪ መዛግብት እና የክምችት ምጣኔ ከ2008 እስከ 2012

በሁሉም ፍርድ ቤቶች ከ2008-2010 ዓ.ም ባለው ጊዜ በየዓመቱ ተሻጋሪ መዝገቦች የመቀነስ አዝማሚያ የታየባቸው ቢሆንም ከ2011 ዓ.ም በኋላ በከፍተኛና መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች ጨምረውና በጠቅላይ ፍርድ ቤት ቀንሰው ታይተዋል። ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሚቀርቡ ጉዳዮች ሰፋፊና ውስብስብ በመሆናቸው ከቀረቡት መዝገቦች ውስጥ ከግማሽ ያላነሱት ከዓመት ወደ ዓመት ይሸጋገራሉ። ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሚቀርቡ ጉዳዮች ከሌሎች አንጻር ብዛት ያላቸው መሆኑ ቢታወቅም በ2012 በጀት ዓመት ለችሎት የቀረቡትም ሆነ የተሻገሩት መዛግብት ቀንሰዋል። ተሻጋሪ መዛግብትን ተከትሎ የየፍርድ ቤቶቹ የመዝገብ ክምችት ምጣኔ በየዓመቱ መቀነስንና መጨመርን እንጂ ወጥነት ያለው መቀነስን አያሳይም። የከፍተኛ ፍርድ ቤት የመዝገብ ክምችት ምጣኔ ከ2008 ዓ.ም እስከ 2011 ዓ.ም እየቀነሰ ይመጣ እንጂ የአምስት አመት የክምችት ምጣኔው ከ0.5 በላይ ከፍ ብሏል፣ በተለይ በ2012 ዓ.ም የነበረው የክምችት ምጣኔ በ2011 ዓ.ም ከነበረው በ40% ጨምሯል። በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከ2009 እስከ 2011 ዓ.ም በተሻለ ሁኔታ የቀነሰ የክምችት ምጣኔ ታይቷል። ሆኖም በ2012 ዓ.ም. በተከሰተው የኮቪድ ወረርሽኝ ፍርድ ቤቶች ለስድት ወራት ከፊል አገልግሎት ሲሰጡ በመቆየታቸው የክምችት ምጣኔ በ2008 ዓ.ም ከነበረው የ2% ጭማሪ አሳይቷል። የጠቅላይ ፍርድ ቤት የክምችት ምጣኔ በተለያዩ ዓመታት መቀነስና መጨመር የሚታይበት ሲሆን የ2012 ዓ.ም የክምችት ምጣኔ በ2008 ዓ.ም ከነበረው በ29% ቀንሷል።

## በቀጠሮ የሚተላለፉ ጉዳዮች ብዛት ከ2008 እስከ 2012




## የፌደራል ፍርድ ቤቶች የመዝገቦች ክምችት ምጣኔ ከ2008 እስከ 2012 ዓ.ም




ምንጭ፦ የፌደራል ፍርድ ቤቶች ሪፖርት (ከ2008 – 2012 ዓ.ም)

## ቅልጥፍናን ለማሳደግ በተደረጉ ጥረቶች የተገኙ ውጤቶች

- የፌራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት አገልግሎት ቅልጥፍናን ለማሳደግ ባደረጉዋቸው ጥረቶች የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር እና የፍርድ ቤት መር አስማሚነት ሥርዓት በሕግ እውቅና እንዲያገኝ ከመደረጉም ሌላ እነዚህን ሥርዓቶች በባለቤትነት የሚፈጸሙ የሥራ ክፍሎችን ለማደራጀትና በጥናት ላይ የተመሰረቱ የአፈጻጸም መመሪያዎች ተዘጋጅተው እንዲተገበሩ

ለማድረግ ያስቻሉ እርምጃዎች ተወስደዋል፡፡ በቅርቡ ይጸድቃል ተብሎ የሚጠበቀው የዳኞች ምዘና መመሪያ ቅልጥፍናን ለማሳደግ ከፍተኛ ድርሻ የሚኖረው ሲሆን ባለፉት ሶስት ዓመታት ተጨማሪ ዳኞች፣ ሬጅስትራሮች፣ ተከላካይ ጠበቆችና ረዳት ዳኞች እንዲሾሙ እና የአስተዳደር ሰራተኞች ቁጥር እንዲጨምር መደረጉ የዳኝነት ቅልጥፍናን ለማሳደግ ከፍተኛ አስተዋፅዖ የሚያበረክቱ ውጤቶች ሆነው ታይተዋል፡፡

- **ውዝፍ መዝገቦችን ማጥራት፦** ውዝፍ መዛግብትን ለማጥራት ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ሲሆን መደበኛ ችሎት በማይኖርበት የክረምት ወቅት ዳኞች የዕረፍት ጊዜያቸውን መስዋዕት አድርገው በመስራት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው መዛግብት ዕልባት እንዲያገኙ ለማድረግ ያስቻሉ እርምጃዎችም ተወስደዋል፡፡ በዚህ ጥረት በ2012 ዓ.ም በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት 3,205 መዝገቦች እና በከፍተኛ ፍርድ ቤት 16,285 መዝገቦች እልባት አግኝተዋል፡፡

## ቅልጥፍናን ለማሳደግ የታዩ ተግዳሮቶች

ቅልጥፍናን ለማሳደግ በተደረጉ ጥረቶች በርካታ ውጤቶች ቢገኙም መፍትሔ የሚያስፈልጋቸው ተግዳሮቶች መኖራቸውን በተካሄደው የዳሰሳ ጥናት መለየት ተችሏል፡፡ ከእነዚህ በስትራቴጂክ ዘመኑ መፍትሔ ሊዘጋጅላቸው ከሚገቡ ተግዳሮቶች መካከል፡-

- **የተገቢው አጭር ጊዜ መለኪያ፦** የዳኝነት ቅልጥፍናን ለመለካት ቀደም ሲል የተዘጋጀውን ስታንደርድ እና በጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር የተዘረጋውን ሥርዓት ጨምሮ የተለያዩ መስፈርቶች ቢዘጋጁም በየደረጃው የሚገኙ ጉዳዮች በተገቢው አጭር ጊዜ ተጠናቀዋል ለማለት የማጥራት አቅምና የውዝፍ ምጣኔ ደረጃንም ሆነ የወጪ መጠን ለይቶ መለካት የሚያስችሉ መስፈርቶች አልታዩም፡፡ እነዚህ መለኪያዎች ባልተሟሉበት ሁኔታ አንድን ጉዳይ በተገቢው አጭር ጊዜ ተጠናቅቆ ቅልጥፍናን መጨመር ተችሏል ማለት ያዳግታል፡፡ የሚቀርቡም ሆነ ዕልባት የሚያገኙ ጉዳዮች በየበጀት ዓመቱ በምን ያህል መጠን እንደሚጨምሩ/እንደሚቀንሱ እና ለልዩነቶቹ ምክንያቶችን መለየት የሚያስችል ጥናት ተካሂዶ በግልጽ የሚታወቅ መረጃ አለመዘጋጀቱም በስትራቴጂክ ዘመኑ ሊሞላ የሚገባው ክፍተት ሆኖ ታይቷል፡፡

- **የአንድ መስኮት አገልግሎት አለመዳበሩ፦** በሁሉም ፍርድ ቤቶች ደረጃ የአንድ መስኮት አገልግሎት ሥርዓት ለመጀመር ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሬጅስትራሮች እንዲሾሙ ቢደረግም ከተወሰኑ ምድብ ችሎቶች በስተቀር ስርዓቱ ሲተገበር አይታይም፡፡ እንዲህ ዓይነቱ አሠራር ባለጉዳዮች በቀላሉ ፋይል ተከፍቶ ለችሎት እንዲቀርብላቸው እና በችሎት የተሰጡ ብይን/ትዕዛዝ/ውሳኔ ግልባጮችን ማግኘት እንዲችሉ ከማድረጉም ሌላ የሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎችን የተከተሉ መዛግብት ተከፍተው ለችሎቶች እንዲቀርቡ ማድረግ በማስቻሉ የዳኝነት ቅልጥፍናን ለማሳደግ በታቀዱ ግቦች ሊካተት ይገባል፡፡

- **የሰው ኃይል፣ የችሎት አዳራሽ፣ የቁሳቁስ አቅርቦቶች እና የመዛግብት አያያዝ በበቂ ሁኔታ አለመሟላት፦** የተሻሻለው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይታዩ

የነበሩ የተወሰኑ ጉዳዮችን ለከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች እንዲሰጡ በማድረጉ በየደረጃው የሚቀርቡ ጉዳዮችን ፍሰት በተወሰነ ደረጃ ይቀንሳል ተብሎ ቢጠበቅም የዳኞችና መዛግብት ጥምርታ መለየት የሚያስችል ሥርዓት ባለመኖሩ በየበጀት ዓመቱ የሚቀርቡ መዛግብትን ለማስተናገድ አዳዲስ ዳኞችን የመሾም መፍትሔ ተግባራዊ ሲደረግ ቆይቷል። የዳኞች ቁጥር መጨመር ለዳኝነት ቅልጥፍና ማደግ አንዱ መፍትሔ ለመሆን ቢችልም በሥራ ላይ የሚገኙ ዳኞችን ትጋትና ውጤታማነት የሚያጎለብቱና በጥናት ላይ የተመሰረቱ ሌሎች ተጨማሪ ሥርዓቶች ባልተዘረጉበት ሁኔታ ቅልጥፍናን መጨመርም ሆነ ውዝፍ መዛግብትን መቀነስ አዳጋች ይሆናል። ከዚህም በላይ የዳኞች ኮምፒዩተር ተጠቃሚነት ውስን በመሆኑና ረዳት ዳኞችን በአግባቡ የማይጠቀሙ ዳኞች በመኖራቸው ማሻሻያ ለማድረግ የሚያስችሉ ተግባራት በዕቅዱ ተገቢውን ትኩረት አግኝተዋል።

- የችሎት አዳራሾች እጥረት ዳኞች በፈረቃ እንዲያስችሉ የሚያስገድዱ አሠራሮችን በማስከተሉ ለጉዳዮች መጓተት ዓይነተኛ ምክንያት ከመሆኑም ሌላ አብዛኛዎቹ የችሎት አዳራሾች የሚያስፈልጉዋቸው ቁሳቁሶች ለምሳሌ መቅረጸ-ድምጽ፣ ድምጽን ወደ ጽሑፍ የሚቀይር ቴክኖሎጂና ሌሎች በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፉ አቅርቦቶች የተሟሉላቸው አለመሆናቸው ለቅልጥፍና ዕድገት ከፍተኛ እንቅፋት ፈጥረዋል። ይህም በዕቅድ ዘመኑ ችሎቶችን ለማዘመን የተጀመሩ ፕሮጀክቶች ተጠናክረው እንዲቀጥሉና ውጤት እንዲያስገኙ ማድረግ የሚያስችሉ ተግባራትን የዕቅዱ አካል እንዲሆኑ ማድረግ ማስፈለጉን አመላክቷል።
- የፍርድ ቤት ውጤት የሆኑና ዘመን ተሻጋሪ መዛግብት በአግባቡ ተደራጅተው እንዲያዙ ለማድረግ የተጀመሩ ጥረቶች ቢኖሩም አልፎ አልፎ የሚከሰቱ የመዛግብት መጥፋት፣ ሥርዓትን ባልተከተለ አደራደር ምክንያት በቀላሉ ማግኘት አለመቻልና ግልባጭ ለመውሰድ ረጅም ጊዜ መጠበቅ ለተገልጋዮች እንግልትና በተለይም ለታራሚዎች በማረሚያ ቤት መቆየት ምክንያት ሆነው ይታያሉ። እንዲህ ዓይነት ችግሮችን ለመፍታት ተዓማኒነት ያለው የመረጃ ቋት ማደራጀትና ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓቱን አጠናክሮ መቀጠል የሚያስችሉ ተግባራት በዕቅዱ እንዲካተቱ ተደርገዋል።

- **ምክንያታዊ ያልሆኑ ተደጋጋሚ ቀጠሮዎች፦** የዕረፍት ጊዜያቸውን መስዋዕት አድርገውና መዝገቦችን ወደቤታቸው ወስደው የሚሠሩ ዳኞች የመኖራቸውን ያህል ምክንያታዊ ያልሆኑ ተደጋጋሚ ቀጠሮዎች የሚሰጡ ዳኞች መኖራውንም ከዳኞች ጋር በተደረጉ ውይይቶች መረዳት ተችሏል። ለምሳሌ ከ1/7/2013 እስከ 30/9/2013 በጠቅላይ ፍርድ ቤት ችሎቶች በአጠቃላይ 14,979 ቀጠሮዎች የተሰጡ ሲሆኑ 73% የሚሆኑት ለምርመራ የተሰጡ ቀጠሮዎች ናቸው። በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሁለት ምድብ ችሎቶች (በቦሌ እና በአቃቂ ምድብ ችሎቶች) ከ1/1/2013 እስከ 4/10/2013 በአጠቃላይ 87,736 ቀጠሮዎች የተሰጡ ሲሆኑ 18,912 (21.5%) ለምርመራ እና 24,551 (27.9%) የትዕዛዝ ውጤት ለመጠባበቅ መቀጠራቸውን ከፍርድ ቤቶቹ የተገኙ መረጃዎች ያመለክታሉ። ለዚህም የተለያዩ ምክንያቶች የተነሱ ሲሆን በዋናነት የዳኞች ማበረታቻ እና

ተጠያቂነት ሥርዓት በተገቢው መንገድ አለመተግበሩ፣ ለችግሩ ምክንያት የሆኑ ጉዳዮችን ለይቶ ለማስተካከል የሚያስችል ጥናት አለመካሄድና ግኝቶችን መሰረት ያደረጉ እርምጃዎች አለመውሰዳቸው፣ የዳኞችና መዛግብት ጥምርታ አለመመጣጠን... የሚሉት ይጠቀሳሉ። በስትራቴጂክ ዕቅዱ ዘመን እነዚህን ችግሮች ለማቃለል የሚያስችሉ ስትራቴጂዎች በመቀረጻቸው መፍትሔዎችን ያስገኛሉ ተብሎ ይጠበቃል። በመሆኑም በየደረጃው በሚገኙ ፍርድ ቤቶች ለሚሰጡ ቀጠሮዎች መደጋገም ምክንያት የሆኑ ጉዳዮችን ለይቶ መፍትሔ መስጠትና የዳኞችን ትጋትና ውጤታማነት ሊጨምሩ የሚችሉ ሥርዓቶችን ዘርግቶ መተግበር ጠቃሚ ይሆናል።

### በየፍርድ ቤቶቹ መረጃ ቋት የተገኙ የቀጠሮ ድግግሞሽና ምክንያቶች




- **ለዳኝነት ቅልጥፍና በሌሎች ባለድርሻ አካላት የሚፈጠሩ ችግሮች፦** በፍትሐብሄር ጉዳዮች ላይ በጠበቃ ያልተወከሉ ተከሳሾች እና ጠበቆች የሚጠይቁዋቸው ተደጋጋሚ የዝግጅት ጊዜ ፈቃዶች፣ የምስክሮች በቀጠሮ ቀን አለመገኘት ችግሮች፣ ማስረጃዎች (የህክምና፣ የፎረንሲክ) እና ፖሊስ ታራሚዎችን በቀጠሮ ቀን አለመቅረብ ችግሮች፣ ዓቃቤ ህግ በሚጠበቅበት የጥራት ደረጃ ኃላፊነቱን አለመወጣትና ክስና ምስክር በጥቅልና በጅምላ ማቅረባቸው፣ በተከራካሪዎች ክስ ለማሻሻል የሚቀርቡ ጥያቄዎች እና ተመሳሳይ ችግሮች ለጉዳዮች መዘግየት ዓይነተኛ ምክንያቶች ሆነው ታይተዋል። እነዚህን ችግሮች በየችሎቱ ለመፍታት ከሚደረጉ ጥረቶች በተጨማሪ ዘላቂ መፍትሔ የሚያገኙበትን ሥርዓት ዘርግቶ ለመተግበር በቁልፍ የውጤት መስክነት ታቅዷል።

## 1.2.2.2. የፍርድ አፈጻጸም ውጤቶችና ተግዳሮቶች

ፍርድ ቤት የሚሰጣቸው ፍርዶች/ውሳኔዎች በተለያየ መንገድ የሚፈፀሙ ሲሆን የፍትሐብሔር ጉዳዮች በፍርድ ቤቶች በተደራጀው የፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት ይፈጸማሉ። ከፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት የ2012 ዓ.ም አፈፃፀም ሪፖርት መረዳት እንደሚቻለው በበጀት ዓመቱ ያቀደውን የመመርመር ሥራ

በ81%፣ የንብረት ግምትና ክፍፍል ኃላፊነት በ60%፣ ንብረቶችን በሐራጅ የመሸጥና ለባለመብቶች የማረካከብ ድርሻ በ54%፣ ወደመረጃ ቋት መግባት የሚገባቸውን መዛግብት በ90 %፣ ከሃራጅ ሽያጭ እና ከተለያዩ ገቢዎች ለመንግሥት የሚገባውን የገንዘብ መጠን በ109% ማሳካት በመቻሉ የአፈጻጸም ቅልጥፍናን ለማሻሻል ያገዙ ውጤቶችን አስገኝቷል። ሆኖም እነዚህን ውጤቶች ለማገኘት በርካታ ክፍተቶችን መሙላትና ተግዳሮቶችን ማለፍ ግድ ነበር። ከእነዚህ ክፍተቶችና ተግዳሮቶች መካከል፡-

- **የውሳኔዎች/ትዕዛዞች ግልጽነት፣ የአደረጃጀትና የአሠራር ችግሮች፦** የፍርድ ቤት ውሳኔ/ትእዛዝ ግልጽ በማይሆኑባቸው አጋጣሚዎች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት ጉዳዩን ግልጽ ለማድረግ ከሚያጋጥሙት በርካታ ምልልሶች በተጨማሪ በአደረጃጀትና በአሠራር የሚያጋጥሙት ችግሮች በርካታ ናቸው። ከእነዚህ ችግሮች በዋናነት የሚጠቀሱት በየፍርድ ቤቱ የሚሰጡ ውሳኔዎችን ቢያስፈጽምም ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ብቻ መሆኑና የሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎችን የተከተለ አደረጃጀት አለመኖሩ፣ አንድን ፍርድ ለማስፈጸምም ተደጋጋሚ መዝገቦች የሚከፈቱበት ሁኔታ መኖሩ፣ ብቃት ያለው የሰው ኃይል መጠንና ጥራት አለመሟላቱ፣ በኢኮቴ የተደገፈ ዘመናዊ አሰራር አለመከተሉና አሰራሩ ለክትትልና ለቁጥጥር (ለኦዲትም) አለመመቸቱ፣ የመዝገብ አያያዝና ውሳኔ የተሰጠባቸው ንብረቶች ማቆያ ቦታን ጨምሮ የበጀት እና የሎጂስቲክስ አቅርቦት ችግሮች መኖራቸው፣ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ባለመዳበሩ ፍርዶችን በተገቢው አጭር ጊዜ ለማስፈጸም እንቅፋት መፍጠሩ መፍትሔ የሚያስፈልጋቸው ሆነው በመታየታቸው በስትራቴጂክ ዘመኑ መፍትሔ የሚያስገኙ ተግባራት በዕቅዱ ተካትተዋል።

### 1.2.2.3. የውሳኔዎች ጥራትና ተገማችነት

ይግባኝ የሚጠየቅባቸው እና እስከ ሰበር ችሎት የሚዘልቁ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔዎች ቀላል ቁጥር ያላቸው ባለመሆናቸው የውሳኔዎችን ጥራት ለማሻሻል የተለያዩ የማሻሻያ ተግባራት በመከናወን ላይ መሆናቸው ይታወቃል። ከእነዚህ የማሻሻያ ሥራዎች ውስጥ ጥቂቶቹን በማሳያነት ለማቅረብ ተሞክሯል።

- **የዳኞች ሙያዊ ብቃት መጎልበት፦** መደበኛ በሆኑ የትምህርትና ስልጠና መርሐ-ግብሮች በተጨማሪ በተመሳሳይ ችሎት የሚሰሩ ዳኞች የእርስ በእርስ መመማሪያ መድረኮች (peer to peer learning)፣ በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የሚዘጋጁ የውይይት መድረኮች፣ በሚዘጋጁ/በሚሻሻሉ የሕግ ማዕቀፎች ዙሪያ በሚካሄዱ ውይይቶች የሚደረጉ ተሳትፎዎች የዳኞችን ሙያዊ ብቃት ለማጎልበት ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸው አዎንታዊ እርምጃዎች ናቸው። ከዚህም በላይ የሚሰጡ ውሳኔዎችን የጥራት ደረጃ መመዘኛ መስፈርቶችን አካትቶ የተዘጋጀው የዳኞች አፈጻጸም ምዘና መመሪያ ጸድቆ ተግባራዊ መሆን ሲጀምርና ጥራትን ለማጎልበት የተዘጋጁ ሌሎች መመሪያዎች አፈጻጸም ሲጠናከር የዳኝነት ጥራትን ለማሳደግ ከፍተኛ ድርሻ ይኖራቸዋል።

- **በጉዳዮች የተለዩ ችሎቶች (Specialisedbenches) መደራጀት፦** በሁሉም የፌደራል ፍርድ ቤቶች ችሎቶች በጉዳዮች ዓይነት ተለይተው መደራጀታቸው ዳኞችን በየችሎቶቻቸው በሚታዩ ጉዳዮች ላይ የተለየ ክህሎት እንዲያጎለብቱ ያደርጋቸዋል። እንዲህ ዓይነት በሙያው

የተካኑ ዳኞችን የያዙ ችሎቶች መኖራቸው ደግሞ ለዳኝነት ቅልጥፍናፍ፣ ጥራትና ተገማችነት ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያበረክታል። ከዚህ አንጻር በጥናቱ ግኝቶች እና ምክረ-ሃሳቦች መሰረት የተደራጁ የንግድ ችሎቶችና አፈጻጸማቸውን ለማጠናከር የተዘጋጀውን የድርጊት መርሐ-ግብር በምሳሌነት ለማንሳት ይቻላል።

## የውሳኔዎችን ጥራት እና ተገማችነት ለማረጋገጥ የፈጠሩ ተግዳሮቶች

- **የዳኝነት ጥራትና ተገማችነት፡-** የዳኝነት ጥራትና ተገማችነትን ለመለካት የሚያግዙ የተለያዩ መመሪያዎች እና አሰራሮች ቢዘጋጁም ተጠናቅቀው ወደ ተግባር ባለመግባታቸው ራሱን የቻለና ሁሉን አቀፍ የጥራት መለኪያዎችን ተጠቅሞ የዳኝነት ጥራትን መለካት አዳጋች ሆኖ ቆይቷል፡ ፡ ከዚህም በላይ የጠበቆችን ወቅቱን የጠበቁ አስተያየቶችን ማሰባሰብን ጨምሮ ተገልጋዮች እና አጠቃላይ ሕብረተሰቡ በፍርድ ቤቶች ላይ ያለውን እርካታና አመኔታ ደረጃ መለየት የሚያስችል የዳሰሳ ጥናት ባለመካሄዱ የዳኝነት ጥራት የሚገኝበትን ደረጃ የሚያሳዩ መረጃዎችን የተመረኮዙ ማሻሻያዎች አለመደረጋቸውን መረዳት ተችሏል። የዳኝነት አገልግሎት ብቻ ሳይሆን በፍርድ ቤቶች የሚሰጡ አገልግሎቶችን የጥራት ደረጃ ለይቶ ተፈጻሚ ለማድረግ የሚያግዙ ስታንደርዶች ባለመዘጋጀታቸውና በአጠቃላይ የጥራት መለኪያ ክፍተቶች በመኖራቸው የየሥራ ክፍሎችን ባህሪ መሰረትያደረጉ መለኪያዎችን ማዘጋጀት የሚያስችሉ ተግባራት የስትራቴጂክ ዕቅዱ አካል እንዲሆኑ ተደርገዋል። ከዚህ ሁሉ በላይ ጭብጥ የመለየት እና ጉዳዩን በአግባቡ የመረዳት ክፍተት ያለባቸው ጥቂት ዳኞች መኖራቸውን ከተደረጉ ውይይቶች መረዳት በመቻሉ የዳኝነት ጥራትና ተገማችነትን ለማሳደግ ለአቅም ግንባታ ሥራዎች ተገቢውን ትኩረት ሰጥቶ መስራት ያስፈልጋል። ለዚህም ዳኞች በሚመደቡባቸው ችሎቶች በሚያዩዋቸው ጉዳዮች ላይ ሊኖራቸው የሚገባውን የተለየ ብቃት ከማጎልበትና በዚያው ችሎት እንዲቆዩ ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት ዘርግቶ ከመተግበር ባሻገር አጠቃላይ በሆኑ የውሳኔ አጻጻፍ፣ የሕግ አተረጓጎምና ትንተና፣ የመሰረታዊና የሥነ ሥርዓት ሕጎች አጠቃቀም ዙሪያ ቀጣይነት ያላቸው ተከታታይ ስልጠናዎችን እንዲያገኙ ማድረግ ጠቃሚ ይሆናል።
- **የውሳኔዎች ምክንያታዊነት (reasoning)፡-** በፍርድ ቤት ከሚሰጡ ውሳኔዎች በሚፈለገው ደረጃ ዝርዝር ምክንያቶችን የያዙ ሆነው አልታዩም። እንዲህ ዓይነት ችግሮች ቅልጥፍናን ለማሳደግ በሚደረጉ ጥረቶች ከሚያጋጥም የጊዜ እጥረት ሊከሰቱ ቢችሉም ከአቅም ውሱንነት ጋር መያያዛቸው ከተረጋገጠ መፍትሔ ሊዘጋጅላቸው ይገባል። በምክንያት ሳይደገፉ አስቀድሞ በተዘጋጀ ቅጽ እየተሞሉ ውሳኔዎች የሚሰጡበት አሰራር ለረዥም ጊዜ ሲሰራበት መቆየቱ ቢታይም አሠራሩ በጥራት ጉድለት ላይ ከሚያስከትለው ተፅዕኖ ባሻገር የተጠያቂነት ሥርዓትን የመተግበሩን ሥራ አዳጋች ያደርጋል። በመሆኑም ምክንያታዊ የውሳኔ አጻጻፍ ሥርዓትን ማጠናከር የሚያስችል ሥርዓት የመዘርጋቱ ሥራ በዕቅዱ ትኩረት ከተሰጣቸው ጉዳዮች አንዱ እንዲሆን ተደርጓል።
- **የሰበር ችሎቶች፡-** የውሳኔዎችን ጥራትና ተገማችነት ለማረጋገጥ የሰበር ችሎት ውሳኔዎች ወጥነት የሚጠበቅ ሲሆን በተወሰነ ደረጃም ቢሆን በተመሳሳይ የህግ ጉዳዮች የተለያዩ ውሳኔዎች የሚሰጡበት አጋጣሚ መኖሩ ጉዳዩን በዕቅድ ዘመኑ ትኩረት ከሚሰጣቸው አንዱ እንዲሆን አድርጎታል። ሕገመንግሥታዊ ድንጋጌዎችን ተከትለው በጠቅላይ ፍርድ ቤት የተደራጁ የሰበር

ችሎቶች የሕግ ስህተት አለባቸው ተብለው ከፌዴራልም ሆነ ከክልል ፍርድ ቤቶች የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ተቀብለው በማስተናገድ የአስገዳጅነት ባህሪ ያላቸው ውሳኔዎችን የመስጠት ኃላፊነት ቢሰጣቸውም ለኃላፊነታቸው የሚመጥን አደረጃጀትና አሠራር የተዘጋጀላቸው አለመሆኑን በተካሄደው የዳሰሳ ጥናት መመልከት ተችሏል። ችሎቶቹ አገር አቀፍ አስገዳጅነት ያላቸው ውሳኔዎችን የመስጠት ስልጣን ያላቸው ቢሆንም ችሎቱን በማጠናከር ረገድ የአሠራር ስርዓት አለመዘርጋቱ፣ ሕገ መንግስቱ ለሰበር ስርዓት ከሰጠው ትኩረት አንጻር የዳኞች አመዳደብ ልዩ ትኩረት የሚጠይቅ መሆኑ፣ የተሰጡ ውሳኔዎችም ሆኑ ሕገመንግሥታዊ ትርጉም የሚጠይቁ ጉዳዮች በሰባት ዳኞች እና በሕገመንግሥት አጣሪ ጉባዔ ከመታየት ባለፈ የሰበር ውሳኔዎች ጥራት የሚረጋገጥባቸው ግልጽ መስፈርቶች ተዘጋጅተው የአገሪቱን የህግ አስተምሮ አለማዳበራቸው፣ የተወሰኑት የሰበር ውሳኔዎች የጥራትና የተገማችነት እጥረት በመኖሩ በፌደሬሽን ምክር ቤት የተሻሩበት ሁኔታ መኖሩ፣ በሰበር አጣሪ ችሎቶች አያስቀርብም ተብለው በሚዘጉ ጉዳዮች ሥራው በጥራት ስለመሰራቱ ቅሬታ የሚያሰሙ ተገልጋዮች መኖራቸው... በስትራቴጂክ ዘመኑ ሊሞሉ የሚገባቸው ክፍተቶች ሆነው ታቅደዋል።

- **ጠንካራ የጥናትና ምርምር ክፍል አለመደራጀት፦** ብቃት ያለው የጥናትና ምርምር ስራ ክፍል ለዳኝነት አገልግሎት ጥራት ወሳኝ ድርሻ ቢኖረውም የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ጥናትና ምርምር ክፍል ኃላፊነቱን በሚመጥን ደረጃ የተደራጀ አለመሆኑን መረዳት ተችሏል። በጠ/ፍ/ቤት ደረጃ የተደራጀው ይህ የሥራ ክፍል የተወሰኑ የሰበር ውሳኔዎችን መርጦ በሕትመትና በድረገጽ እንዲሰራጩ ከማድረግ አልፎ የዳኝነት አገልግሎት የሚያሻሽሉ የሕግ ጥናቶችን ባለማካሄዱ ኃላፊነቱን በተገቢው መንገድ ሳይወጣ ቆይቷል። በመሆኑም በዚህ ስትራቴጂክ ዘመን ተገቢ ቦታ እንዲሰጠውና ደረጃውን የጠበቀ የሕግ ጥናትና ምርምር ተግባራትን የሚያከናውንበትን አቅም እንዲኖረው የሚያደርጉ ስትራቴጂዎች ተቀርጸዋል።
- **የዳኞች ሥነ ምግባር ችግር /ሙስና/፦** በሥነ ምግባር ችግር ወይንም በሙስና ጉዳይ የሚጠቀሱ ዳኞች መኖራቸው ቢነገርም በዚህ ረገድ ለዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የቀረቡ ጉዳዮች አነስተኛ በመሆናቸው እና ችግሩን ለማጥራት የተሄደበት ርቀት አነስተኛ መሆኑን ለማየት ተችሏል። በጉዳዩ ላይ በፍርድ ቤቱ አመራሮች፣ ዳኞች እና አስተዳደር ሠራተኞች መካከል በተሟላ መልኩ ግልጽ ውይይት ካለመደረጉም ሌላ ፍርድ ቤቶች በሙስና ጉዳይ ያላቸውን አቋም ለሕዝብ የሚያሳውቁበት ተግባር አለመከናወኑ ሊሞሉ የሚገባቸው ክፍተቶች ሆነው ታይተዋል፤
- **የተገልጋይ አያያዝ፦** የፍርድ ቤት አሰራር ሰብአዊነት/ሰዋዊነት የሚጎድለውና በተገልጋዮች አያያዝ ረገድ መፈታት የሚገባቸው ችግሮች መኖራቸው ታይቷል። የገለልተኝነትን መርህ ተግባራዊ አድርጎ ለተከራካሪ ወገኖች እኩል ዕድል በመስጠትና በትህትና በማስተናገድ፣ የመስማትና ማስረጃ የማቅረብ መብቶችን ያከበረ ሰዋዊ የዳኝነት አገልግሎት እንዲያገኙ በማድረግ በኩል መፍትሔ የሚፈልጉ ችግሮች ከመኖራቸውም ሌላ ኃይለ-ቃል ተጠቅሞ የአንደኛውን ተከራካሪ ወገን የማሸማቀቅ ተግባር እንደሚፈጸም መረዳት ተችሏል። እንዲህ ዓይነት አሠራሮች በፍርድ ጥራት እና ተገማችነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ በመሆናቸው በዕቅዱ እንዲስተናገዱ ተደርገዋል ።

## 1.2.3. የዳኝነት አገልግሎት ተደራሽነት

ሁሉን አቀፍ የሆኑ የፍርድ ቤቶች አገልግሎት ማሻሻያ ፕሮጀክቶች የተደራሽነት ችግሮችን ለመፍታት ለሚያስችሉ ተግባራት ተገቢውን ትኩረት ሰጥተው ሲሠሩ ይታያሉ። ከዚህ አንጻር ፍርድ ቤቶች አሰራራቸውን ለተገልጋይ ግልጽ ማድረግ፤ አገልግሎቶችን በቀላሉ ማግኘት የሚችሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤ አቅም ያገናዘበ የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ መተመን እና ተገቢነት ባለው አጭር ጊዜ ለጉዳዮች ዕልባት የሚሰጥበት አሰራር መዘርጋት የሚያስችል ሥርዓት ለመዘርጋት የሚደረጉ ጥረቶችን ማሳያ ማድረግ ይቻላል። እነዚህ አሠራሮች ባልተሟሉበት ሁኔታ የሚሰጥ የዳኝነት አገልግሎት ከተደራሽነት አንጻር ውስን ስለሚሆን ችግሮችን ለመፍታት የተለያዩ ጥረቶችን በማድረግ የተወሰኑ ውጤቶች ተገኝተዋል።

### የፍትህን ተደራሽነት ለማሻሻል ውጤት የታየባቸው እርምጃዎች

- **አካላዊ ተደራሽነትን ማጎልበት፦** የፌደራል ከፍተኛ እና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች በሀገሪቱ በሙሉ ወይም በከፊል እስኪደራጁ ስልጣናቸው ለክልል ፍርድ ቤቶች በውክልና የተሰጠ መሆኑ ይታወቃል። የውክልና ስልጣናቸው በተነሳባቸው ክልሎች የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተዘዋዋሪ ችሎቶችን በማደራጀት አገልግሎቱን ሲሰጥ ቆይቷል። የተዘዋዋሪ ችሎቶችን ቁጥር ከሁለት ወደ ስድስት ማሳደጉ የከፍተኛ ፍርድ ቤትን የበለጠ ተደራሽ አድርጎታል። በተጨማሪም ተዘዋዋሪ ችሎቶችን በቋሚ ምድብ ችሎት ለመተካት በሚያደርገው ጥረት በቅርቡ በሃዋሳ ከተማ ቋሚ ምድብ ችሎት የተደራጀ ሲሆን በአርባምንጭ ከተማ ተጨማሪ ምድብ ችሎት ለማደራጀት የሚደረገው እንቅስቃሴ ለፍርድ ቤቱ ተደራሽነት ማደግ ከፍተኛ እመርታ ነው።

- **የመረጃ ተደራሽነት፦** በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ከዳኝነት አገልግሎት ጋር ተያያዥነት ያላቸው መረጃዎች ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችሉ አሰራሮች በተወሰነ ደረጃ ተዘርግተዋል። ከነዚህም መካከል የመረጃ መስጫ ዴስክ፤ የተሻለ ድረ ገጽ፤ ተገልጋዮች የመዝገብ ቀጠሮ እና በየዕለቱ በችሎት የሚታዩ የመዛግብት ዝርዝር የሚታይበት የፕላዝማ ስክሪን፤ ነጻ የጥሪ ማዕከል፤ አቅጣጫ አመላካች ታፔላዎች፤ የሠራተኞችን ማንነት በተለይም የችሎት አገልግሎት ሰጪዎችን ለይቶ ለማወቅ የሚያስችሉ የሥራ ልብሶች/ጋወኖች፤ እና የባለሙያዎች የደረት መለያ ባጆች ጥቅም ላይ መዋላቸው የመረጃ ተደራሽነት በማሳደግ ምቹ ሁኔታን የሚፈጥሩ መልካም ጅምሮች ናቸው።

- **የዳኝነት ክፍያ ተደራሽነት፦** በፍርድ ቤቶች ስራ ላይ ያለው የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ከ68 ዓመት በላይ ያገለገለ በመሆኑና በህግም አነስተኛ የገቢ ምንጭ ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች የሚስተናገዱበት "የደሃ ደንብ" በመኖሩ በዳኝነት ክፍያ ምክንያት የተገልጋዮች ፍትህ የማግኘት መብት አልተገደበም። ከዚህም በላይ የፌደራል ፍርድ ቤቶች ወቅታዊ ሁኔታውንና የዳኝነት አገልግሎት አሰጣጥ ደረጃን ባገናዘበ መልኩ በጥናት ላይ ተመስርቶ ረቂቅ የዳኝነት ክፍያ ደንብ መዘጋጀቱ የሚበረታታ ነው።

- **በቴክኖሎጂ የታገዘ ተደራሽነት፦** የኢኮቴ መስፋፋት የፍርድ ቤቶች አገልግሎትን ለማሻሻል ከፍተኛ ፋይዳ ያለው ነው። በክልል ለሚገኙ ባለ ጉዳዮች በቪዲዮ ኮንፈረንስ የርቀት ችሎት ማዕከል እና ኢ-ፋይሊንግ ተጠናክሮ መቀጠሉ ተገልጋዮች አዲስ አበባ መምጣት ሳያስፈልጋቸው በሚኖሩበት

አቅራቢያ በሚገኝ የርቀት ችሎት ማዕከል እና በማረሚያ ቤት መስተናገዳቸው እንግልትን የቀነሰላቸው ከመሆኑም በላይ ምቹ ሁኔታዎችን ፈጥሮላቸዋል፡፡ ካለው የመዝገብ ብዛት አንጻር በቂ ባይሆንም በ2013 ዓ.ም መደበኛ ችሎት በሚካሄድባቸው ችሎቶች የቪዲዮ ኮንፈረንስ ክርክሮችን በማካሄድ 5,900 ተከራካሪ ወገኖች የተሳተፉባቸው 2,284 መዝገቦች ዕልባት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ የክልል ተከራካሪዎች የኢ-ፋይሊንግ ሥርዓትን በመጠቀም ባሉበት ሆነው አቤቱታቸውንም ሆነ መልሳቸውን እንዲያቀርቡ በመደረጉ በተመሳሳይ በጀት ዓመት በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ብቻ ከዘጠኝ ክልሎች የተላኩ 1,737 የይግባኝ እና የሰበር መዝገቦችን ለማስተናገድ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ለተገልጋዮች የሞባይል አጭር የጽሁፍ መልዕክት አገልግሎት በመስጠት መዝገቦቻቸው የሚገኙበትን ደረጃ እንዲያውቁ እየተደረገ ይገኛል፡፡

- **ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተገልጋዮች የሚደረግ ድጋፍ፦** በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዲስ በሚገነቡ ህንጻዎች ለአካል ጉዳተኞች፣ ለአረጋውያንና ለአቅመ ደካሞች አመቺ የሆኑ የችሎት ቢሮ አደረጃጀቶች እንዲኖሩ ታሳቢ እየተደረገ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም እነዚህ የሕብረተሰብ ክፍሎች ወደ ፍርድ ቤቶቹ አገልግሎት ለማግኘት በሚመጡበት ጊዜ ከሌሎች ተገልጋዮች ቅድሚያ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ እየተደረገ ሲሆን አሰራሩም እየጎለበተ ይገኛል፡፡

- **ሴቶችን እና ህጻናትን የተመለከቱ ድጋፎች፦** የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጾታዊ ትንኮሳን የሚመለከት ፖሊሲ አውጥቷል፡፡ በፌደራል ፍርድ ቤቶች በተለይ ህጻናት ይዘው ለሚመጡና ነፍሰጡር ሴቶች ግቢ ከመግባት ጀምሮ ቅድሚያ አገልግሎት የመስጠት አሰራር እየተተገበረ ይገኛል፡፡ በወንጀል ጉዳይ ተከሰው ፍርድ ቤት ለሚቀርቡ ህጻናት ባህሪ እና ስነልቦና ምቹ የሆነ የተደራጀ ችሎት መኖሩ፣ ህጻናት በተለየ ክፍል በካሜራ አማካኝነት ለችሎት ምስክርነታቸውን የሚሰጡበት አሰራር መኖሩ፤ በየምድብ ችሎቶች የህፃናት ማቆያ ማዕከላት መደራጀቱ እና ሴቶችና ሕጻናት ነጻ የህግ ሙያ ድጋፍ እንዲያገኙ መደረጉ በፍርድ ቤቶቹ እመርታ የታየባቸው አሰራሮች ናቸው፡፡ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተቋቋመው የህጻናት ፍትህ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት በ2013 በጀት ዓመት ለ3,422 ሕጻናት (ሴት 1541 ወንድ 1881) ነጻ የህግ አገልግሎት ሰጥቷል፡፡ በተጨማሪም ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሥነ ልቡና ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው 290 (ሴት 197 ወንድ 93) ሕጻናትን የመደገፍ፤ ወላጆቻቸውን የማስማማት እና በልጆች አስተዳደግ ዙሪያ ያተኮረ የምክር አገልግሎት ድጋፍ አድርጓል፡፡

- **ተከላካይ ጠበቃና እና ሌሎች የህግ ድጋፎች፦** የተከላካይ ጠበቆች ጽህፈት ቤት በቂ ባለሙያዎች የሌሉበት ሆኖ የቆየ ቢሆንም ካለፉት ሶስት ዓመታት ወዲህ ተጨማሪ ተከላካይ ጠበቆች ተመድበውለታል፡፡ ተከላካይ ጠበቆች ከሲቪል ሰርቪስ አስተዳደር ወጥተው በዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ስር እንዲተዳደሩ ተደርገዋል፡፡ ይህንንም ተከትሎ በጽ/ቤቱ የአደረጃጀት ማሻሻያዎችን በማድረግ ለመጀመሪያ ጊዜ 74 ተከላካይ ጠበቆች በጉባዔው እንዲሾሙ የደመወዝ እና የጥቅማጥቅም መሻሻሎች በማድረግ አበረታች አስተዳደራዊ እርምጃዎች ተወስደዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ጽህፈት ቤቱ በየምድብ ችሎቶች እና በተዘዋዋሪ ችሎቶች ተመድበው አገልግሎት ለሚሰጡ ተከላካይ ጠበቆች ቢሮ እንዲደራጅና የአቅርቦት ፍላጎቶች እንዲሟሉ ተደርጓል፡፡

በመሆኑም ጽ/ቤቱ በ2013 ዓ.ም በከባድ ወንጀል ተከሰው ጠበቃ ማቆም የኢኮኖሚ አቅም ውስንነት ላለባቸው በ12,023 መዛግብት ለተከሰሱ 29,923 ባለጉዳዮች የተከላካይ ጥብቅና አገልግሎት መስጠት ችሏል። ሌሎች የሕግ ምክርና ድጋፍ አገልግሎቶች በጠበቆች ማህበር፣ በትምህርት ተቋማት እንዲሁም በሲቪክ ማህበራት እየተሰጠ የሚገኝ ሲሆን የፌደራል ፍርድ ቤቶች በግቢዎቻቸው ውስጥ እነዚህ ተቋማት የህግ ድጋፍ እንዲሰጡ በመፍቀድ እየተባበሩ ይገኛሉ።

- **የፍርድ ቤት መር አስማሚነት አገልግሎት፦** አዋጅ ቁጥር 1234/2013 የፍርድ ቤት መር አስማሚነት ስራ የህግ እውቅና እንዲያገኝና ለፍርድ ቤት በቀረቡ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚ እንዲሆኑ ይደነግጋል። ይህም ጉዳዮች በአጭር ጊዜ፣ በአነስተኛ ወጪ እና ሁለቱም ወገኖች በሚቀበሉት ውጤት እንዲጠናቀቅ ሊያደርግ የሚችል እንደሚሆን ይታመናል። አሁን ባለው ሁኔታ ፍርድ ቤት መር የሆነ የማስማማት ስራ በተገልጋዮች ፈቃደኝነት ላይ ተመስርቶ በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ የአስማሚነት ክህሎት ስልጠና በተሰጣቸው ረዳት ዳኞች እየተከናወነ ይገኛል። በዚህም ከችሎት የሚመሩላቸው ጉዳዮችን በስምምነት ዕልባት እንዲያገኙ በማድረግ የዳኝነት ቅልጥፍናን ለማሳደግ የራሳቸውን አስተዋጽዖ እያበረከቱ ናቸው። በተጨማሪም የፍርድ ቤት መር አስማሚነት የአሰራር ስርዓት ለመዘርጋት የሚያስችል መመሪያ እንዲሁም የአስማሚነት የስልጠና ዕቅድ እና ማንዋል በዝግጅት ሂደት ላይ ይገኛሉ።

### የዳኝት አገልግሎት ተደራሽነትን በተመለከተ የሚታዩ ተግዳሮቶች

የፌደራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት አገልግሎት ተደራሽነትን ለማጎልበት ትኩረት ከሚሹ ጉዳዮች መካከል፡-

- **አካላዊ ተደራሽነት፦** የፌደራል ፍርድ ቤቶችን በክልሎች የማደራጀቱ ስራ የተጀመረ ቢሆንም የት ይደራጁ የሚለውና የተደራጁት ለየትኛው አካባቢ ያገለግሉ የሚለው ራሱን በቻለ ጥናት በሚፈለገው ደረጃ ያልተመለሰ ነው። የፌደራል ፍርድ ቤቶች በክልል እንዲደራጁ የክልል ፍርድ ቤቶች ፍላጎት መሆኑ የታየ ሲሆን በተለይ ከፌደራል ስርዓት ግንባታ አንጻር የሚኖረው ትርጉም ታይቶ በተሟጠነ ሁኔታ ምላሽ አላገኘም። በአዲስ አበባም ቢሆን ፍርድ ቤቶቹ በየክፍለ ከተማው የተደራጁበት አግባብ የአስፈፃሚውን አደረጃጀት በቀጥታ የተከተለ መሆኑ ተገቢ ስለመሆኑ ጥያቄ የሚቀርብበት በመሆኑ በጥናት ሊመለስ የሚገባው ነው። ለዚህም የተደራሽነት (በአካል፣ በገንዘብ፣ በቴክኖሎጂ) መለኪያ ጥናት አካሂዶ አካባቢያዊ ሁኔታዎች፣ የህዝብ ብዛት፣ እንዲሁም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴን ያገናዘበና የተገልጋዮችን የፍትህ ፍላጎት ታሳቢ ያደረገ ዘላቂ አደረጃጀትን የሚያመለክት ንድፍ (judicial mapping) ማዘጋጀት ያስፈልጋል።
- **የመረጃ ተደራሽነት፦** ፍትህ በማግኘት ሂደት ከፍርድ ቤት አገልግሎት ተደራሽነት አንጻር ተገልጋዮች ሁሉን አቀፍ መረጃ በቀላሉ ማግኘት የሚችሉበት ስልቶችን የመጠቀማቸው ሁኔታ አንዱ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው። በአካል ለሚቀርቡ ሰዎችም ይሁን በርቀት በድረ ገጽ አማካኝነት መረጃ ማግኘት የሚሹ አካላት መረጃ እንዲያገኙ ለማስቻል የመረጃ ምንጮችን ተደራሽነትና አማራጭ መንገዶችን ማሳደግ ይጠይቃል። በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ያለው የመረጃ አሰጣጥ አካል ጉዳተኞችን ያገናዘበ መሆኑ እና ነጻ የህግ ድጋፍ ማዕከል የሚገኝባቸውን አማራጮች የሚጠቀም

እንዲሆን ከማስቻል አንጻር ክፍተት ይታይበታል። የመረጃ ዴስክ በሁሉም ፍርድ ቤቶች ማደራጀትና ባለሙያዎችን በተገልጋይ አያያዝ ዙሪያ ማሰልጠን፣ የተገልጋይ አያያዝን የሚመለከት መመሪያን ማዘጋጀት፤ የድረ ገጽ ግንባታን እና መረጃን የሚሟላት ስራ በሁሉም ፍርድ ቤቶች በፍጥነት ማጠናቀቅ፤ እንዲሁም በባለሙያ የማይታገዙ ተሟጋቾች በቀላሉ ሊረዱት በሚችል ግልጽ ቋንቋ መረጃ ሊሰጡ የሚችሉ ህትመቶች ማዘጋጀት በቀጣይ ትኩረት የሚሹ ናቸው።

- **ተዘዋዋሪ ችሎት፦** የፌደራል ፍርድ ቤቶችን በክልሎች ለማደራጀት የሕግ ማሻሻልን የሚጠይቅ ሲሆን ማደራጀቱም ሰፊ የሎጀስቲክ አቅርቦት ይፈልጋል። በመሆኑም የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን በክልሎች የማደራጀቱ ጉዳይ ተግባራዊ እስከሚሆን ድረስ ቋሚ የተዘዋዋሪ ችሎትን በሚፈለገው ቁጥርና ቦታ የማደራጀት፤ ቀደም ሲል የተደራጁትንም የማጠናከር፤ የቪዲዮ ኮንፈረንስ የርቀት ችሎት አገልግሎት ማዕከላትን በርካታ ተገልጋዮች በሚኖሩባቸው ቦታዎች የማስፋፋት ስራን መስራት ያስፈልጋል። ከዚህ ጎን ለጎን በተዘዋዋሪ ችሎቶች የሚስተዋለውን የሎጂስቲክና የአበል ክፍያ ችግሮችን፤ እንዲሁም የዳኞችና ሌሎች ባለሙያዎች የደህንነት ስጋቶችን እያጠኑ መቅረፍ ተገቢ ይሆናል።

- **የክልል ፍርድ ቤቶች የፌደራል ዳኝነት ስልጣን፦** ፌደራል ፍርድ ቤቶች ባልተደራጁባቸው ክልሎች በፌደራል የዳኝነት ስልጣን ስር ያሉ ጉዳዮች በክልል ፍርድ ቤቶች በውክልና ይታያሉ። ነገር ግን በክልል ፍርድ ቤቶች የሚታዩ የፌዴራል ጉዳዮች ሁኔታ በፌደራል ፍርድ ቤቶች የሚታወቁበት አሰራር ባለመዘርጋቱ መረጃዎች ተለይተው በአግባቡ አይደራጁም። አፈጻጸሞችን የሚያሳዩ ሪፖርቶችም ለፌደራል ፍርድ ቤቶች አይቀርቡም። ክልሎቹ ለሚያከናውኑት ተግባር የማካካሻ በጀት በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሚላክላቸው ቢሆንም በጀቱ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መሰጠት አለበት ከሚለው ጥያቄ አንስቶ አሰራሩ ጥያቄ የሚነሳበትና የድጎማ መጠኑም በተጠና ሁኔታ ተወስኖ የሚላክ ባለመሆኑ የሚታዩ ክፍተቶች የሚሞሉበት ሥርዓት አልተዘረጋም። የክልል ፍርድ ቤቶች የውክልና አሰራርን የሚገነዘቡበት ሁኔታ በሕገ መንግሥት የተሰጠ ስልጣን ከመሆኑ አንጻር በመሆኑ በተጨማሪም በፌደራል ጉዳዮች ላይ የዳኝት አገልግሎት ሲሰጡ የገለልተኝነትን ጥያቄ ይነሳባቸዋል። በነዚህ ጉዳዮች ላይ ከክልል ፍርድ ቤቶች ጋር ተቀራርቦ የመስራት ክፍተቶች ይታያሉ።

- **የፍርድ ቤቶች ምድረ ጊቢ ተገልጋይን ማዕከል ያደረገ አለመሆኑ፦** የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ምድረ ጊቢ በአጠቃላይ ተገልጋይን ማዕከል ያደረገ ከመሆን አንጻር ክፍተት ይታይበታል። የፍርድ ቤት አካባቢ ከሕዝብ መጸዳጃ ቤት አንስቶ ለተገልጋዮች አመቺ የሆነ መሰረተ ልማቶች ያለው አለመሆኑ፤ እንዲሁም ልዩ ፍላጎት ላላቸው ሰዎችም ጭምር አመቺ የሆነ ቦታ አለመሆን በቀጥታ ምልከታ መታዘብ ይቻላል። ከዚህ አንጻር ፍርድ ቤቶች አገልግሎት የሚሰጡባቸው ማዕከላትን በሁሉም መስክ ለተገልጋይ ምቹ የማድረግ ስራ ትኩረት የሚፈልግ ነው።

- **ልዩ ድጋፍ የሚፈልጉ ባለጉዳዮችን በተመለከተ፦** የፌደራል ፍርድ ቤቶች የሚከራዩዋቸው አንዳንድ ህንጻዎች ለአረጋውያን፣ አካላዊ ጉዳት ላለባቸው ሰዎች እና ልዩ ድጋፍ ለሚፈልጉ ሰዎች ምቹ ያልሆኑ፤ በቂ መቀመጫ የሌላቸውና የተገልጋይን ፍላጎት ያላገናዘቡ መሆናቸው ይታያል። አካላዊ

ጉዳት ላለባቸው ሰዎች አሁን ያሉትን ህንጻዎች ተደራሽ ማድረግ አስቸጋሪ የሚሆንበት ሁኔታ እንደሚኖር የሚታመን ሲሆን ይህን ለማካካስ አማራጭ ሁኔታዎችን ለመጠቀም የሚያስችል መመሪያም ሆነ አሰራር አልተዘጋጀም።

- **የዳኝነት ክፍያ፦** ዳኝነት ለመክፈል አቅም የሌላቸው ተገልጋዮችን በሚመለከት አሁን ያለው አሰራር ከክፍያ ነጻ ማድረግ ብቻ ሲሆን ሌሎች አማራጮችን ለምሳሌ ቀስ በቀስ መክፈል የሚቻልበትን አሰራር አያካትትም፤ በተሻሻለው ረቂቅ የዳኝነት ክፍያ ደንብ ላይም አልተካተተም። የዳኝነት ክፍያው ላይ ማሻሻያ ለማድረግ የተጀመረ ሥራ ቢኖርም የክፍያው መጠን ከተጠየቁት አገልግሎቶች ጋር ማገናዘብ፣የዳኝነት ጥራት ለማረጋገጥ የሚኖረው ሚና እና ምክንያት የሌለው ክስ ፍርድ ቤት እንዳይቀርብ ለመከላከል የሚያስች እንዲሆን  እንዲሁም ፍትህ የማግኘት መብትን እንዳያጠብ ከማድረግ አኳያ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልገዋል።
- **የህጻናትን ጥቅም ማስጠበቅን በተመለከተ፦** የህጻናት ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት በርካታ ውጤቶችን ያሳካ ቢሆንም ለበርካታ ዓመታት የፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ሆኖ የቆየ፣ የአደረጃጀቱ አግባብነት እና ቀጣይ አሰራሩ ምን እንደሚሆን ግልጽ አቅጣጫ ያልያዘ ነው። ከፕሮጀክት ወጥቶ ራሱን በቻለ ስርአት ስለሚተዳደርበት ሁኔታ የተወሰደ ተጨባጭ እርምጃ አይታይም። የበጀት ምንጭ የማስፋፋት/የማጎልበት ሥራ ሥራም ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።
- **የተከላካይ ጥብቅና እና የህግ ድጋፍ ተደራሽነት፦** በሀገሪቱ የወንጀል ፍትህ ፖሊሲ ነጻ የጥብቅና አገልግሎት ከታሰሩ ሰዎች አንስቶ እንደሚሰጥ የሚያመለክት ቢሆንም በተግባር ላይ የዋለ አይደለም። ስለሆነም የተከላካይ ጠበቆች የሚሰጡት የህግ ድጋፍ አገልግሎት በፍርድ ቤት የችሎት ሂደቶች ላይ ብቻ ያተኮረ እንዳይሆን እና ክሱ ከመሰማቱ በፊትም አገልግሎቱ የሚያስፈልግ ለመሆኑ ግንዛቤ ተይዞ መተግበር ያለበት ነው። በሌላ በኩልም ፅህፈት ቤቱ በሰው ኃይልም ሆነ በሎጂስቲክ በተሻለ ትኩረት እና ደረጃ ላይ ቢሆንም ተጨማሪ ፍላጎቶቹ እየታዩ ሊፈቱ የሚገባቸው ናቸው። የተከላካይ ጠበቃ አገልግሎትና የጽህፈት ቤቱ አደረጃጀት በጥናት የተደገፈ ውሳኔ ይጠይቃል።
- **የትርጉም አገልግሎት፣** የፌደራል ፍርድ ቤቶችን የስራ ቋንቋ ለማይረዱ ባለጉዳዮች በብቃት፣ በሚፈለገው መጠንና አይነት አስተርጓሚ ማግኘት ህገመንግስታዊ መብት ነው። ይህ መብት ግን በተሟላ መልኩ እየተጠበቀ አለመሆኑ ይስተዋላል። ለዚህም አንዱ ምክንያት ለአስተርጓሚ የሚፈጸመው ክፍያ ማነስ ነው። ከክፍያው አነስተኛነት ባሻገር የአከፋፈል ሁኔታ ላይ ያለ አመቺ ያልሆነ አሰራር መኖሩ የትርጉም አገልግሎት የሰጡ ባለሙያዎች ክፍያ ለመቀበል መጓጓዝ ያለባቸው እና አንዳንድ ጊዜም ምልልስ የሚታይበት ነው። ይህ አሰራር በስራ ላይ ላሉትም አስተርጓሚዎች ስራውን በፍላጎት እንዳያከናውኑ የሚያደርግ ነው። በሌላም በኩል በፍርድ ቤቶቹ በርካታ ቋንቋዎች የትርጉም ፍላጎት ቢኖርም አስተርጓሚ በሚፈለገው ደረጃ የማይገኝ መሆኑ ለፍርድ ሂደቱ ቅልጥፍና እንቅፋት ነው።
- **ፍርድ ቤት መር አስማማነት፡-** እስከ አሁን ባለው አሰራር አማራጭ የሙግት መፍቻ መንገዶች ትርጉም ባለው መልኩ ለፍርድ ቤት ስራ አጋዥ ሆነው አልተተገበሩም። ፍርድ ቤት መር አስማሚነት አገልግሎት በሙከራ ደረጃ መስጠት የተጀመረ ቢሆንም ያስገኘው ውጤት ወይም የገጠመው

ችግር በጥናት አልተለየም። ይሁን እንጂ በተሻሻለው አዋጅ ፍርድ ቤት መር አስማሚነት የህግ ማዕቀፍ ድጋፍ እንዲያገኝ በመደረጉ አገልግሎቱን በሰፊው መስጠት የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸትና መደበኛውን የዳኝነት አገልግሎት ጫና በመቀነስ ቅልጥፍናን ማጎልበት የሚችልበት አሰራር መዘርጋት የሚጠበቅ ይሆናል።

## 1.2.4. የህዝብ አመኔታ እና ተቀባይነት

የፌደራል ፍርድ ቤቶች የሚሰጡዋቸው የዳኝነት አገልግሎቶች የዳኝነት ነጻነትና ገለልተኝነትን ያስከበሩ፣ ፣ ቅልጥፍናን፣ ጥራትና ተደራሽነትን ያሳደጉ፣ የሕብረተሰቡን መብትና ግዴታዎች ያሳወቁ እና የተሰጡ ፍርዶችን ማስፈጸም ያስቻሉ ሆነው ከተገኙ በሕዝብ ዘንድ ያላቸውን ተቀባይነት እና ተዓማኒነት ማሳደግ ይችላሉ። እንዲህ ዓይነቱን ተዓማኒነት ለማምጣት ባለፉት የተወሰኑ ዓመታት በተከናወኑ በርካታ ተግባራት የተወሰኑ ተጨባጭ ለውጦች መታየት የጀመሩ ሲሆን ጥቂቶቹን በማሳያነት ለማቅረብ ተሞክሯል።

### ውጤት የታየባቸው እርምጃዎች

- **የፍርድ ቤት አመራር አቋም፦** የፌደራል ፍርድ ቤቶች አመራር በሚሰራቸው ስራዎች የህዝብን አመኔታ ለማግኘት አልሞ እየሰራ መሆኑ፣ የሕዝብን አመኔታ ለማግኘት ክርክሮችን በሰላምና በሕግ የበላይነት መቋጨት የሚያስፈልግ መሆኑንና ክርክሮች እንደ ኢንቨስትመንት ሊወሰዱ የሚችሉ መሰረታዊ ጉዳይ መሆናቸውን አመራሩ የተረዳው መሆኑ እንደ ጥንካሬ የሚወሰድ ነው።
- **የፍርድ ቤቶች መረጃዎች፣ ሂደቶች እና ውሳኔዎች ለህዝብና ለሚዲያዎች ያላቸው ተደራሽነት፦** የፍርድ ቤቶች መረጃዎች ለተገልጋዮች እንዲሁም ለህዝብና ለሚዲያዎች ማድረስ በተለይ ተገልጋዮች ጉዳዮቻቸውን ለመከታተል የሚያስችላቸው የኢኮቴ ማሻሻያዎች፣ የምስክሮች ቃል የሚቀዳበት አሰራር መኖር፣ የመዝገቦች ዲጂታይዝ መሆን ለፍርድ ቤቱ ተገልጋዮች ላላቸው እርካታ አስተዋጽዖ ያለው ጉዳይ ነው። በተጨማሪም የችሎቶች አዳራሾች እጥረት እንደተጠበቀ ሆኖ ጉዳዮችን በግልፅ ችሎት ለማካሄድ ያለው ጅምርና ቁርጠኝነት፣ ውሳኔዎችን የማሳተም (በዌብሳይት ማድረስን ጨምሮ) እና የማሰራጨት ጉዳይ ጥሩ ጅምሮች ናቸው።
- **የህዝብን ግንዛቤ እና ተሳትፎ ማጎልበት ፦** የህዝብን ግንዛቤ ከማሳደግ አንጻር በፌደራል ፍርድ ቤቶች እየተተገበሩ ያሉ መልካም ጅምሮች አሉ። ለምሳሌ፣ በሬዲዮ ፋና የሚተላለፍ ፕሮግራም፣ በማህበራዊ ሚዲያዎች የሚሰራጭ መረጃ፣ በትምህርት ቤቶች የህግ ግንዛቤን ለማጎልበት ከትምህርት ሚንስቴር ጋር የተደረሰው ስምምነት ተጠቃሾች ናቸው።
- **የተገልጋይ አስተያየት የሚሰበሰብበት አሰራር፦** የተገልጋዮችን አያያዝ ማሻሻል የህዝብ አመኔታን ለማግኘት አስፈላጊ ከሆኑ እርምጃዎች ውስጥ አንዱ ነው። ከዚህ አንጻር ተገልጋዮች ቅሬታቸውን ለፍርድ ቤቶቹ ማሰማት የሚችሉበት አሰራር ለተገልጋዮች በተሻለ ግልጽነት መቀመጡ ተገልጋዮች በፍርድ ቤት ላይ ያላቸውን አመኔታ ለማሳደግ ያስችላል። የተገልጋዮችን እርካታ በመለካት ምላሽ የሚፈልጉ አቅጣጫዎችን ለመለየት የሚያስችል መረጃ የመሰብሰብና የመተንተን ሁኔታ በተወሰነ መልኩ እየተተገበረ ይገኛል። ከዚህ አንጻር በቀጥታ የህዝብ አስተያየት የሚሰበሰብበት አሰራር

በቋሚነት የተዘረጋ ባይሆንም በሬጅስትራር አሰራር ላይ ያሉ የተገልጋይ አስተያየቶችን የማሰባሰብ ስራ በጠቅላይ ፍርድ ቤት እየተከናወነ ይገኛል።

## የህዝብ አመኔታን በተመለከተ የሚከተሉት ጉዳዮች ትኩረት የሚያስፈልጋቸው ናቸው።

- **የህዝብ አመኔታ መለኪያ አለመኖር፦** እስካሁን ባለው አሰራር ፍርድ ቤት በሕዝብ አመኔታ አገኘ ለማለት ጥቅም ላይ የሚውለው መለኪያ አይታወቅም። የመረጃ ምንጭ ማነው፣ ተቀባይት ያለው የአመኔታ ጥናት ማከናወኛ መንገድ የትኛው ነው፣ በየስንት ጊዜው ሊሰራስ ይገባዋል የሚሉትና መሰል ጥያቄዎችን የሚመልስ መለኪያ ማውጣትና መተግበር ያስፈልጋል፤

- **የተገልጋዮች እና የማህበረሰብ አስተያየት መለኪያ ሰርቬይ** (periodic client satisfaction survey and public perception survey)፦ የህበረተሰቡን አስተያየት በመሰብሰብ ረገድ ከዚህ በፊት የተሰሩ የተወሰኑ ጥናቶች ያሉ መሆኑ ቢገለጽም ይፋ ተደርገው ለእርምት የሚሆኑ ሀሳቦች የተወሰዱበት መሆኑ በግልጽ አይታይም፤ ፤ የተገልጋይ ሰርቬይ በተወሰነ ደረጃ እየተሰራ ቢሆንም በተጠናከረ መልኩ በየተወሰነ ጊዜና በመደበኛነት/በቋሚነት የሚሰራ (periodic) የማህበረሰቡን አስተያየት የሚለካ ሰርቬይ እየተሰራ አይደለም።

- **ለሚዲያ እና ለህዝብ የሚቀርብ ሪፖርት፦** የፍርድ ቤትን ተዓማኒነት ለማግኘት ፍርድ ቤቶች የሚሰሩት ስራ በሕዝቡ ዘንድ መታወቅ አለበት። በዚህ ረገድ በ2012 ዓ.ም አንድ ክንውን ለማዘጋጀት የተቻለ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ በስርዓት ለማህበረሰቡና ለሚዲያ የሚያቀርበው አመታዊ ሪፖርት (state of the judiciary report) እስካሁን መደበኛ ስርዓት የሌለው፣ ያልተሰራበት እና ትኩረት የሚፈልግ ጉዳይ ነው።

- **ጉዳዮችን በሚዲያ ማስተላለፍ፦** የሌሎች አገራት ልምድ እንደሚያሳየው በህግ ገደብ ባልተጣለባቸው ጉዳዮች ችሎቶችን በቀጥታ ስርጭት ማስተላለፍ ማህበረሰቡ በፍርድ ቤት ላይ ያለውን አመኔታ ለማጠናከር አስተዋጽዖ ያበረክታል። ይህ ስርዓት በፍርድ ቤት ላይ ያሉ የተዛቡ መረጃዎችን በማስቀረት የፍርድ ቤቶችን አሰራር ለህዝብ ለማስተዋወቅ የሚያግዝ ከመሆኑም በላይ ዳኞች በከፍተኛ ሥነ ምግባር እና ሕግን በተከተለ መልኩ ተግባራቸውን እንዲያከናውኑ ይረዳል።

- **ግልጽ ችሎትና የመገናኛ ብዙኃን አዘጋገብ መመሪያና ስልጠና አለመኖር፦** ለህዝብ ግልፅ የሆነ ችሎት በመሰረቱ ለሚዲያም ግልፅ የሚሆን ቢሆንም በተወሰነ ጉዳይ ላይ ዳኝነት በዝግ ችሎት ሊካሄድ ይችላል። በተወሰነ ደረጃም (ለምሳሌ፣ የካሜራ አጠቃቀም፣ የሚቀረጽ/የማይቀረፅ ጉዳይ፣ የሕጻናት ጉዳይ ወዘተ) ላይ የአዘጋገብ ገደብ ሊደረግ ይችላል። ይህ ዝርዝር ጉዳይን የሚመለከት በመሆኑ መመሪያ ያስፈልገዋል። ይሁን እንጂ በዚህ ረገድ የወጣ መመሪያ የለም።

- **ማህበረሰቡን በቀጥታ ማግኘት** (outreach)፦ በፍርድ ቤቶች አመራር፣ በዳኞችና የፍርድ ቤት ሰራተኞች አማካኝነት ለሕብረተሰቡ የሲቪክ ትምህርት መስጠትና ስለፍርድ ቤት አሰራር ግንዛቤ የማኅልበት ጉዳይ እንዲሁም የፍርድ ቤትን አሰራር በተለያዩ መድረኮች፣ በበራሪ ወረቀቶች እና መሰል ተግባራት ለህብረተሰቡ ማድረስ የተለመደ አይደለም። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከትምህርት

ሚንስቴር ጋር በተደረሰው ስምምነት መሰረት የተጀመረውን የሲቪክ ትምህርትን ጨምሮ ሌሎች አማራጮችንም በመጠቀም ፍርድ ቤቱ ወደ ህዝቡ የሚደርስበትን ዕድል ማስፋት ያስፈልጋል።

- **የኮሚዩኒኬሽን ስትራቴጂ አለመኖር፦** የኮሚዩኒኬሽን ስትራቴጂ እና መመሪያ በፍርድ ቤቱ ሊኖሩ የሚገባቸውን የህዝብ ግንኙነት፣ የፍርድ ቤቶች መረጃ አሰጣጥ ሂደት፣ አስፈላጊውን ስልጠና ወዘተ . . . ከማስቀመጥ አኳያ ፋይዳ አላቸው። በረቂቅ ደረጃ የሚገኘውን የፍርድ ቤቱ ኮሚዩኒኬሽን ስትራቴጂ የፍርድ ቤትን አመኔታ ከመገንባት አንጻር ፋይዳው ከፍተኛ በመሆኑ በፍጥነት አጽድቆ መተግበር ያስፈልጋል።

## 1.2.5. የፌደራል ፍርድ ቤቶች የአቅም ሁኔታ

በስትራቴጂያዊ ዕቅድ ዝግጅት ወቅት የሚካሄድ የአቅም ክፍተት ትንተና የተቋም ጥንካሬና ድክመትን ለመለየት የሚያስችል ወሳኝ ጥናት ነው። በሌላ በኩል ጥናቱ ስትራቴጂን ከተቋማዊ አቅም ጋር አስማምቶ ለመቅረጽም ጠቀሜታው የጎላ ነው። የፌደራል ፍ/ቤቶች የአቅም ክፍተት ትንተና ፍርድ ቤቶቹ ባላቸው የአቅም ጥንካሬና ክፍተት ላይ የሚያተኩር ሲሆን ዋና ዋና ጭብጦቹም የአመራር፣ የፖሊሲና ስትራቴጂ እና በሀብት አስተዳደር ላይ ያሉ አቅሞች/ብቃቶች ናቸው።

### 1.2.5.1. የአመራር ብቃት

አመራሩ ለልህቀትና ቀጣይነት ላለው መሻሻል ያለው ቁርጠኝነት ሲታይ ለምሳሌ ያህል ተልዕኮ፣ እሴቶችና ራዕይን በመቅረጽና በማጋራት ረገድ አዲሱ የሪፎርም አመራር ከመጣ ካለፉት ሦስት ዓመታት ወዲህ “የህዝብ አመኔታ” ማግኘት የራዕዩ ማዕከላዊ ጭብጥ እንዲሆን አድርጓል። በሌላ በኩል ራዕዩን ወደ ኦፕሬሽን ከማሸጋገር ወይም ሥራዎችን በስትራቴጂያዊ ዕቅድ ከመምራት አንጻር አመራሩ ከነባሩ ስትራቴጂያዊ ግቦች የተመረጡ ግቦች ጋር የተሳሰሩ የሦስት ዓመት ማስፈጸሚያ ፕሮግራሞችን ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛል። የበላይ አመራሩ የፍርድ ቤቶች ማሻሻያ ፕሮግራሞችን በመቀየስ፣ በማደራጀትና በመምራት ረገድ ቁርጠኝነትና ብቃት የታየበት እርምጃ ወስዷል። በሌላ በኩል ከአመራር ጋር ተያይዘው ትኩረት ሊሰጥባቸው የሚገቡ የሚከተሉት ነጥቦች አሉ።

- የፍርድ ቤቶቹ እሴቶች ከአሠራር እና አደረጃጀት ሥርዓት ጋር በአግባቡ አለመተሳሰራቸው እና ጠንካራ የተጠያቂነትና የዲሲፕሊን ሥርዓት ገና ያልዳበረ በመሆኑ እሴቶች በበቂ ሁኔታ የአመራሩና የሠራተኛው የየዕለት ባህሪ ሊሆኑ አልቻሉም፤
- ቁልፍ እሴቶችን በማስረጽ የፍርድ ቤቶችን ባህል መቀየር በጣም ፈታኝና ጊዜ የሚጠይቅ ተግባር በመሆኑ በአመራሩ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነው። ሆኖም የፍርድ ቤቶችን ባህል ለመለወጥ በተጠና፣ በተሟላና ስትራቴጂያዊ በሆነ መልኩ ስራዎችን ማከናወን ላይ ክፍተት ይታያል፤
- ስልታዊና ዘወትራዊ በሆነ መልኩ ስራዎችና ሰራተኞችን የመጎብኘትና የማነቃቃት ባህል አልዳበረም፤
- ፍርድ ቤቱ ሰፊ የሪፎርም ስራ ላይ እንደመሆኑ ግልጽ የሥራዎች ቅደም ተከተል አሰጣጥ

ስርዓት አልዳበረም፤

- ለጊዜው የጋራ ውሳኔዎችን ለማሳለፍ እንቅፋት ባይሆንም በአመራር አካላት መካከል በአንዳንድ ቁልፍ ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ላይ የጋራ አቋም አለመኖርና ተናቦ የመስራት ብቃት ጉድለት ይታያል፤
- የተደራሽ ቢሮ (ኦፕን ዶር) ፖሊሲና አሠራር በተሟላ ሁኔታ አልተዘረጋም፤
- የተሟላ የአስተዳደራዊ ኮሙኒኬሽን ሥርዓት አልተዘረጋም፤

### 1.2.5.2. የፌደራል ፍርድ ቤቶች ፖሊሲና ስትራቴጂ

የፌደራል ፍርድ ቤቶች አመራር ፖሊሲዎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ለማሟላት፣ ለማዘመንና ወቅታዊነታቸውን ለመጠበቅ ከፍተኛ ጥረት እያደረገ መሆኑን ባለፉት ሦስት ዓመታት ከወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መገንዘብ ይቻላል። በተለይ ከተሻሻለው የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ጋር በተያያዘ ብዛት ያላቸው ደንቦችና መመሪያዎች በመዘጋጀትና በመውጣት ላይ ይገኛሉ። ሆኖም ከአዋጁ ጋር የተገናኙ የተለያዩ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ማዘጋጀትና ማውጣት የፌደራል ፍርድ ቤቶች ቁልፍ ተግባር ሆኖ መቀጠሉ አይቀርም። ከዚህ አንጻር የሚከተሉት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና መመሪያዎች በሁሉም ፍርድ ቤቶች ተሟልተው አልተገኙም ።

- ሁሉን አቀፍ የሆነ የዳኝነት ፖሊሲ
- የተቀናጀ የአስተዳደር ሠራተኞች የሰው ሀብት ፖሊሲ ስትራቴጂና መመሪያ
- ፍርድ ቤት አቀፍ የሥልጠናና የሰው ሀብት ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ
- የዕውቀት ሥራ አመራር ሥርዓት
- የሰው ሀብት መረጃ ሥራ አመራር ሥርዓት
- የተተኪዎች ማፍሪያ ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና መመሪያ
- የኮሙኒኬሽን ፖሊሲና ስትራቴጂ
- የጥናትና ምርምር ፖሊሲና ስትራቴጂ
- የብዝኃነትና አካታችነት ፖሊሲና ስትራቴጂ
- የአገልግሎት ስታንዳርድና ቻርተር

### 1.2.5.3. የፌደራል ፍርድ ቤቶች የኃብት ሥራ አመራር

#### የፍርድ ቤቶች አደረጃጀት

አደረጃጀት ሀብት በአግባቡ በመጠቀም የተቋም ራዕይና ተልዕኮን ለማስፈጸም የሚያገለግል የሥራ አመራር መሳሪያ ነው። አሁን በሥራ ላይ ያለው አደረጃጀት በ2010 ዓ.ም የተዘጋጀና ተግባራዊ የተደረገ ቢሆንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተጀመሩ የሪፎርም እሳቤና የተዘረጉ ፕሮግራሞችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የተሟላ አደረጃጀት ፈጥሯል ለማለት አስቸጋሪ መሆኑን ከተደረጉ ውይይቶች ለማወቅ ተችሏል። የ2010 ዓ.ም የአደረጃጀት ለውጥ ነባሩ አደረጃጀት የፈጠረውን ችግር በከፊል

ለመፍታት ያለመ እንጂ የአሁኑን የሪፎርም ሃሳብ ሙሉ በሙሉ ለማስፈጸም የሚያስችል አልነበረም። እንዲህም ሆኖ የአደረጃጀት ጥናቱ ተግባራዊ የሆነው በከፊል ነው። በመሆኑም ፍርድ ቤቶች ከአደረጃጀት አንጻር የሚከተሉት ክፍተቶች ትኩረት የሚያስፈልጋቸው ናቸው።

- አደረጃጀቱ ስትራቴጂውን መሠረት አድርጎ የተዘጋጀ አለመሆኑ፣ በመሆኑም የተሟላ የስትራቴጂና ፕሮግራም ማስፈጸሚያ መሳሪያ ሆኖ ሊያገለግል አልቻለም፤
- ሥራዎች ተፈጥሯዊ ፍሰታቸውን ጠብቀው አልተደራጁም፤
- በአንዳንድ የሥራ ክፍሎችና የሥራ መደቦች መካከል የተግባርና ኃላፊነት ድግግሞሽ ይታያል፤
- የሥልጣን ውክልና ሥርዓት ባለመዘርጋቱ አንዳንድ ሥራዎች በተማከለ ሁኔታ ተደራጅተዋል፤
- ምድብ ችሎቶች በተሟላ የሥራ መደብና ሠራተኛ አልተደራጁም፣
- የሥራ መደቦች ምዘና፣ ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም የሥራ መደቡ ለዳኝነት ሥራ ካለው ፋይዳ አንጻር በጥንቃቄ የተለየና የተቀረጸ አይደለም።

## የሰው ሀብት ሥራ አመራር

በፌደራል ፍርድ ቤቶች ከሰው ሀብት (ዳኞችና ሌሎች ሰራተኞች) አስተዳደርና ልማት ጋር ተያይዞ ሰፊ የማሻሻያ ስራዎች እየተሰሩና አበረታች ውጤቶችም እየተመዘገቡ ይገኛሉ። ዋና ዋናዎቹም፦

- የሰው ኃይሉን ለአንድ ዓላማ አቀናጅቶ ለመምራት እንዲቻል የሲቪል ሰርቪስ ሰው ሀብት አስተዳደር ስምሪት ለፍርድ ቤቶቹ መሰጠቱ፣
- የዳኞች ደመወዝና ጥቅማጥቅም እንዲሻሻል መደረጉ፣
- የሰው ሀብቱ በተጠኑ ፖሊሲዎችና መመሪያዎች እንዲመራ የተከናወኑ የጥናት ሥራዎችና የወጡ መመሪያዎች፤
- ዳኞች የድህረ ምረቃ ትምህርታቸውን እየሠሩ እንዲማሩ ዕድል መፈጠሩ፣ ሆኖም የትምህርት ዕድሉ በሁሉም ደረጃ መስፋት የሚኖርበት መሆኑ፤
- የሥራ ቦታዎችንና አካባቢዎችን ለማሻሻል የተወሰዱ እርምጃዎችና የተገኙ ውጤቶች መኖራቸው፤ ለምሳሌም የቢሮ ማሻሻያ፣ የሥራ መሳሪያዎች አቅርቦት ማሻሻያ፣ የቢሮ መገንቢያ በጀት ማስፈቀድ፣ የችሎት አዳራሽ ስታንዳርድ መዘጋጀቱ ወዘተ . . . ፤
- የዳኞች የአፈጻጸም ምዘና መመሪያ መዘጋጀቱ፤
- የዳኞች የሥነ ምግባር ደንብ ተሻሽሎ መውጣት፤
- የችሎቶችንና የዳኞችን ቁጥር በተለይ በመጀመሪያና ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ለማሳደግ የተደረገው ጥረትና የተገኙ ውጤቶች ተብለው ሊጠቀሱ ይችላሉ።

## የፋይናንስ እና ንብረት ሥራ አመራር

የፌደራል ፍርድ ቤቶች በጀት ከቅርብ አመታት ወዲህ በጉልህ እያደገ የመጣ ቢሆንም አሁንም ከአገራዊ በጀትም ሆነ ፍርድ ቤቶቹ ስራቸውን በአግባቡ ለማከናወን ከሚያስፈልጋቸው ሀብት አንጻር ሲታይ በጣም

ዝቅተኛ ነው። ፍርድ ቤቶች የሚመደብላቸውን በጀት የሚያስተዳድሩት በመንግስት የፋይናንስና የግዥ መመሪያዎች መሠረት መሆኑ አግባብነት ያለው ቢሆንም ፍርድ ቤቶቹ የሚመደብላቸውን በጀት በራሳቸው መደልደልና ማስተዳደር አለመቻላቸው የዳኝነት ነፃነት ጥያቄ ከማስነሳቱ በተጨማሪ የፋይናንስ አስተዳደር ቅልጥፍና ላይ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተጽእኖ ይኖረዋል። በጥቅሉ ከፋይናንስና ግዥና ንብረት ሥራ አመራር ጋር ተያይዞ የሚከተሉት ዋና ዋና ተግዳሮቶች ይስተዋላሉ።

- በቂ በጀት የማይመደብ መሆኑና የፌደራል ፍርድ ቤቶች የሚያመነጩትን ገቢ ቢያንስ በተዘዋዋሪ ፈንድ መልክ እንዲጠቀሙበት አለመደረጉ፤
- በዳኝነት ሥራና በኃላፊነት ቦታ የሚገኙ ሥራ መሪዎች የፋይናንስ ግዥና ንብረት ሥራ አመራር ዕውቀትና ክህሎት ዝቅተኛ መሆኑ፤
- የፋይናንስ ባለሙያዎች የተቀናጀ የፋይናንስ ሥራ አመራር መረጃ ሥርዓትን (IFMIS) በመተግበር ረገድ ያጋጠሟቸው ተግዳሮቶች በወቅቱ አለመፈታት፤
- የፋይናንስ አሰባሰብና አጠቃቀም ላይ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ስጋቶች አለመለየታቸው፣ አለመመዘናቸውና ወሳኝ ስጋቶችን ለመቀነስ በዕቅድ ላይ የተመሠረተ እርምጃ አለመወሰዱ፤
- የልዩ ልዩ ንብረቶች ጥገና የሚከናወነው ሲያመችና በዘመቻ መልክ መሆኑ ንብረትን በዕቅድ የመንከባከብና የመጠገን ዘላቂ አሠራር አለመኖሩን የሚያሳይ መሆኑ፤
- ውስን ቢሆንም በአንዳንድ ምድብ ችሎቶች በቀላሉ ተጠግነው አገልግሎት ሊሠጡ የሚችሉ ንብረቶች ያለአገልግሎት መቀመጣቸውና በምትካቸውም አዲስ የሚገዛ መሆኑ፤
- የፕሮክዩርመንት ዕቅድ በገበያ የዋጋ ጥናት ላይ ተመስርቶ የሚዘጋጅ ባለመሆኑና የብር ግሽበትና ምንዛሬ ምጣኔን በአግባቡ መተንበይ የሚሳነውና በዋጋ ዕቅድና በትክክለኛ ዋጋው መካከል በሚፈጠር ክፍተት የግዥ መጓተትንና መሰረዝን የሚያስከትልበት ሁኔታ መኖሩ፤
- ፕሮክዩርመንት በዕቅድ የማይመራና የዘርፉ ዕውቀትና ክህሎት በሚገባው ደረጃ አለመዳበር፣ ግዥና አቅርቦት ቀልጣፋና ውጤታማ እንዳይሆን ማድረጉ፤
- የግዢ ስርአት የማዕቀፍ ግዥ ፍላጎትን መሠረት የማያደርግ ከመሆኑም በላይ ጥራትን የማያይና የሚዘገይ መሆኑ፤
- የንብረት/የማቴሪያል አያያዝና አጠቃቀም ኮምፒዩተርን መሠረት ባደረገ የመረጃ ሥርዓት የማይመራ በመሆኑ ንብረቶች ለብክነት ተጋላጭ እንዲሆኑና ተደራሽም እንዳይሆኑ ማድረጉ፤
- የንብረት አስተዳደርና ቁጥጥር በቴክኖሎጂ የሚታገዝ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ አለመሆን፤
- የፕሮክዩርመንትና ንብረት አስተዳደር ፖሊሲዎችና መመሪያዎች በሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በአግባቡ የማይታወቁ መሆናቸው የአፈጻጸም ጥራትንና ቅልጥፍናን የሚጎትት መሆኑ፤
- የንብረት ማከማቻና መሰራጫ ሥርዓት በአግባቡ ያልተደራጀ መሆኑ የንብረት አጠቃቀምን ቅልጥፍናና ውጤታማነት የሚጎዳ መሆኑ ሊጠቀሱ ይችላሉ።

## የኢንፎርሜሽ ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ሥራ አመራር

የፌደራል ፍርድ ቤቶች የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ (ኢኮቴ) አጠቃቀምን በተመለከተ ኢኮቴን ለዳኝነት አገልግሎት ማዋል የተጀመረው ከሃያ ዓመት በፊት ሲሆን እንደ አጀማመሩ እየዘመነ የሄደ አይደለም፡፡ ሆኖም የሪፎርም አመራሩ የፍርድ ቤቶችን የኢኮቴ አጠቀቃቀም በዝርዝር በማስጠናት ሰፊ የኢኮቴ የማሻሻያ ፕሮግራሞችን ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ በሌላ በኩል የፌደራል ፍርድ ቤቶች የኢኮቴ ሥርዓትና አጠቃቀም የሚከተሉት ክፍተቶች አሉበት፡፡

- የኢኮቴ አቅምን ሙሉ በሙሉ አለመጠቀም፤ ለምሳሌ ያህል የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር ሥርዓት ኢኮቴን የመጠቀም ብቃት ውስን ሲሆን አብዛኛው የአገልግሎቱ ባህሪያት ተግባራዊ አልሆኑም፤
- የጥሪ ማዕከላት ቴክኖሎጂ ጊዜው ያለፈበት መሆኑ፤
- የፌደራል ፍ/ቤቶች የልህቀት ሥራ አመራር ሞዴል የሚጠቀሙ ባለመሆናቸው የላቁና ውጤታማ ቴክኖሎጂዎችን ለመጠቀም አለመቻሉ፤
- የኢኮቴ አጠቃቀም በሁሉም ደረጃ ባሉ ፍርድ ቤቶች ዝቅተኛ ሲሆን በተለይ በከፍተኛና በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች ደግሞ በእጅጉ ዝቅተኛ መሆኑ፤
- የፌደራል ፍርድ ቤቶች ማዕከላዊ የመረጃ ቋት የሌላቸው መሆኑ፤ በተለይም ምድብ ችሎቶች የራሳቸው የሆነ አመቺ ቢሮ የሌላቸው በመሆኑ የመረጃ ቋቶችን ለማደራጀት ተግዳሮት መሆኑ፤
- የኤሌትሮኒክስ ፋይሊንግ ሥርዓት አገልግሎትን በተገቢው መንገድ አለመስፋፋቱ፤
- በሥራ ላይ ያለው ኤስ.ኤም.ኤሲ አገልግሎት ቴክኖሎጂ ጊዜው ያለፈበት በመሆኑ ምርጥ ተሞክሮዎች ላይ በመመስረት መሻሻል የሚገባው መሆኑ፤
- ራንደም ኬዝ ድልድል የጉዳዮችን ክብደት መሠረት ማድረግና ከጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር ጋር ማቀናጀት የሚገባ መሆኑ፤
- የራንደም ኬዝ ድልድል ሥርዓትን በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች ችሎቶች ማስፋፋት፤ የጉዳዮች ምደባ ንኡሳን ስፔሻሊቲዎችን የማይከተል በመሆኑ የተለየ ክህሎት የሚፈልጉ ጉዳዮችን በልዩ ሁኔታ የማያይ መሆኑ፤
- የተዘጉ መዝገቦች በአብዛኛው ዲጂታይዝድ አለመሆናቸው፤
- የመረጃ ቋት ሠራተኞችና የኢኮቴ ባለሙያዎች የአቅም ክፍተት መኖር፤
- የፍርድ ቤቶች ኢኮቴ ሥርዓት ለዳኞችና ለአመራሩ ተፈላጊውን መረጃ በጥራትና በጊዜው የማይሰጡ መሆናቸው፤
- የቪዲዮ ኮንፈረንሲንግ ሥርዓት የሚቋረጥበት ጊዜ በብዛት መኖሩ፤
- ለመደበኛውም ስራ ቢሆን የኤሌትሪክ ኃይል መቆራረጥና ተተኪ የኃይል ምንጭ አለመኖር፤
- በርካታ ዳኞች በጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር አለመሰልጠናቸው፤
- የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር ዳኞች የሚፈልጉትን ስታትስቲካዊ መረጃ የማይሰጥ መሆኑ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

የፍርድ ቤቶችን ውስጣዊ ጥንካሬና ድክመቶች ለይቶ ቀጣይ አቅጣጫዎችን ለመቀየስ የተለያዩ ማዕቀፎችን መሰረት በማድረግ በተካሄደ የዳሰሳ ጥናት የተለዩ ግኝቶች በሚቀጥለው ሰንጠረዥ ተጠቃልለው ቀርበዋል፡፡

| ጠንካራ ጎኖች | ድክመቶች |
|---|---|
| • ሰፊ የሆነ ፍርድ ቤቶችን የማሻሻል ሥራ እየተተገበረ መሆኑና ለውጥን እውን ለማድረግ ቁርጠኛና ያላሰለሰ ጥረት የሚያደርግ አመራር መኖር፣<br>• በስትራቴጂያዊ ዕቅድ ማዘጋጀት እና ትግበራ ላይ ልምድ መኖር፣<br>• በፍርድ ቤቶች የዳኝነት ነፃነት ተግባራዊነትን ለማሳደግ አበረታች እርምጃ እየተወሰደ መሆኑ (በጀት በቀጥታ ለፓርላማ ማቅረብ፣ የአስተዳደር ሰራተኞችን በቀጥታ ማስተዳደር የመሳሰሉ)፣<br>• የሕግ ማዕቀፎች መሻሻላቸው፣ የአሰራር ስርዓትን ለማሻሻል ብዛት ያላቸው ደንቦችና መመሪያዎች የተዘጋጁ ወይም እየተዘጋጁ መሆኑ፣<br>• የፌደራል ፍርድ ቤቶች የአዲስ አበባና የድሬደዋ ምድብ ችሎቶችን ጨምሮ በመጠኑ የዳበረ አደረጃጀት ያላቸው መሆኑ፣<br>• የተጠያቂነት ሥርዓት በበቂ ሁኔታ አለመዳበር፣<br>• ኢኮቴ አጠቃቀምን በማስፋፋት የፍርድ ቤቶችን አሠራር ቅልጥፍና እና ጥራት ለማሳደግ የሚያግዝ ከፍተኛ ትኩረት መኖሩና ፕሮግራም ተቀርጾ ወደ ስራ መገባቱ፣<br>• የጾታ እኩልነት ላይ ያሉ መሻሻሎች (የሴት ዳኞችና አመራሮች መጨመር፣ የጾታዊ ትንኮሳ ላይ ፖሊሲ መውጣቱ)፣<br>• የረዥም ጊዜ ልምድ ያላቸው ዳኞችና ሠራተኞች መኖራቸው፣ | • የፌደራል ፍርድ ቤቶች በክልሎች ያላቸው አደረጃጀትና ተደራሽነት አነስተኛ መሆን፣<br>• ጥራትን፣ ቅልጥፍናንና የፍርድ ቤቶቹን አጠቃላይ አሰራር ለመለካት የሚያስችሉ በቂና ግልጽ መመዘኛዎችና ደረጃዎች ያለመኖር፣<br>• የፌደራል ፍርድ ቤቶች በአገር፣ በአህጉር እና በአለም አቀፍ ደረጃ ካሉ አግባብነት ካላቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ያላቸው ግንኙነትና አጋርነት አለመጠናከር፣<br>• የፍርድ ቤቶችን አሰራር እና በጎ ገጽታ አጉልቶ የማሳየት ልምድና የኮሙኒኬሽን ሥራዎች በበቂ ሁኔታ አለመዳበር፣<br>• ለቅልጥፍና ተግዳሮት የሆኑ በቀላሉ ሊፈቱ የሚችሉ ጉዳዮች በቂ ትኩረት አለማግኘታቸው፣<br>• ጥራትን ለማረጋገጥ የተጠናከረ ስርዓት አለመበጀቱ (የውሳኔ ትንተና፣ የጠበቆች/ተገልጋዮች ሰርቬይ፣ የፍርድ ምርመራ/ኦዲት)፣<br>• ለጥራት እና ለቅልጥፍና አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎች በበቂ ሁኔታ አለመዘርጋታቸው (በጉዳዮች የተለዩ ችሎቶች፣ አማራጭሙግት መፍቻ፣ መዝገብ አያያዝ ማዘመን)፣ የሥነ ምግባር እና ሙስና ጉዳዮች ላይ በበቂ ሁኔታ ሰው/ተገልጋይ ተኮር አለመሆን፣ የአገልጋይነት መንፈስ አለመዳበር፣<br>• የተጠናከረ የጥናት፣ ምርምርና የዕውቀት አስተዳደር ስርዓትና አደረጃጀት አለመኖር፣<br>• በጥራት እና በቅልጥፍና ለመፈፀም የሚያስችል የዳኞችና የሰራተኞች የዕውቀትና የክህሎት ውስንነት፣<br>• የተሟላ የዳኞች/ሰራተኞች የስልጠናና የአቅም ግንባታ ስርዓትና አደረጃጀት አለመኖር፣ |

| ጠንካራ ጎኖች | ድክመቶች |
|---|---|
| • እየተሻሻለ የመጣ የትምህርት ዕድል መኖሩ፣<br>• ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተሻሻለ የመጣ የፍርድ ቤቶችን ስራ የማስተዋወቅና አጋርነትን የመገንባት ጥረት መኖሩ፣ | • የፌደራል ፍርድ ቤቶች አደረጃጀት የተለጠጠ፣ ተደራራቢና በውል ልዩነታቸው ያልተቀመጡ የስራ ክፍሎች የያዘ ቅልጥፍናና ውጤታማነት ከማረጋገጥ አንጻር ክፍተት ያለው መሆኑ፣<br>• የተጠናከረና የተሟላ የክትትል እና የግምገማ ማዕቀፍ አለመኖርና በሥርዓቱና ሳያሰልስ የሚከናወን አለመሆኑ፣<br>• የሀብት ማሰባሰብ፣ የበጀት ዝግጅትና አስተዳደር አቅም ውስን መሆን፣<br>• የፕሮጀክት ጽነሳ፣ አስተዳደር እና ክትትል ጠንካራ ስርዓት አለመኖር፣<br>• ለተገልጋይና ተደራሽና ምቹ እንዲሁም ለሰራተኞች ምቹ ያልሆኑ የስራ ቦታዎችና መገልገያዎች፣<br>• አሠራሮች በሚገባው መጠንና ፍጥነት በኢኮቴ አለመደገፋቸው፣<br>• ለተገልጋይና ተደራሽና ምቹ እንዲሁም ለሰራተኞች ምቹ ያልሆኑ የስራ ቦታዎችና መገልገያዎች፣<br>• የሀብት ማሰባሰብ፣ የበጀት ዝግጅትና አስተዳደር አቅም ውስን መሆን፣<br>• የፕሮጀክት ጽነሳ፣ አስተዳደር እና ክትትል ጠንካራ ስርዓት አለመኖር፣<br>• አሠራሮች በሚገባው መጠንና ፍጥነት በኢኮቴ አለመደገፋቸው፣ |

## 1.3. የፖለቲካ፣ ኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ፣ ቴክኖሎጂያዊ፣ አካባቢያዊና ህጋዊ ሁኔታዎች ትንተና

ስትራቴጂክ ዕቅዱን ለማዘጋጀት የሚስፈልጉ ግብዓቶችን ለማሰባሰብ በተካሄደ ዳሰሳ ከተለዩ ውስጣዊ ጥንካሬዎችና ድክመቶች በተጨማሪ በዳኝነት አገልግሎት ዙሪያ ሊኖሩ የሚችሉ ውጫዊ መልካም አጋጣሚዎችና ስጋቶችን መለየት ያስቻለ ዳሰሳ ተካሂዶ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ፣ የቴክኖሎጂ የሕግ ሁኔታዎች ቅኝትና ትንተና ተካሂዶ ለቀጣዩ ስትራቴጂያዊ ዘመናት የሚያስከትሉዋቸውን አዎንታዊና አሉታዊ ተጽዕኖዎች ለመለየት ተሞክሯል።

**ፖለቲካዊ ሁኔታ፦** ኢትዮጵያ ፖለቲካ ሁኔታ መሰረታዊና ሰፊ የለውጥ ሂደት ላይ ያለ እንደመሆኑ

ያለመረጋጋትና ተገማች ያለመሆን ባህሪ ይታይበታል። በአንድ በኩል የፖለቲካ ምህዳሩን ለማስፋት፣ የዳበረ ዲሞክራሲና የህግ የበላይነትን የተጠያቂነትን እሴቶች ለመገንባት የሚያስችሉ ሰፊ የለውጥ ስራዎችና ዕድሎች አሉ። በከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎች በየጊዜው የሚሰጡ መግለጫዎችና መመሪያዎች የህግ የበላይነትና የፍርድ ቤቶች ነጻነትን አጉልቶ የሚያሳይ መሆኑ ከፍተኛ ተስፋ የሚያጭር አዲስ ክስተት ነው ሊባል ይችላል። ሆኖም አስፈጻሚው በፍርድ ቤቶች ላይ ያሳደረው የቆየ ተጽእኖ በተለይም ደግሞ በሀብት፤ በፕሮቶኮልና በህዝብ ግንዛቤ የሚገለጽ ስለሆነ ይህንን ሁኔታ ለማስተካከል ረዘም ያለ ጊዜና ትኩረት ያለው እንቅስቃሴ ይጠይቃል። በሌላ በኩል ከፍተኛ የሆነ ጽንፈኝነትና ከዚህም ጋር ተያይዞ የፖለቲካና የማንነት ልዩነቶችን መሰረት ያደረጉ ግጭቶችና መፈናቀሎች በሰፊው እየተከሰቱ ይገኛሉ። እነዚህ ፖለቲካዊ ክስተቶች ውስብስብ ጉዳዮች ወደ ፌደራል ፍርድ ቤቶች እንዲመጡ ከማድረጋቸው በተጨማሪ የፍርድ ቤቶቹን ገለልተኝነትና አመኔታ ጥያቄ ውስጥ ያስገባሉ። በሚዲያ ዘርፍ እያደገ የመጣው ነጻነት በፍርድ ቤት ውሎና አስተዳደር ዙርያ የመዘገብንና ትችት የማድረጉን ሁኔታ የሚያሰፋ ስለሚሆን ጥንቃቄ የሚሻ የመሆኑን ያክል በሌላ በኩል ሚዲያውን በአዎንታዊ መልክ ለግንዛቤ መዳበርና ለበጎ የገጽታ ግንባታ ጥቅም ላይ የማዋል ዕድል አስፍቷል።

**ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ፦** የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ባለፉት ዓመታት ፈጣን የሚባል ዕድገት ሲያስመዘግብ ቆይቷል። ይህ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት በረዢሙ ጊዜ እንደሚቀጥል ቢገመትም በሚቀጥሉት ጥቂት አመታት ግን ኢኮኖሚው የመቀዛቀዝ ሁኔታ ሊያጋጥመው ይችላል። በከፊል ከዚህ ጋር በተያያዘ እና ከኢኮኖሚ መዋቅራዊ ፈተና በሚመነጭ የስራ አጦች ቁጥር ይጨምራል፤ ተገቶ የነበረው የግሽበት ምጣኔ ያድጋል የሚሉ ተጨባጭ ስጋቶች አሉ። እነዚህ ስጋቶች የወንጀል ቁጥርን በማበራከትና በማወሳሰብ ረገድ የራሳቸው አሉታዊ ተጽእኖ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል። የኢኮኖሚው መቀዛቀዝና የመንግስት የበጀት ጉድለት ፈተናዎች ለፍርድ ቤት የሚመደበውን በጀት ከፍላጎት አንጻር አነስተኛ ስለሚያደርገው ፍርድ ቤቶች ያላቸውን ክፍተት ለመሙላት እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። ፍርድ ቤቶች የለውጥ እንቅስቃሴዎች በአግባቡ አስተናግደው የሚጠበቀውን ውጤት ለማግኘት ከለጋሽ ድርጅቶች የሚገኘውን ድጋፍ ማጠናከር የሚያስችል ፖሊሲና አሰራር መዘርጋት ይኖርባቸዋል። በአጠቃላይ የኢኮኖሚው ሊበራላይዝ መደረግ፣ የውድድር ስርአትና የሸማቾች መብት ትግበራ መሻሻል እንዲሁም የሀገሪቱ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት በመጪዎቹ ዓመታት ወደ ፍርድ ቤቶች የሚመጡ ጉዳዮችን እንዲጨምሩና በይዘታቸውም እንዲወሳሰቡ የሚያደርግ መሆኑ ይጠበቃል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ወደ ፍርድ ቤት የሚመጡ ተቋማትና ግለሰቦች አግባብነት ያለው ውሳኔ የማግኘት እምነታቸውን አጎልብተው ለተጀመረው የኢኮኖሚ ዕድገት የበኩላቸውን አስተዋጽዖ እንዲያበረክቱ የሚያደርግ ቀልጣፋ እና ተገማች የፍትህ አገልግሎት መስጠት ከፌደራል ፍርድ ቤቶች የሚጠበቅ ኃላፊነት ነው። በኢኮኖሚው እንቅስቀሴ ውስጥ የሚገጥሙ አለመግባባቶችን እና ፍርድ ቤት የሚቀርቡ ክርክሮችን እንደ ኢንቨስትመንት በመመልከት በአግባቡ ቀልጥፎ መፍታትም ይጠይቃል።

**ማህበራዊ ሁኔታ፦** የማህበረሰቡ ንቃተ ህግና የሰብአዊ መብቶች ግንዛቤ መጨመር ለፍርድ ቤቶች ለሚቀርቡ ክርክሮች ቁጥርና ውስብስብነት መጨመር የራሱ የሆነ አስተዋጽዖ አለው። ከፍተኛ የሕግ ትምህርት ተቋማት መበራከትን ተከትሎ በየዓመቱ እየጨመረ የመጣው የህግ ትምህርት ምሩቃን ቁጥር

መጨመር ለፍትህ ዘርፉ አቅም መጎልበት የራሱ በጎ አስተዋጽዖ ቢኖረውም ፍርድ ቤቶች ከህዝቡ ቁጥር መጨመር ጋር ተያይዘው ለሚቀርቡላቸው ማህበራዊ ችግሮች እልባት ለመስጠት የሚያስችል አቅም የመፍጠሩን ሥራ አጠናክረው መቀጠል እንደሚኖርባቸው እሙን ነው፡፡ የሕግ ትምህርት ቤቶች የሕግ ምሩቃንን በስፋት የሚያስመርቁበትን እድል በመጠቀም ፍርድ ቤቶች ከትምህርት ቤቶች ጋር ስምምነት ላይ በመድረስ ዳኞች ሊሆኑ የሚችሉ ተማሪዎችን በተለይም ሴት ተማሪዎችን አስቀድመው በመለየት በዚሁ እውቀትም ክህሎትም ይዘው እንዲወጡ የማድረግ እድልንም ይፈጥራል፡፡ ከዚህ ሌላ ሙስናን የመጸየፍ ባህል እየቀነሰ መምጣት፣ የተከራካሪነት ወኔ (litigiousness) አለመብረድ እንዲሁም ከዚህ ጋር ተይይዞ ለማህበራዊ ካፒታል የሚሰጠው ዋጋ እየቀነሰ መምጣቱ አንድ ላይ ክርክርን በተለይም የወንጀል ክርክርን የማበራከት አስተዋጽዖ አላቸው፡፡ በሌላ በኩል የከተሜው ቁጥር መጨመር የጉዳዮች አይነት ላይ የራሱ የሆነ ተጽዕኖ እንደሚያስከትል እሙን ነው፡፡ በማህበራዊ ጉዳይ ሌላ ታሳቢ መሆን ያለበት አሁን ላይ በህዝቡ እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ገደብ የጣለው የኮሮና ቫይረስ መስፋፋት እና ማህበራዊ እገዳዎች ፍርድ ቤቶች በተመሳሳይ እንዲህ አይነት አስከፊ ክስተቶች በሚኖርበት ጊዜ ሊገጥማቸው የሚችለውን የአገልግሎት መቆራረጥ ታሳቢ ባደረገ መልክ ከወዲሁ ሪፎርም ማድረግ እንዳለባቸው ሰፊ አስገንዛቢ ሁኔታ ነው፡፡

**ቴክኖሎጂያዊ ሁኔታ፦** በአለማችን ብሎም በሀገራችን ፈጣን የቴክኖሎጂ ለውጦች ይታያሉ፡፡ ፍርድ ቤቶች ይህንን ዕድል አሰራራቸውን ለማፋጠን፣ ወጪን ለመቀነስ እና የፍትህ አሰጣጡን ይበልጥ ለማሳለጥ ጥቅም ላይ ማዋል ይጠበቅባቸዋል፡፡ ቴክኖሎጂ በአጋዥነት ብቻ ሳይሆን የዳኝነት ስርአቱን በማዘመንና በማሻሻል ረገድ ቀጥተኛ የሆነ አስተዋጽዖ አለው፡፡ የፍርድ ቅልጥፍና ጥራት፣ ግልጽነት እንዲሁም ተደራሽነት ያለቴክኖሎጂ የሚታሰቡ አይደሉም፡፡ በተለይ የሞባይል ቴክኖሎጂ፣ የኬዝ አስተዳደር ቴክኖሎጂ፣ በኤሌክትሮኒክ መንገድ የማስቻል ስርአት፣ የቴሌኮምፒቲንግ አገልግሎት፣ የዲጂታላይዜሽን ቴክኖሎጂ እንዲሁም አርቴፊሻል ኢንተለጀንስና ወረቀት አልባ ስርአት የማይታለፉ የቴክኖሎጂ ትሩፋት ከመሆናቸውም በላይ በነዚህ መጠቀም ፈጣን ለውጥ ለማምጣት ሁነኛ መንገድ ነው፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን ቴክኖሎጂ የጥፋትና የፈተና ምንጭ የመሆን ዕድል ያለው መሆኑ በተለይም በሳይበር ጥቃትና ማህበራዊ ሚዲያን መሰረት ያደረጉ ወንጀሎች መበራከትና በዚህ ረገድ የማስረጃ ስርአት አለመዳበሩ ፍርድ ቤቶችን የሚፈታተኑ አዳዲስ ክስተቶች ናቸው፡፡

**አካባቢያዊ ሁኔታ፦** የሀገራችን ሁሉ-አቀፍ ዕድገት በአረንጓዴ የዕድገት ዘይቤ የሚመራ ነው፡፡ አገራችን በአረንጓዴ ለውጥ ቀዳሚ ከሚባሉ አገሮች ናት፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ብክለትን፣ የደኖች መራቆትን፣ የአፈር መሸርሸርን እና ሌሎች የተፈጥሮ መዛባቶችን ለመከላከል በርካታ ህጎች ወጥተዋል፡፡ ስለሆነም ፍርድ ቤቶች እንደ ተቋም ከዚሁ ጋር የተጣጣመ አሰራርን ማዳበር ይጠበቅባቸዋል፡፡ ለምሳሌም የአካባቢ ተስማሚነትን ስልት መንደፍ፣ የቆሻሻ አወጋገድ ስርአትን ማዘመን፣ ወረቀት አልባ አሰራርን ማዳበርና የስራ ቦታን አረንጓዴ ከማድረግ አንጻር ለዘላቂ ልማት ትርጉም መስጠት ያስፈልጋቸዋል፡፡ ከዚህ ሌላ ከህዝብ ብዛት ጋር በተዛመደና ከአካባቢያዊ ብክለት ጋር በተሳሰረ በርካታ ጉዳዮች ወደ ፍርድ ቤት ሊቀርቡ እንደሚችሉም ታሳቢ ማድረጉ ጠቃሚ ነው፡፡

**የህግ ሁኔታ፦** በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ከፍተኛ የሆነ የህግ ማውጣት ስራ የሚካሄድበት ወቅት ነው፡ ፡ ከተፈጠረው የሪፎርም አስተሳሰብ እና ለሪፎርም ዝግጁነትን ከማረጋገጥ አንጻር ህጎች እየተከለሱና በርካታ ማሻሻያዎች እየተደረጉ ይገኛሉ። በመሆኑም አፋኝና ገዳቢ ተብለው የሚታወቁት ህጎች በአሁኑ ጊዜ ከሞላ ጎደል ሁሉም በአዲስ ተተክተዋል። ከዚህ ሌላ ሰፊ ይዘት እንዳለው የሚታወቀው የንግድ ህግ ማሻሻያ ተደርጎበት በተወካዮች ምክር ቤት ጸድቆ ወጥቷል። ለመጀመሪያ ጊዜ የአስተዳደር ሥነ ሥርዓት ሕግ ጸድቋል። በአማራጭ የአለመግባባት መፍቻ ዘዴ ረገድ ኢትዮጵያ የኒውዮርክ የግልግል ዳኝነት ኮንቬንሽን መፈረምዋ አንድ ራሱን የቻለ ለውጥ እንደሆነ ተደርጎ ተወስዷል። በተመሳሳይም የፍርድ ቤትን ችግር ሊቀርፉ የሚችሉ የፍርድ ቤት አስተዳደር ሕጎች ወጥተዋል። እነዚህን ሕጎችም ለማስፈጸም የሚያስችሉ ደንቦችና መመሪያዎችም ወጥተዋል። የተሻሻሉ አዋጆችን ተግባራዊ ለማድረግ ወደፊትም እንደአስፈላጊነቱ የሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች ይኖራሉ። በዚህ መልኩ የወጡ ሕጎች የፍርድ ቤትን ውጤታማነት በማሳደግ ተቀባይነቱን ለማጎልበትና ተዓማኒነቱን ለማሳደግ የበኩላቸውን ሚና የሚጫወቱ ሲሆን ለፍርድ ቤቶቹም ተጨማሪ ደንቦችንና መመሪያዎችን ማውጣት እንዲችሉ ዕድል የሚፈጥሩም ናቸው።

በዳሰሳ በተለዩ የውጫዊ ሁኔታዎች ዳሰሳ ለቀጣዮቹ ስትራቴጂ ዘመናት ሊኖሩ ይችላሉ ተብለው የተለዩ መልካም አጋጣሚዎች እና ስጋቶች በሚቀጥለው ሰንጠረዥ ተጠቃልለው ቀርበዋል።

| ተ/ቁ | የትንተና ዕይታ | መልካም አጋጣሚዎች | ስጋቶች |
| --- | --- | --- | --- |
| 1 | ፖለቲካ | • ነጻ የዳኝነት አካል ህገ መንግስታዊ ዋስትና ያገኘ መሆኑና ይህንን ለመተግበር ተጨባጭ እርምጃዎች በመወሰድ ላይ መሆናቸው፤<br>• በከፍተኛ የመንግስት ሃላፊዎች በኩል ስለ የህግ የበላይነትና የፍርድ ቤቶች ነጻነት የሚሰጡት መግለጫዎችና የሚገቡት ቃሎች ለፍርድ ቤቶች ጥሩ ዕድሎች መሆናቸው፤<br>• በአገሪቱ እየተተገበረ ያለው የፖለቲካ ሪፎርም የፌደራል ፍርድ ቤቶችን ለማጠናከር ከፍተኛ ዕድል የሚሰጥ መሆኑ፤<br>• የሚድያ ነጻነት መስፋት በፍርድ ቤቶች ገጽታ ግንባታ ሊፈጥረው የሚችለው መልካም ዕድል መኖሩ፤<br>• በክልሎች አካባቢ የፌደራል ፍርድ ቤቶች እንዲደራጁ በክልሎቹ ያለው ፍላጎት የፌደራል ስርአትን ለማጠናር ከፍተኛ ዕድል መሆኑ፤ | • የመንግስትና የፖለቲካ ድርጅት መሪዎች ስለ ፍርድ ቤቶች ነጻነትና ገለልተኝነት ጠቀሜታ በተሟላ መልኩ ግንዛቤ የጨበጡ አለመሆናቸው አላስፈላጊ የሆነ ጣልቃ ገብነትንና አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል መሆኑ፤<br>• በህዝቡ በኩል ስለ ፍርድ ቤት ሚናና ድርሻ ያለው ግንዛቤ አነስተኛ መሆንና ፍርድ ቤቶችንና አስፈጻሚ መስሪያ ቤቶችን መለየት አለመቻሉ፣ አለዚያም ፍርድ ቤቶችን የበታች አድርጎ መመልከቱ፤<br>• በአገሪቱ የፖለቲካ ሥርዓት ዋልታ ረገጥነት የብሄራዊ መግባባትን በማደናቀፍ ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑና የፍርድ ቤትን ጫና ማብዛቱ፣ የፍርድ ቤት ገለልተኝነት እይታ ላይም የራሱን ጫና ማሳደሩ፤<br>• የብሄር ተኮርና ሌሎች ግጭቶች ለፌደራል ፍርድ ቤቶች የሚቀርቡ ጉዳዮችን ውስብስብነትና ብዛት የሚያሳድጉ ሲሆን በፍርድ ቤቶች ገለልተኝነትና መልካም ገጽታ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ መሆኑ፤<br>• ከጸጥታ ችግር ጋር ተያይዞ የኮንትሮባንድ እና የህገ-ወጥ ንግድ ሁኔታ በአሳሳቢ ደረጃ ሊጨምር የሚችል መሆኑ፤<br>• ለሴቶች፣ ወጣቶች እና አካል ጉዳተኞች የተሰጠው ከፍ ያለ ህጋዊ ከለላና የመብት ጥበቃ በርካታ ተጨማሪ ጉዳዮች ወደ ፍርድ ቤት እንዲመጡ የሚያደርግ መሆኑ፤ |

| ተ/ቁ | የትንተና ዕይታ | መልካም አጋጣሚዎች | ስጋቶች |
|---|---|---|---|
| 2 | ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች | • አገር በቀል የኢኮኖሚ ፖሊሲ እና የአሥር ዓመት የልማት ስትራቴጂ ዕቅድ መኖር የረዥም ጊዜ ዕድገትን ለማምጣት መሰረት ሊጥል የሚችል መሆኑ፣ በዚህ ረገድ ፍርድ ቤቶች የተነቃቃ እና ሳቢ ስራ ለመስራት ዕድል የሚሰጣቸው መሆኑ፤<br>• የልማት አጋሮች ከፌደራል ፍርድ ቤቶች ጋር ለመሥራት ከፍተኛ ፍላጎት እያሳዩ መሆኑ የፍርድ ቤቶችን የቴክኒክና የበጀት አቅም ሊያሳድግ የሚችል መሆኑ፤ | • በኮቪድ 19 ወረርሽኝና በሰላም እጦት ምክንያት የአገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት እየቀነሰ መምጣቱ ለፌደራል ፍርድ ቤቶች በቂ በጀት እንዳይመደብ የሚያደርግ መሆኑ፤<br>• ከፍተኛ የኑሮ ውድነትና የዋጋ ግሽበት መኖር ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው በጀት እንዳይጠናቀቁ የሚያደርግና ከፍተኛ ብቃት ያላቸውን ዳኞችና ሠራተኞችን ለማቆየት የሚያስቸግር መሆኑ፤<br>• ከግሽበት ጋር በተያያዘ ኢኮኖሚያዊ ሙስናና ወንጀሎች እየተወሳሰቡና እየሰፉ መምጣታቸው በፌደራል ፍርድ ቤቶች ላይ ከፍተኛ የሥራ ጫና ሊያስከትል የሚችል መሆኑ፤<br>• የውድድር ህግና የሸማቾች ጥበቃ እየተጠናከረ መሄድና የሊበራላይዜሽን ጉዳይ እየተጠናከረ መሄድ ውስብስብ ጉዳዮች ወደ ፍርድ ቤቶች እንዲመጡ የሚያደርግ መሆኑና ከዚህም የተነሳ የፍርድ ቤቶችን አቅም የሚፈትን ሁኔታ የሚያጋጥም መሆኑ፤ |
| 3 | ማህበራዊ | • በህግ ትምህርት መስፋፋት ምክንያት በርካታ የህግ ምሩቃን ገበያ ላይ የሚገኙ መሆኑ፤<br>• የሕዝብ ቁጥር መጨመሩ፣ ህብረተሰቡ የዳበረ ባህላዊ አማራጭ የግጭት መፍቻ ሥርዓት ያለው መሆኑ ጉዳዮችን በዚሁ አግባብ | • የህግ ትምህርትና ሥልጠናዎች በንድፈ ሃሳብ ላይ እንጅ በተፈላጊ ክህሎቶች እና አመለካከቶች ላይ የማያተኩሩ መሆናቸው የሚፈለገው ብቃት ያላቸው ምሩቃን ለመለየት የሚያስችል ሥርዓት አለመዘርጋቱ፣<br>• ደካማ የሥራ ባህል እና ሙያዊ ያለመሆን የፍርድ ቤቶችን ምርታማነትና ሥነ ምግባር የሚጎዳ መሆኑ፤ |

| ተ/ቁ | የትንተና ዕይታ | መልካም አጋጣሚዎች | ስጋቶች |
|---|---|---|---|
| | ማህበራዊ | በመፍታት የፍርድ ቤቶችን ጫና ለመቀነስ የሚያስችል መሆኑ፤<br>• የትምህርት መስፋፋትና የህግ ንቃት በመጠኑም ቢሆን እያደገ መምጣት፤<br>• ብቃት ያለውን ዳኛ አስቀድሞ መመልመል የሚያስችል ዕድል የሚፈጥር መሆኑ፤ | • ዓለም አቀፍ ወረርሽኝ የሆነው ኮቪድ 19 የሚያስከትለው ማህበራዊ ቀውስና በፍርድ ቤቶች ሥራ ላይ የሚያሳድረው አሉታዊ ተጽዕኖና ከዚህ ጋር ተያያዥ በሆነ መልኩ ተመሳሳይ ስራ ሊያስቆሙ የሚችሉ ክስተቶች ሊመጡ እንዲሚችሉ በቂ አመላካች መኖሩና ለዚህም ፍርድ ቤቶች በበቂ ሁኔታ የተዘጋጁ አለመሆናቸው፤<br>• የሴቶች ህጻናትና አካል ጉዳተኞች ሰብዓዊ መብቶችን በልዩ ሁኔታ ለማስከበር አገራዊ አቅም አለመፈጠሩ፤<br>• የሙስና መስፋፋትና ይህም በዳኝነት ጥራትና ቅልጥፍና ላይ የሚያስከትለው አሉታዊ ተጽዕኖ፤<br>• የህዝብ ብዛት መጨመር በፍርድ ቤቶች ላይ የስራ ጫና የሚጨምር መሆኑ፤ በተለይም የከተማ ነዋሪ ህዝብ ቁጥር ዕድገት መጨመር ለፍርድ ቤቶች የሚቀርቡ ጉዳዮችን የሚያበዛና የሚያወሳስብ መሆኑ፤<br>• ከፍተኛ የሥራ አጥነት ቁጥር መኖር የወንጀል መስፋፋትን የሚያስከተል መሆኑ፤<br>• የህብረተሰቡ የመሟገት ባህል ከፍተኛ መሆኑ የጉዳዮችን ፍሰት እንዳይቀንስ ምክንያት መሆኑ፤<br>• ዜጎች ለማህበረሰብ እሴት የሚሰጡት ዋጋ እየቀነሰ መምጣቱና ጉዳዮችን ሁሉ ለፍርድ ቤት የማቅረብ አዝማሚያ መብዛቱ፤ |

| ተ/ቁ | የትንተና ዕይታ | መልካም አጋጣሚዎች | ስጋቶች |
|---|---|---|---|
| 4 | ቴክኖሎጂያዊ ሁኔታ | • ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች በሀገሪቱ እየተተገበሩ መሆናቸው፤<br>• የቴክኖሎጂ መሰረተ ልማትና የሞባይል ቴክኖሎጂ፣ የኬዝ ፍሰት አስተዳደር፣ የቴሌኮምዩቲንግ አገልግሎት፣ በኤሌክትሮኒክስ እንዲከወን ማስቻል እንዲሁም ዲጂታላይዜሽን እና ወረቀት አልባ ስርአቶች በተነጻጻሪ በተሻለ ሁኔታ ለመተግበር የሚያስችሉ የቴክኖሎጂ ኢንፍራስትራክቸርና እውቀት በአገሪቱ መኖሩ፤ | • አገራዊ የኢኮቴ ኢንፍራስትራክቸር ደካማ መሆን፤<br>• አብዛኛው የፌደራል ፍርድ ቤቶች ተገልጋዮች የኢኮቴ አጠቃቀምና ግንዛቤ አነስተኛ መሆን፤<br>• የኢኮቴ ኢንፍራስትራክቸርና መፍትሔዎች በፍጥነት የሚያድጉና የሚቀየሩ መሆናቸው ከፍተኛ ወጪ የሚያስከትል መሆኑ፤ ፍርድ ቤቶችም ይህንን እድገት በፍጥነት ከፍርድ ቤት ስራ ጋር አዋህደው ለመተግበር ያላቸው አቅም ውሱን መሆኑ፤<br>• የማህበራዊ ሚዲያ መስፋፋት አዳዲስ ወንጀሎችን ሊፈጥር የሚችል መሆኑ፤<br>• በሳይበር ሴኩሪቲ ላይ ጥቃት የመፈጸሙ ዕድል ሩቅ አለመሆኑ፤ |
| 5 | አካባቢያዊ ሁኔታ | • የአረንጓዴ ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ መኖርና ተቋማዊ መሆኑ፤<br>• በተለያዩ የመንግስት መስሪያ ቤት የስራ አከባቢ አረንጓዴና ጽዱ የማድረግ ልምድ እየዳበረ መምጣቱ በፍርድ ቤቶች ላይ ሊኖረው የሚችለው በጎ ተጽዕኖ፤<br>• የአረንጓዴ ስትራቴጂ ትግበራ ፍርድ ቤትን ለዳኞችም ሆነ ለተገልጋዮች ምቹ፣ ሳቢና ተስፋ ሠጪ የማድረግ እድል ያለው መሆኑ፤ | • የህዝብ ብዛትና የተፈጥሮ ሃብት አለመመጣጠን የሚፈጥረው ውዝግብና ከዚህ የተነሳ እየጨመረ ሊመጣ የሚችለው የጉዳይ ብዛት፤<br>• ከህዝቡና የሲቪክ ማህበረሰቦች ንቃተ ህግና የሙብት ግንዛቤ መዳበር ጋር ተያይዞ ከአካባቢ ጥበቃ ጋር የተገናኙ በርካታ በዓይነታቸው የተለዩ ጉዳዮች ወደ ፍርድ ቤት ሊመጡ መቻላቸው፤<br>• ወረቀት አላባ አገልግሎትን ለመስጠት የተገልጋይ ሁኔታ ገዳቢ ገዳቢ መሆኑ፣ |

| ተ/ቁ | የትንተና ዕይታ | መልካም አጋጣሚዎች | ስጋቶች |
|---|---|---|---|
| 6 | ህጋዊ ሁኔታ | • የፌደራል ፍርድ ቤቶችና የዳኞች አስተዳደር ህጎች መሻሻልና የፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን ማረጋገጥ እና ለተቋሙ የተሻለ ገጽታ አስተዋጽዖ ያለው መሆኑ፤<br>• የዳኝነት ነፃነትና የፍትህ ስርዓቱን ለማጎልበት የሚያግዙ ብዛት ያላቸው የመደበኛና የሥነ ሥርዓት ህጎች ማሻሻያዎች እየተደረጉ መሆኑ | • አስፈላጊ ሕጎች በሚፈለገው ጥራትና ጊዜ አለመውጣታቸው፣<br>• የህግ አስከባሪ ኃይላት ህግ የማስከበር ብቃት በሚፈለገው ደረጃ አለመሆኑ፣<br>• አዳዲስ ህጎች ውስብስብ በመሆናቸው የዳኞችና የፍርድ ተቋሙ አቅምን የሚፈታተኑ መሆናቸውና በእነዚህ ዙርያ የተሟላ አገልግሎት ለመስጠት የሚጠበቀው ዝግጅት አለመሟላቱ፤ |

## 1.4. አስቻይና ፈታኝ ሁኔታዎች

በተካሄዱ ውስጣዊ ቅኝቶች የተለዩ ጥንካሬዎችን እና በውጫዊ ዳሰሳ የተለዩ መልካም አጋጣሚዎችን በመጠቀም የተቋሙን ስትራቴጂክ ዕቅድ ውጤታማ ለማድረግ የሚያግዙ አስቻይ ሁኔታዎች እና በውስጣዊ ድክመቶችና በውጫዊ ስጋቶች ሊያጋጥሙ የሚችሉ ፈተናዎች የተለዩ ሲሆን በሚከተለው ሰንጠረዥ ተጠቃልለው እንዲታዩ ተደርገዋል።

| አስቻይ ሁኔታዎች | ፈታኝ ሁኔታዎች |
|---|---|
| • ሁሉን አቀፍ ሀገራዊ የማሻሻያ ስራዎች መኖራቸው እና በፍርድ ቤቱ አመራሮች ቁርጠኝነት ሰፊ የዳኝት አገልግሎት ማሻሻያ ሥራዎች በሂደት ላይ መሆናቸው (አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ የአሰራርና የአደረጃጀት ለውጦች.... )፤ | • የፌደራል ፍርድ ቤቶች በክልሎች ያላቸው አደረጃጀትና ተደራሽነት አነስተኛ መሆን፣<br>• የዳኝነት አገልግሎት ጥራትና ቅልጥፍናን ለማሳደግ የሚያግዝ ጠንካራ ስርዓት አለመዘርጋቱ፣ (የአፈጻጸም ምዘናና እውቅና፣ የውሳኔ ትንተና፣ የጠበቆች/ ተገልጋዮች ሰርቬይ፣ የፍርድ ምርመራ/አዲት.... )፣ |

| አስቻይ ሁኔታዎች | ፈታኝ ሁኔታዎች |
|---|---|
| • የዳኝነት ነፃነት ህገመንግስታዊ ዋስትና ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያግዙ እና ተግባራዊነቱን ለማሳደግ የሚያስችሉ አበረታች እርምጃዎች እየተወሰዱ መሆናቸው (በጀት በቀጥታ ለፓርላማ ማቅረብ፣ የአስተዳደር ሰራተኞችን ማስተዳደር...)፣<br>• አንጻራዊ በሆነ መልኩ የፌደራል ፍርድ ቤቶች በአዲስ አበባና በድሬደዋ መደራጀታቸው፤<br>• በሀገሪቱ ያለው የኢኮቴ መሰረተ ልማትና የተጠቃሚዎች ቁጥር እድገት ታሳቢ ያደረገ በኢኮቴ የታገዘ የዳኝነት አገልግሎት ለመስጠት የተጀመሩ የማሻሻያ ስራዎች ተጠናክረው መቀጠላቸው፤<br>• የፍርድ ቤቶችን ስራ የማስተዋወቅና አጋርነትን የማበራከት ስራ አንጻራዊ በሆነ መልኩ እየተጠናከረ መምጣቱ እና ባለድርሻ አካላት ለማሻሻያ ስራዎች የሚያደርጓቸው ድጋፎች መጨመራቸው፤<br>• የጾታ እኩልነት ላይ ያሉ መሻሻሎች (የሴት ዳኞችና አመራሮች መጨመር፣ የጾታዊ ትንኮሳ ላይ ፖሊሲ መውጣቱ)፣<br>• የዳኝነት ዘርፉ በሃገሪቱ የአሥር ዓመት ስትራቴጂያዊ የልማት ዕቅድ ውስጥ መካተቱ የተከማቹ ችግሮችን ለመፍታት ተገቢ ትኩረት ሊያስገኝ የሚችል መሆኑ፤<br>• አገሪቱ ያሏትን የተለያዩ አማራጭ የግጭት መፍቻ ባህላዊ ሥርዓቶች ተጠቅሞ የፍርድ ቤቶችን የሥራ ጫና የሚቀንስ ፍርድ ቤት መር አስማሚ ስርዓት የህግ ዕውቅና ማግኘቱ፤ | • የሥነ ምግባር እና የመልካም አስተዳደር መርሆዎችን ያገናዘበ የአገልጋይነት ስሜት እና የተጠያቂነት ሥርዓት በበቂ ሁኔታ አለመዳበር፣<br>• የተጠናከረ የጥናት፣ ምርምርና የዕውቀት አስተዳደር ስርዓትና አደረጃጀት አለመኖር፣<br>• የተሟላ የዳኞች/ሰራተኞች የትምህርትና ስልጠና መርሐ-ግብር ተዘጋጅቶ የአቅም ግንባታ ስርዓት ባለመተግበሩ የመምራትና የመፈጸም ውስንነት መታየቱ፤<br>• የፌደራል ፍርድ ቤቶች አደረጃጀት የተለጠጠ፣ ተደራራቢና በውል ልዩነታቸው ያልተገለጸ የስራ ክፍሎችን በመያዙ ቅልጥፍናና ውጤታማነት ከማረጋገጥ አንጻር ክፍተት ያለው መሆኑ፣<br>• የበጀት አስተዳደር ነጻነት በተሟላ መልኩ አለመተግበር፣<br>• የተጠናከረ የፕሮጀክት ስራ አመራር ስርዓት አለመኖር፤<br>• የስራ ቦታዎችና መገልገያዎች ምቹና ተደራሽ አለመሆን<br>• የሀገሪቱ የኢኮቴ መሰረተ ልማት በሚፈለገው ደረጃ ያደገ አለመሆን፤ የፍርድ ቤት አሠራሮችም በሚገባቸው መጠንና ፍጥነት በኢኮቴ አለመደገፋቸው፣<br>• የሀገሪቱ የፖለቲካ ባህል እና የፍርድ ቤቶች የኮሙኒኬሽን ሥራ በበቂ ሁኔታ ባለመዳበሩ ምክንያት በህብረተሰቡ ዘንድ የተፈጠረ አሉታዊ አመለካከት እና ግንዛቤ የፍርድ ቤቶቹን ገለልተኝነትና አመኔታ ጥያቄ ውስጥ ማስገባቱ፤<br>• የህግ የበላይነትን የማስከበር ተልዕኮ በአግባቡ አለመተግበር የፍርድ ቤቶች አገልግሎት ቅልጥፍናና ጥራት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚፈጥር መሆኑ፤<br>• መሰረተ ልማት ለማስፋፋት የሚያስችል በቂ በጀት አለመኖሩ፣ |

# 1.5. የተገልጋዮችና የባለድርሻ አካላት ፍላጎት ትንተና

የፌደራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ተግባራቸውን የሚያከናውኑት ከሌሎች የፌደራልና የክልል የመንግስት አካላት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት እንዲሁም ከማህበረሰቡ ውጪ በመሆን አይደለም፡፡ የፌደራል ፍርድ ቤቶች በከፍተኛ ደረጃ ተጽዕኖ ፈጣሪና ጠንካራ ውጤት የሚያመጡ ባለድርሻ አካላት አላቸው፡፡ ባለድርሻ አካላቱም ፍርድ ቤቶቹ በሚያከናውኑት ተግባር ላይ ከፍተኛ ፍላጎት አላቸው፡፡ ይህ ስትራቴጂያዊ ዕቅድ በሚተገበርበት ወቅትም በቀጥታ ተሳታፊ ናቸው፡ ፡ ፍርድ ቤቶቹ በሚያከናውኗቸው የለውጥ ስራዎች ውስጥ ባለድርሻ አካላቱ የለውጡ አካል፣ ስለለውጡ ደጋፊና ተከራካሪ እንዲሁም አጋር በመሆን ሊያለግሉ ይችላሉ፡፡

### የተገልጋዮች እና የባለድርሻ አካላት ትንተና

| ተገልጋዮች/ ባለድርሻ አካላት | ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት ከፍርድ ቤት የሚጠብቁት | ፍርድ ቤት ከተገልጋዮች/ከባለድርሻ አካላት የሚጠብቀው | የሚጠበቀው ባይከናወን የሚያስከትለው ተጽዕኖ | የተጽዕኖ ደረጃ |
|---|---|---|---|---|
| የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት | • ፍርድ ቤቱ ብዝኃነት የሚታይበት እና አካታች እንዲሆን፣<br>• ሕግ ለማውጣት በተወከሉባቸው ጉዳዮች ላይ በውክልናው ልክ በወቅቱ ህግ (መመሪያ) እንዲያወጡ፣<br>• ከሙስና የጸዳ፣ የሥነ ምግባር ችግር የማይታይበትና ተጠያቂነት የሰፈነበት ፍርድ ቤት እንዲሆን፣<br>• ቀልጣፋ ፍትህ የሚሰጥበት እንዲሆን፣<br>• በበጀት አቀራረብና አፈጻጸም ላይ አቅሙ የተገነባ ፍርድ ቤት እንዲሆን ይፈልጋል፡፡ | • የፍርድ ቤትን ተልዕኮ ማሳካት የሚያስችሉ ሕጎችን በወቅቱ እንዲያወጡ፣<br>• በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውስጥ የዳኝነት ጉዳይን ለብቻው የሚከታተል ቋሚ ኮሚቴ እንዲደራጅ፣<br>• በቀመር ላይ የተመሰረተ በቂ በጀት እንዲመደብ፣<br>• በህግ አወጣጥ ላይ የፍርድ ቤት ተሳትፎ እንዲኖር ይፈልጋሉ፡፡ | • የዳኝነት ነፃነትና ተጠያቂነት መጓደል፣<br>• ቀልጣፋና ውጤታማ ፍትህ በተገቢው አጭር ጊዜ ውስጥ መስጠት አለመቻል፣ | ከፍተኛ |

| ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት | ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት ከፍርድ ቤት የሚጠብቁት | ፍርድ ቤት ከተገልጋዮች/ከባለድርሻ አካላት የሚጠብቀው | የሚጠበቀው ባይከናወን የሚያስከትለው ተጽዕኖ | የተጽዕኖ ደረጃ |
|---|---|---|---|---|
| የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ | • ፍርድ ቤት በላቀ ብቃት አርአያ ሆኖ የሚሰራ፣ ተደራሽ፣ ነጻና ተጠያቂነት የተመዛዘኑበት፣ በተካነ (ስፔሻላይዝድ) ችሎትና ዳኛ የሚሰራ ቀልጣፋ ፍርድ ቤት፣<br>• የዳኞች ቁጥር፣ የሰበር ስርአት፣ የፍርድ ቤት አመራሮችን የሚተዳደሩበት ስርአት እና መሰል ጉዳዮች በስርአት እንዲመለሱና ተቋማዊ እንዲሆኑ፣<br>• ፍርድ ቤትን በመሰረቱ በሚለውጥ ተግባር ላይ አተኩሮ መስራት፣<br>• በታወቀ ስርአት ከዳኞች እና ሌሎች ሰራተኞች ጋር የስራ ግንኙነት መመስረት፣<br>• ደመወዝና ጥቅማ ጥቅምን በጥናት ላይ በተመሰረተ ማዕቀፍ (ፓኬጅ) መመለስ ይፈልጋሉ። | • ጉባኤው ፍትኃዊ፣ ግልጽ፣ ጠንካራ እና ዘመናዊ ሆኖ እንዲሰራ፣<br>• በሕግ የተሰጠውን ኃላፊነት በፍትኃዊነት እና በግልጽነት እንዲያከናውን፣<br>• ፍርድ ቤትን በመሰረቱ በሚለውጥ ተግባር ላይ አተኩሮ እንዲሰራ፣<br>• የዳኞችን እና የፍርድ ቤትን ነጻነትና ተጠያቂነት ማረጋገጥ፣ የዳኞችን ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም በጥናት ላይ በተመሰረተ ማዕቀፍ (ፓኬጅ) እንዲመልስ ይፈልጋል። | • ተገቢ የሆነ ውሳኔ በተገቢው ጊዜ እና ጥራት አለመስጠት፣<br>• ለአጠቃላይ አገልግሎት አሰጣጥ እንቅፋት መሆን<br>• ፍርድ ቤት የተጣለበትን ኃላፊነት በአግባቡ መወጣት አለመቻል፣<br>• እምነት እና አመኔታ ማጣት፣ | ከፍተኛ |
| የፌደሬሽን ምክር ቤት | • የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ያስፈልጋቸዋል የተባሉ ጉዳዮች በወቅቱ እንዲቀርቡ፣<br>• ለሕገ መንግስትና ሕገ መንግስታዊ ስርዓት ዋስትና የሚሰጡ ውሳኔዎች እንዲሰጡ ይፈልጋል። | • የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄዎች ላይ ግልጽ፣ ፈጣንና ሕገ መንግስታዊ ትርጉም ብቻ የተሰጠበት ውሳኔ እንዲሰጥ ይፈልጋል። | • የህገ መንግስት ትርጓሜ ክፍተት መፈጠር፣<br>• የሕገ መንግስታዊ ስርአት ግንባታ ዋስትና መታጣት፣ | ከፍተኛ |

| ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት | ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት ከፍርድ ቤት የሚጠብቁት | ፍርድ ቤት ከተገልጋዮች/ከባለድርሻ አካላት የሚጠብቀው | የሚጠበቀው ባይከናወን የሚያስከትለው ተጽዕኖ | የተጽዕኖ ደረጃ |
|---|---|---|---|---|
| የጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት | • ብቃትን መሰረት ያደረገ የዳኞች ምልመላ | • የዳኞች ሹመት በወቅቱ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲቀርብ | • የቅልጥፍና ችግር ያጋጥማል። | ከፍተኛ |
| የገንዘብ ሚኒስቴር | • እሴት የሚጨምር ውጤታማ የሃብት አጠቃቀም፥<br>• ግልፅነትና ተጠያቂነት<br>• ሙያዊነት | • ሙያዊነት፥ በቂ በጀት እንዲመደብ፥<br>• በጀት በወቅቱ እንዲለቀቅ፥<br>• በጀት የማስተዳደር ነፃነት እንዲከበር፥ | • የፍርድ ቤት ነፃነት ሳንካ ይገጥመዋል። | ከፍተኛ |
| የመንግስት አካላት | • ሙያዊነት የሰፈነበት የዳኝነት ስርአት፣<br>• ስልታዊ አጋርነት፣<br>• ነጻ፣ተጠያቂና ቀልጣፋ የዳኝነት ስርአት፣<br>• በሕገ መንግስት የተጣለበትን ኃላፊነት የሚወጣ ፍርድ ቤት እንዲኖር ይፈልጋሉ። | • ሙያዊነት፣ በሕገ መንግስት የተጣለባቸውን ኃላፊነት በአግባቡ እንዲወጡ፣<br>• የፍርድ ቤትን ስልጣን እና ነጻነት እንዲያከብሩ፣ | • የስልጣን ክፍል አደጋ ውስጥ ይወድቃል፣<br>• የፍርድ ቤት ተቀባይት፣ ተዓማኒነት እና አስፈላጊነት ይቀንሳል፣ | ከፍተኛ |
| የክልል ፍርድ ቤቶች | • የተናጠልና የጋራ ስራዎችን በመለየት በጋራ መስራት፣<br>• ፌደራሊዝም ላይ እና የፍርድ ቤቶች አደረጃጀት አረዳድ ላይ መግባባት እንዲኖር፣<br>• የፍርድ ቤቶች የጋራ መድረክና የዳኞች ፎረም (ትስስር) እንዲኖር፣<br>• የሰው ኃይል አስተዳርን በማጥናት የተቀራረበ | • መረጃ እንዲይዙ፣<br>• የፌደራልን ጫና መቀነስ የሚያስችሉ ጥራት ያላቸውን ፍርዶች እንዲሰጡ፣<br>• የድጎማ በጀትን ለአላማው እንዲያውሉ፣<br>• በጋራ መድረኮች ላይ በንቃት እንዲሳተፉ፣ | • የፍርድ ቤቶች ቅልጥፍ እና ውጤታማነት ዝቅተኛ ይሆናል፣<br>• ወጥ የሆነ የዳኝነት ስርአት አይኖርም፣ በዚህም ሕብረተሰቡን ግራ የሚያጋባ የዳኝነት ስርአት ይፈጠራል፣ | ከፍተኛ |

| ተገልጋዮች/ ባለድርሻ አካላት | ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት ከፍርድ ቤት የሚጠብቁት | ፍርድ ቤት ከተገልጋዮች/ከባለድርሻ አካላት የሚጠብቀው | የሚጠበቀው ባይከናወን የሚያስከትለው ተጽዕኖ | የተጽዕኖ ደረጃ |
|---|---|---|---|---|
| የክልል ፍርድ ቤቶች | አሰራር መፍጠር፣ ውጤታማ ስርአት መዘርጋት፣<br>• በክልል የሚታዩ የፌደራል ጉዳዮችን መለየት፣ ለስራውም ተመጣጣኝ ድጎማ በሚታወቅ ቀመር ማግኘት፣<br>• ስልጠና፣ የልምድ ለውውጥ፣ የዘመናዊ ቴክኖሎጂ እና የቴክኒክ ድጋፍ ማግኘት፣<br>• በክልል ፍርድ ቤቶች እጩ ዳኞች ሹመት ላይ በፍጥነት አስተያየት ማግኘት፣<br>• የሰበር ውሳኔዎች በጊዜ ተደራሽ መሆን፣<br>• መሰረታዊ በሆኑ የዳኝነት ጉዳዮች ላይ የተቀራረበ አሰራር እንዲኖር ይፈልጋሉ። | • የፌደራል ጉዳዮችን ለይተው የተሟላ የክልል ዳኞች አሿሿም ላይ ሕገ መንግስትን በጥብቅ እንዲተገብሩ፣<br>• ስልታዊ አጋርነት እንዲኖር ይፈልጋሉ። | • በሀገሪቱ ያሉ ፍርድ ቤቶች ወጥ የሆነ አሰራር እንዳይኖራቸው ያደርጋል ወይም ተገማች እንዳይሆኑ ያደርጋል፣<br>• በፍርድ ቤቶች መካከል የአቅም ልዩነት እየጎላ ይሄዳል፣<br>• ተገልጋዩ ክፍል በተቋማት መካከል የአመኔታ ልዩነት መፍጠር ይጀምራል፣ | |
| ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ | • ነጻ፣ ተጠያቂነት ያለበት፣ ገለልተኛ፣ ብቃት ያለው፣ ፍርድ ቤት እንዲሆን፣ ፍትሐዊ፣ ተገማች፣ የዳኞች አቅምን በሚታይ መልኩ መገንባት፣<br>• አስተማሪ ፍርድ እንዲሰጥ፣<br>• የፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲከበርና ለመላው ሕብረተሰብ በሚጠቅም መልኩ እንዲፈጸም፣ | • እውነትን ለማውጣትና ፍትህን ለማስፈን የሚያስችል ክርክር ማቅረብ፣<br>• የክስ አመሰራረት፣ የተከሳሽ አቀራረብ፣ የምስክር አሰማም ሂደት ለዳኝነት ተግባር እንቅፋት እንዳይሆን፣ | • ፍትህ የማግኘት መብት ይደናቀፋል፣ | ከፍተኛ |

| ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት | ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት ከፍርድ ቤት የሚጠብቁት | ፍርድ ቤት ከተገልጋዮች/ከባለድርሻ አካላት የሚጠብቀው | የሚጠበቀው ባይከናወን የሚያስከትለው ተጽዕኖ | የተጽዕኖ ደረጃ |
| --- | --- | --- | --- | --- |
| ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ | • የፍርድ ቤት አመራር እንዲናበብ፣ የፍርድ ቤትን መርሆዎች በአርአያነት የሚተገብር እንዲሆን፣<br>• የፕሮጀክት አፈጻጸምን አቅም እንዲገነባ፣<br>• ከሌሎች የመንግስት አካላት ጋር በመርህና በጎንዮሽ ግንኙነት ላይ የተመሰረተ ግንኙነት እንዲኖረው፣<br>• ፌደራል ፍርድ ቤቶች በክልሎች እንዲቋቋሙና እንዲደራጁ፣<br>• የሌጋል ኦዲቲንግ ስራ እንዲሰራ ፍልጋል። | • ሙያዊ ክርክር እንዲቀርብ፣<br>• የፍርድ ቤት የቅጣት ውሳኔዎች በአግባቡ ስለመፈጸማቸው ክትትል እንዲያደርግ ይፈልጋል። | | |
| ማረሚያ ቤቶች | • በፍርድ ቤት የሚሰጡ ትዕዛዞች በማረሚያ ቤቱ ማንጄት ውስጥ ጣልቃ እንዳይገባ፣<br>• ፍርድ ቤት ምላሽ ሰጪ እንዲሆን፣ የይግባኝ ግልባጭ እንደተጠየቀ ወዲያውኑ እንዲሰጥ፣<br>• የገንዘብ ቅጣት አፈጻጸምና የአመክሮ ችግር እንዲፈታ፣<br>• ችግሮች የሚፈቱበት የጋራ የውይይት መድረክ እንዲኖር፣<br>• ቀልጣፋ፣ ግልፅና የማያመላልስ ውሳኔዎች/ትዕዛዞች እንዲሰጣቸው፣ | • ታራሚን በህግ መሰረት አርሞ ከህብረተሰቡ ጋር መቀላቀል የሚያስችል ውጤታማ ስርአት እንዲገነባ፣<br>• ደጋጋሚነትን የሚያስቀር፣ የሰብአዊ መብት የሚያስጠብቅ፣ በመረጃ ላይ የተመሰረተ እርምት እንዲኖር፣<br>• የቀጠሮ እስረኛን በቀጠሮ ማቅረብ፣ በፍርድ ቤት የሚሰጡ ትዕዛዞችን በአግባቡ እንዲፈጸም ይፈልጋል። | • የእስረኞች አያያዝ ደረጃውን ያልጠበቀ እንዲሆን ያደርጋል፣<br>• በተቋሙ እምነት ይተፋል፣<br>• ደጋጋሚነት ይጨምራል፣<br>• እስረኛውም ሆነ የማረሚያ ቤት ሰራተኞች ላልተፈለገ | ከፍተኛ |

| ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት | ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት ከፍርድ ቤት የሚጠብቁት | ፍርድ ቤት ከተገልጋዮች/ከባለድርሻ አካላት የሚጠብቀው | የሚጠበቀው ባይከናወን የሚያስከትለው ተጽዕኖ | የተጽዕኖ ደረጃ |
|---|---|---|---|---|
| | • አስተማሪ ውሳኔ እንዲሰጥ፣<br>• አማራጭ ቅጣቶች እንዲተገበሩ፣ የመልሶ መቀላቀል ስርአት ተግባራዊ እንዲሆን ይፈልጋሉ። | | ወጪ እና እንግልት ይዳረጋሉ፣ | ከፍተኛ |
| ፖሊስ | • ክብርን የጠበቀ መስተንግዶ እንዲኖር፣<br>• በገለልተኝነት እንዲስተናገዱ፣<br>• የኤግዚቢት አያያዝ እና አወሳሰን ላይ ፈጣን መፍትሄ እንዲሰጥ፣<br>• የሀገር አቀፍ የፍትህ አካላት የጋራ መድረክ እንዲጠናከር፣<br>• አስተማሪና ወቅታዊ ውሳኔ እንዲሰጥ፣<br>• ለምስክሮች በህጉ መሰረት አግባብ ያለው ጥበቃ እንዲደረግ ይፈልጋል። | • የዘመነ፣ ንጹሃንን ከጥፋተኛነት የሚለይ ጥራት ያለው የወንጀል ምርመራ ስርአት እንዲኖር፣<br>• የፍርድ ቤት ትዕዛዝ እንዲከበር፣<br>• በምርመራ ሂደት፣ ተከሳሽን ሆነ ማስረጃን በማቅረብ እንዲሁም በአጠቃላይ ተግባሩ ለፍትህ መጓተትም ሆነ መታጣት ምክንያት እንዳይሆኑ፣<br>• ሰብአዊ መብትን ያከበረ የተጠርጣሪ አያያዝ እንዲኖር ይፈልጋል። | • የፍትህ መዛባት፣ መጓተትና መታጣት፣<br>• በተቋማቱ መካከል ትብብር እና መተማመን እንዳይኖር ያደርጋል፣ | ከፍተኛ |
| ማህበረሰቡና ተከራካሪ ወገኖች/ተገልጋይ | • ተገልጋይ ተኮር፣ መብቶችን በግልጽነት፣ በተገቢው ጊዜና በተደራሽነት የሚያስከብር ነጻና ተጠያቂ ፍርድ ቤት፣<br>• ገንቢ አስተያየት መስጠት የሚያስችል ስርአት እንዲገነባ፣ | • ሙስናንና ብልሹ አሰራርን እንዲጠየፍና አምርሮ እንዲታገል፣<br>• ቅሬታዎቹን ሁሉ ለፍርድ ቤት እንዲያቀርብ፣ የተሟላ ክርክር እንዲያቀርብ፣ | • የፍትህ አሰጣጥ ቅልጥፍናና ጥራት መጓደል፣<br>• በፍርድ ቤት አገልግሎት ያለመርካት፣ አመኔታ ማጣት፣ | ከፍተኛ |

| ተገልጋዮች/ ባለድርሻ አካላት | ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት ከፍርድ ቤት የሚጠብቁት | ፍርድ ቤት ከተገልጋዮች/ከባለድርሻ አካላት የሚጠብቀው | የሚጠበቀው ባይከናወን የሚያስከትለው ተጽዕኖ | የተጽዕኖ ደረጃ |
|---|---|---|---|---|
| | • ምላሽ ሰጪ ፍርድ ቤት እንዲሆን፣<br>• ውሳኔዎች በጥራት እንዲሰጡና ያለእንግልት እንዲፈጸሙ፣<br>• የሚታመን ፍርድ ቤት እንዲገነባ፣<br>• ጉዳይ በተቀጠረበት ዕለት እንዲከወን ይፈልጋሉ። | • ለጉዳይ መጓተትም ሆነ ለፍርድ ቤት አለመታመንና ውጤታማነት መጥፋት ምክንያት እንዳይሆን፣<br>• ህግን፣ ሀቅን መሰረት ያደረገ ክርክር እንዲቀርብ ይፈልጋል። | • ፍትህን በሌላ አማራጭ መፈለግ፣ | |
| የሲቪክ ማህበራት | • ቀልጣፋና ውጤታማ የጉዳይ አስተዳደር<br>• በአጋርነት መስራትና የመረጃ ልውውጥ፣<br>• ግልጽነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት የዳኝነት ስርአት፣<br>• ፕሮጀክቶችን በጋራ መተግበር፣<br>• ሕዝብ ተኮር ክርክሮች ላይ መሳተፍ፣<br>• ፍትህን ተደራሽ የሚያደርግ አሰራር እንዲኖር ይፈልጋሉ። | • በተሰጣቸው ኃላፊነት ልክ ለፍርድ ቤት ተልዕኮ መሳካት የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ፣<br>• የፍርድ ቤትን ተግባር በአግባቡ ለሚመለከታው ማድረስ፣<br>• የሙያ ደረጃ እና ሥነምግባር በሚያሳድግ ስራ ላይ ውጤታማ እንዲሆኑ፣<br>• ነጻ የሕግ ድጋፍን እንዲያበረታቱ፣<br>• የህግ ፍልስፍና እንዲያድግ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያረክቱ፣ | • አጋር የፋይናንስና የቴክኒክ ድጋፍ ማግኘት ያስቸግራል፣<br>• የፕሮጀክቶች ትግበራ እክል ይገጥመዋል፣<br>• የፍትህ ስርቱ በሚገባው ልክ ጠንካራ ላይን ይችላል። | ከፍተኛ |
| ሚዲያ | • የፍርድ ሂደት በግልጽነት እንዲካድ<br>• ትክክኛና እና ወቅታዊ መረጃ ማግኘት፣<br>• በዘገባ ስለሚሳተፉበት ሁኔታ ግልጽ መመሪያ እንዲኖር ይፈልጋሉ። | • ፍትሃዊ፣ ትክክለኛና በማስረጃ ላይ የተመሰረተ ዘገባ እንዲሰራ፣<br>• መረጃዎችን በአግባቡና በወቅቱ እንዲያሰራጩ፣<br>• የሚዲያ እና ዘገባ ሥነ ምግባርን ጠብቀው እንዲሰሩ፣ | • የህዝብ አመኔታ ማግኘትና ይደናቀፋል፣ | መካከለኛ |

| ተገልጋዮች/ ባለድርሻ አካላት | ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት ከፍርድ ቤት የሚጠብቁት | ፍርድ ቤት ከተገልጋዮች/ከባለድርሻ አካላት የሚጠብቀው | የሚጠበቀው ባይከናወን የሚያስከትለው ተጽዕኖ | የተጽዕኖ ደረጃ |
|---|---|---|---|---|
| ጠበቆች እና የጠበቆች ማህበር | • የጊዜን ዋጋ የተገነዘበ እና ለጊዜም ዋጋ የሚሰጥ፣ ተገማች፣ ነጻ፣ ተጠያቂ፣ በሁለንተናዊ ብቃቱ የተገነባና ብቃቱ የሚታመን፣ የሚመዘን፣ ባለጉዳዩን በክብር የሚይዝ፣ ውሳኔዎቹ ሁሉ በምክንያት የሚተነተኑበት፣ ዳኞች በስራቸው ሁሉ የሚታመኑበት ፍርድ ቤት እንዲሆን፣<br>• የተካነ ዳኛ እንዲኖር፣ ምደባቸውም ፍላጎትንና ዝንባሌን ጭምር ያገናዘበ እንዲሆን፣ የፍርድ ቤት ውሳኔ የህግ ፍልስፍናን እንዲያሳድግ፣<br>• የፍርድ ቤት ስራ ጠንካራ አገር ከመገንባት ጋር የሚያያዝ መሆኑ ላይ መግባባት እንዲኖር፣<br>• ፍርድ ቤት የሚያዘጋጀው እቅድ የክልሎችን ነባራዊ ችግርም የሚፈታ እንዲሆን፣<br>• የፌዴራል ፍርድ ቤት በክልሎች እንዲደራጅ፣<br>• የወጪና ኪሳራ አወሳሰን በሙግት ላይ ከፍተኛ እንድምታ ያለው በመሆኑ በዘፈቀደ አለመወሰን፣<br>• ስልታዊ አጋርነት፣ ፍርድ ቤቶች ከጠበቆች ማህበር ጋር በዳኞች ሹመት፣ አቅም ግንባታ፣ ህግ በማውጣት፣ በህግ ድጋፍ፣ ጊዜያዊ ዳኛ ሆኖ በመስራት ሂደት በጋራ የሚሰሩበትን ስርአት ማበጀት ይፈልጋሉ። | • ሙያዊ፣ ገለልተኛ፣ ከሙስናና ብልሹ አሰራር የጸዳ የጥብቅና አገልግሎት እንዲሰጡ፣<br>• ብልሹ አሰራሮችን በንቃት እንዲታገሉ፣<br>• ደንበኞቻቸውን በትጋትና በሀቀኝነት እንዲያገለግሉ፣<br>• ለጉዳይ መጓተትም ሆነ ለፍርድ ቤት አለመታመንና ውጤታማነት መጥፋት ምክንያት እንዳይሆኑ፣<br>• በስራቸውም ሆነ በግል ኑሯቸው የፍርድ ቤትን ገጽታ የሚያበላሹ እንዳይሆኑ፣<br>• በፍርድ ቤት ስራዎች ውስጥ በአጋርነት በንቃት እንዲሳተፉ ይፈልጋል። | • የዜጎች ፍትህ የማግኘት መብት አይረጋገጥም፣<br>• አቅም የሌላቸው ዜጎች መብታቸው በአግባቡ አይተገበርም፣<br>• የጉዳይ መጓተት፣ የጥራት ችግር፣ የህዝብ አመኔታና እርካታ ማጣት ይከሰታል፣<br>• ከአዳዲስ ህጎችና የአሰራር ሁኔታዎች እንዳይተዋወቁ ያደርጋል፣<br>• የሚሰሩትን ስራ ትኩረት አለመስጠት፣<br>• ጠንካራ የፍርድ ቤት አጋርን ማጣት ይከተላል፣ | ከፍተኛ |

| ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት | ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት ከፍርድ ቤት የሚጠብቁት | ፍርድ ቤት ከተገልጋዮች/ከባለድርሻ አካላት የሚጠብቀው | የሚጠበቀው ባይከናወን የሚያስከትለው ተጽዕኖ | የተጽዕኖ ደረጃ |
|---|---|---|---|---|
| ዩኒቨርሲቲ/የህግ ት/ቤቶች | • የነፃ የህግ ድጋፍ ስራ በጋራ ትብብር ተጠናክሮ እንዲቀጥል፣<br>• የትምህርት፣ ስልጠና፣ ጥናትና ምርምር ስራዎችን በጋራና በትብብር መስራት፣<br>• የየተቋሙን ባለሙያዎች በጋራ መጠቀም፣<br>• የህግ ተማሪዎች በፍርድ ቤቶች የሚያደርጉት የተግባር ልምምድ ውጤታማ እንዲሆን ይፈልጋሉ። | • ጥራት ያለው የህግ ባለሙያ እንዲያፈሩ፣<br>• የጋራና የትብብር ስራ እንዲጎለብት፣<br>• ስልታዊ አጋርነት እንዲኖርና እንዲጠናር ይፈልጋል። | • የዳኝነት ጥራት ይቀንሳል፣<br>• ብቃት ያለው የህግ ምሩቅ ይቀንሳል፣<br>• የህግ ትምህርትን ከተግባር ጋር መተሳሰርን ይቀንሳል | ከፍተኛ |

የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ከላይ በዝርዝር የተገለጹ የጥናት ግኝቶችን (የውስጥ ጥንካሬና ድክመት፣ የውጭ መልካም አጋጣሚና ስጋት) መሰረት በማድረግ አስቻይ ሁኔታዎችን ተጠቅሞ ፈተናዎችን በመቋቋም የቀጣዮቹን አምስት ዓመት አፈጻጸም ለማሳደግ በሚከተሉት ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች እና ቁልፍ የውጤት መስኮች ላይ አትኩሮ ለመስራት ታቅዷል ።

# ክፍል ሁለት

## 2 ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች

የፌደራል ፍርድ ቤቶች የሚሰጡዋቸውን የዳኝነት አገልግሎቶች ለማሻሻል የጀመሩዋቸውን የለውጥ ሥራዎች አጠናክረው በመቀጠል በሶስተኛ ስትራቴጂክ ዘመን ለማከናወን ያቀዱትን ስትራቴጂክ ዕቅድ ለማሳካት የጋራ ስምምነት የተደረገባቸው የተቋም ራዕይ፣ ተልዕቆና ዕሴቶች ከመዘጋጀታቸውም ሌላ ሊተኮሩባቸው የሚገቡ ስትራቴጂያዊ ጉዳዮችን መሰረት ያደረጉ ቁልፍ የውጤት መስኮች ተቀርጸዋል፡፡ እነዚህ የውጤት መስኮች የየራሳቸው ግቦች እንዲኖሩዋቸው የተደረገ ሲሆን ግቦችን ለማሳካት የሚረዱ ስትራቴጂዎች፣ ከግቦቹ የሚጠበቁ ውጤቶችና መለኪያዎቻቸውም ተቀምጠውላቸዋል፡፡

### 2.1. ራዕይ፣ ተልዕኮ እና እሴቶች

#### ራዕይ

የሕዝብ አመኔታ ያተረፈ የዳኝነት ተቋም ሆኖ ማየት

#### ተልዕኮ

ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ተደራሽ የዳኝነት አገልግሎት በመስጠት የህግ የበላይነትን ማረጋገጥ

#### ቁልፍ እሴቶች

**ነፃነትና ተጠያቂነት፣**

ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥራቸውን ከማንኛውም አካል ጣልቃ ገብነት ነጻ በሆነ መልኩ ማከናወን የሚኖርባቸው መሆኑን የሚመለከት ነው፡፡ ፍርድ ሲሰጡም ህግንና ማስረጃን ብቻ መሠረት በማድረግ መሆን ይኖርበታል፡፡በመሆኑም ዳኞች የፍርድ ቤት ነጻነትን የመጠበቅና በአርአያነት የመጠቀም ግዴታ አለባቸው፡፡ዳኞች በሚሰጡት ውሳኔ ህጋዊነትና አግባብነት ልክ ተጠያቂም ይሆናሉ፡፡ ሌሎች የፍርድ ቤት ሠራተኞችም የፍርድ ቤት ነጻነትና ተጠያቂነት በማስከበር ረገድ አዎንታዊ ሚና ይጫወታሉ፡፡

**ገለልተኝነት፥ -**

ፍርድ ቤቶች እና ዳኞች ማንኛውንም ተገልጋይ በእምነት፣በአመለካከት...ልዩነት ሳይፈጥሩ በእኩልነት ማገልገል ይኖርባቸዋል፡፡ሥራቸውንም በህግና በማስረጃ ብቻ ተንተርሰው ያከናውናሉ፡፡

**ግልጽነት፥ -**

ፍርድ ቤቶች የቀረቡላቸውን ጉዳዮችን በግልጽ ችሎት ይመለከታሉ፡፡ የአሰራር ስርዓታቸውንና

አገልግሎቶቻቸውን በተመለከተ ለሕብረተሰቡ በቂ መረጃ በመስጠት ግልጽነትን ማስፈን ይጠበቅባቸዋል፡፡ ለዚህም የሕዝብ አስተያየትና ትችትን በመቀበል፣ መልካም አስተዳደርን በማስፈን እና ለሚያከናውኗቸው ተግባራት ኃላፊነት በመውሰድ መርህ ይሰራሉ፡፡

### ሙያዊ ብቃት፡-

በየደረጃው የሚገኙ የፍርድ ቤት አመራሮች፣ ዳኞች እና ሠራተኞች ለሥራ መደባቸው የተቀመጠውን ዕውቀት፣ ክህሎትና ባህሪ አሟልተው ችግር ፈችና የመፍጠር ብቃት ያላቸው ይሆናሉ፡፡ ለዚህም ቀጣይነት ባለው መልኩ ራሳቸውን ማብቃት የሚጠበቅባቸው ሲሆን ፍርድ ቤቶች በብቃትና ውጤት ላይ የተመሠረተ ተቋማዊ የመማማር ስርዓትን ዘርግተው መተግበር ይኖርባቸዋል፡፡

### ቴክኖሎጂ ተጠቃሚነት፡-

ፍርድ ቤቶች የዘመናዊ ቴክኖሎጂ ውጤቶችን በመዘርጋትና በአግባቡ በመጠቀም ቅልጥፍናን፣ ተደራሽነትን፣ የተገልጋይ እርካታ እና የሕዝብ አመኔታን ማሳደግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

### ሕዝብ ያማከለ፡-

ፍርድ ቤቶች ፍትህን በማገልገል ሂደት ተገልጋዮችን ለማርካት ይሰራሉ፡፡ ተገልጋይ ተኮር በመሆን የተገልጋዮች እርካታን ማረጋገጥ የፍርድ ቤቶቹ ግዴታ ነው፡፡ በመሆኑም ፍርድ ቤቶች የተገልጋዩን ፍላጎትና ምርጥ ተሞክሮዎችን ያገናዘበ የአገልግሎት ስታንዳርድ የማውጣት በስታንዳርዱ መሠረት አገልግሎት የመስጠትና ተገልጋዮችን በአክብሮት በመያዝ ግዴታ ተግባራቸውን ያከናውናሉ፡፡ ተገልጋዮች የሚፈልጉትን መረጃና አገልግሎት በቅልጥፍናና በጥራት የመስጠት ዝግጅትም ይኖራቸዋል፡፡ የተገልጋዮችን አስተያየት በየጊዜው በመሰብሰብ የማሻሻያ እርምጃዎችን በመውሰድ ይሰራሉ፡፡

### ሀቀኝነት፤

የፍርድ ቤት ውሳኔዎች በህግ፣ አግባብነት እና ተቀባይነት ባላቸው ማስረጃዎች ላይ ብቻ ይመሰረታሉ፤

## 2.2. ቁልፍ የውጤት መስኮች፣ ግቦች፣ ስትራቴጂዎች ፣ ውጤቶች እና ውጤት አመልካቾች

በዚህ ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ትግበራ ዘመን የፌደራል ፍርድ ቤቶች ተልዕኳቸውን ለማሳካት በሚከተሉት ስድስት ቁልፍ የውጤት መስኮች ላይ አትኩረው ይሰራሉ፡፡

### 2.2.1. ቁልፍ የውጤት መስኮች

ቁልፍ የውጤት መስክ 1፦ የዳኝነት ነፃነት፣ ገለልተኛነት፣ግልጽነት እና ተጠያቂነት

ቁልፍ የውጤት መስክ 2፦ የዳኝነት ቅልጥፍና እና ጥራት

ቁልፍ የውጤት መስክ 3፦ የዳኝነት ተደራሽነት

ቁልፍ የውጤት መስክ 4፦ ስትራቴጂያዊ አጋርነት እና ውጤታማ ኮሚዩኒኬሽን

ቁልፍ የውጤት መስክ 5፦ ተቋማዊ ለውጥና ብቃት

ቁልፍ የውጤት መስክ 6፦ የላቀ የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀም

### 2.2.2. የቁልፍ የውጤት መስክ ማብራሪያዎች

## ቁልፍ የውጤት መስክ 1፦ የዳኝነት ነፃነት፣ ገለልተኛነት፣ ግልጽነት እና ተጠያቂነት

በዚህ የውጤት መስክ የተገለጹ መርሆዎችን ውጤታማ ለማድረግ በርካታ ተግባራት ታቅደዋል። የዳኝነት ነጻነትን ለማረጋገጥ በአንድ በኩል ከአስፈጻሚው እና ከህግ አውጪው አካል ጋር ያለውን መስተጋብር ከማጎልበት፣ ግንዛቤን ከማዳበር፣ ህጎች ከመጽደቃቸው በፊት በሚኖረው ሂደት የዳኝነት አካል ምልከታ ሊኖር የሚችልበትን ስርዓት ከመዘርጋት እና የውሳኔ ነጻነትን ከማጎልበት ባሻገር በስራ ላይ ያሉ የዳኝነት አካል ነጻነት ላይ እንደምታ ያላቸው ህጎች ተፈትሸው ማሻሻያዎች ይደረጋሉ። በሌላ በኩል በአሰራር ምክንያት የዳኝነት ነጻነት ላይ እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮች ተለይተው መፍትሄ የሚያገኙ ሲሆን የዳኞች ሥልጠናና ሙያዊ ልማትን ለማጎልበት ፍርድ ቤቶች የራሳቸው የሆነ የስልጠና ስርዓት ለመዘርጋትና ማሰልጠኛ ተቋም ለማደራጀት የሚያስችሉ ተግባራት ይከናወናሉ። ገለልተኛ የዳኝነት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት የባህል፣ የሀይማኖት፣ የግል አመለካከት፣ የልዩ ልዩ ቡድኖች እና ሌሎች ተጽዕኖዎችን ለይቶ መፍትሄ ለመስጠት የሚረዱ ስራዎች በዕቅዱ ተካትተዋል። የዳኝነት አገልግሎትን ግልጽነት በተላበሰ መልኩ ለመስጠት የሚያስችሉ ተግባራትን በማከናወን ከተገልጋይ የሚቀርቡ ቅሬታዎች፣ ጥቆማዎች እና አቤቱታዎች የሚስተናገዱባቸው አሰራሮችን አሻሽሎ የሚሰጡ ምላሾች ግልጽነት የሚረጋገጥበት አሰራር ትኩረት ተሰጥቶታል። ተቋማዊ እና ግለሰባዊ ተጠያቂነት ሊረጋገጡባቸው የሚችሉ አሰራሮችን መዘርጋት፣ ማጠናከር፣ ውጤታማነታቸውን ማረጋገጥ... የሚያስችሉ ስትራቴጂያዊ ተግባራትም በዚህ የውጤት መስክ ውስጥ ተካተዋል።

| ስትራቴጂያዊ ግቦች | ስትራቴጂዎች | የግብ ውጤቶች (Outcomes) | አመልካቾች (Indicators) |
|---|---|---|---|
| 1.1. የዳኝነት ነጻነት እና ገለልተኝነትን ማረጋገጥ | 1.1.1. የዳኝነት ነጻነት የሚሸረሽሩ ህጎች እና አሰራሮች እንዲሻሻሉ ማድረግ፤<br>1.1.2. በዳኝነት ነጻነት ግንዛቤ እና አተገባበር ላይ ዕንቅፋት የሆኑ ችግሮችን መለየትና መፍትሄ እንዲያገኙ ማድረግ፤<br>1.1.3. የበጀት አመዳደብ እና አስተዳደር ነጻነት እንዲኖር ማድረግ፤<br>1.1.4. የዳኞችን ሁለንተናዊ ደህንነት ማረጋገጥ፤<br>1.1.5. የዳኝነት ስልጠና ስርዓት መዘርጋት እና መተግበር፣<br>1.1.6. የዳኝነት ገለልተኝነትን ማረጋገጥ፣ | • የዳኝነት ነጻነትና ገለልተኝነትን የሚያረጋግጥ የሕግ ማዕቀፍ ተዘጋጅቷል፣<br>• በቂ በጀት ተመድቦ ለተገቢው አገልግሎት ውሏል፣ | • የዳኝነት ነጻነት እና ገለልተኝነት ዕድገት በመቶኛ |
| 1.2. የዳኝነት ግልጽነት እና ተጠያቂነት ሥርዓትን ማጠናከር | 1.2.1. የፍርድ ቤቶች አሰራርና አገልግሎቶች ለሕዝብ ግልጽ ማድረግ፣<br>1.2.2. የግልጽ ችሎቶች አገልግሎቶችን ማጠናከር፣<br>1.2.3. የፍርድ ቤቶችን የሪፖርት አቀራረብ ስርዓት ማሻሻል፣<br>1.2.4. ግልጽ አሰራርን የተከተለ የዳኝነት ተጠያቂነት ስርዓት ማጠናከር፣ | • የዳኝነት ግልጽ አሰራር እና ተጠያቂነት ጎልብቷል፤ | • በተዘረጉ ስርዓቶች የተሰጡ አገልግሎቶች ዕድገት በመቶኛ |

## ቁልፍ የውጤት መስክ 2፦ የዳኝነት ቅልጥፍና እና ጥራት

በጉዳዮች ፍሰት አመራር እና አስተዳደር ስርዓት የተቀመጡ የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርዶችን ተግባራዊ በማድረግ የዳኝነት ጥራትና ቅልጥፍናን የሚሻሽሉ ተግባራት ትኩረት ተሰጥቷቸዋል። ለቅልጥፍና እድገት ተግዳሮት የሆኑት ጉዳዮችን ለይቶ በመፍታት፣ስታንዳርድ አውጥቶ በመተግበር፣አግባብነት ያላቸው የሥነ

ሥርዓት ህግ ድንጋጌዎችን ለይቶ በማሻሻል፣ የዳኞች ውጤታማነትን በማሳደግ፣ በሚሰጡ ፍርዶች አፈጻጸም ላይ ዘላቂነት ያለው ሁለንተናዊ ለውጥ የሚያመጡ ማሻሻያዎችን በማድረግ የፍርድ ቤቶችን እና የተገልጋዮችን ጊዜና ወጪ መቆጠብ የሚያስችሉ ተግባራት ታቅደዋል፡፡ ጥራትን ለማረጋገጥ የጉዳዮች ፍሰት አመራርና አስተዳደር ስርዓትን ተግባራዊ የማድረግ፣ የሰበር ችሎት አደረጃጀትና አሰራር ስርዓትን የማስተካከል፣ የጥናት እና ምርምር ስራዎችን የማጠናከር ተግባራት የዕቅዱ አካል ሆነዋል፡

| ስትራቴጂያዊ ግቦች | ስትራቴጂዎች | የግብ ውጤቶች (Outcomes) | አመልካቾች (Indicators) |
|---|---|---|---|
| 2.1. የዳኝነት አገልግሎት ቅልጥፍና ማሳደግ | 2.1.1. የሬጅስትራር አገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነትን ማሻሻል፤<br>2.1.2. የዳኞች ትጋትና ውጤታማነት የሚጨምሩ ስርዓቶችን ማጠናከር፤<br>2.1.3. የተፋጠነ እና አጭር ስነ-ስርዓት አተገባበርን ማጠናከር<br>2.1.4. የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር ስርዓት በተሟላ መልኩ መዘርጋትና መተግበር፤<br>2.1.5. ውዝፍ መዛግብትን መቀነስ የሚያስችል ስልት ዘርግቶ መተግበር፤<br>2.1.6. የፍርድ አፈጻጸም ውጤታማነት የሚያጎለብቱ የአሰራር፤አደረጃጀት እና የሰው ኃይል አቅምን ማጠናከር፤ | • ፍርድ ቤት የሚቀርቡ ጉዳዮች ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ እና ወጪ ዕልባት አግኝተዋል | • የሬጅስትራር አገልግሎት ዕድገት በመቶኛ<br>• በተቀመጠላቸው ጊዜ ዕልባት ያገኙ መዛግብት ዕድገት በመቶኛ<br>• ያደገ የማጥራት ምጣኔ በመቶኛ<br>• የተፈጸሙ ፍርዶች ዕድገት በመቶኛ |
| 2.2. የዳኝነት ጥራት ማጎልበት | 2.2.1. አሳታፊና ግልጽ አሰራርን የተከተለ የአገልግሎት ጥራት ደረጃ አዘጋጅቶ መተግበር፤<br>2.2.2. ውጤታማ የችሎት አደረጃጀት ሥርዓት መዘርጋትና መተግበር ፤ | • የውሳኔዎች ፍትህዊነት እና ተገማችነት ጎልብቷል | • የጥራት ደረጃን ያሟሉ ውሳኔዎች እድገት በመቶኛ<br>• ይግባኝ/በሰበር የጸኑ ውሳኔዎች ዕድገት በመቶኛ |

| ስትራቴጂያዊ ግቦች | ስትራቴጂዎች | የግብ ውጤቶች (Outcomes) | አመልካቾች (Indicators) |
|---|---|---|---|
| | 2.2.3. በሰበር ችሎቶች አደረጃጀት፣ አሰራር፣ በዳኞች አሰያየም... ላይ ማሻሻያዎችን ማድረግ፤<br>2.2.4. የውሳኔዎችን ምክንያታዊነት ማሳደግ፤<br>2.2.5. የጥናት፣ የምርምር እና የዕውቀት አስተዳደር ስራዎችን ማጠናከር፤<br>2.2.6. የባለጉዳዮች አያያዝ ስርዓት ዘርግቶ መተግበር፤ | | |

## ቁልፍ የውጤት መስክ 3፡- የዳኝነት ተደራሽነት

ውሳኔ ለማግኘት እንቅፋት የሆኑ ችግሮችን ለይቶ መፍትሄ ለመስጠት ባለጉዳዮች አገልግሎቶችን በቀላሉ ማግኘታቸውን፣ ልዩ ፍላጎት ላላቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች ምቹ የአገልግሎት ማግኛ ከባቢዎች መዘጋጀታቸውን፣ በቂ የህግ ድጋፎች (የተከላካይ ጠበቃ፣የቃል እና የሰነድ ትርጉም አገልግሎት...) መደረጋቸውን፣ የዳኝነት ክፍያ ተመን የተገልጋዮችን አቅም ማገናዘቡን፣ መረጃዎች በተለያዩ ዘዴዎች መሠራጨታቸውን፣አማራጭ የውሳኔ ማግኛ ዘዴዎች መመቻቸታቸውን... በመገምገም የተለዩ ክፍተቶችን የሚሞሉ እርምጃዎችን መውሰድ ትኩረት የተሰጣቸው የዕቅዱ አካል ናቸው። ዉክልና በተነሳባቸዉ ክልሎች የፌደራል ፍርድ ቤቶችን ማደራጀት፣ ዉክልና ባልተነሳባቸዉ ክልሎች የሚሰጡ የዳኝነት አገልግሎቶች ክትትልና ድጋፍ ማሻሻል ፣ የህጻናት፣የተዘዋዋሪ እና የፕላዝማ ችሎቶችን ተደራሽነት ማሳደግ የሚያስችሉ ተግባራት በዕቅዱ ተካትተዋል።

| ስትራቴጂያዊ ግቦች | ስትራቴጂዎች | የግብ ውጤቶች (Outcomes) | አመልካቾች (Indicators) |
|---|---|---|---|
| 3.1. የፍርድ ቤቶችን የአገልግ ሎቶችና አሰራሮች | 3.1.1. ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም የዳኝነት አገልግሎት ተደራሽነትን ማሳደግ፤<br>3.1.2. የዳኝነት አገልግሎት መረጃዎችን ተደራሽነት ማሳደግ | • የፌደራል ፍርድ ቤቶች አገልግሎቶችና አሰራሮች ለተገልጋዮች ያላቸው ተደራሽነት ጨምሯል | • በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ተደራሽ የሆኑ ተገልጋዮች ዕድገት በመቶኛ |

| ስትራቴጂያዊ ግቦች | ስትራቴጂዎች | የግብ ውጤቶች (Out-comes) | አመልካቾች (Indi-cators) |
|---|---|---|---|
| ተደራሽነት ማሳደግ | 3.1.3. የተከላካይ ጠበቆች ጽ/ቤት አደረጃጀትና አሰራር ስርዓት ማሻሻልና አገልግሎት አሰጣጥን ማጠናከር፤<br>3.1.4. የፍርድ ቤት መር አስማሚነት ስርዓትን ማጠናከር፤<br>3.1.5. የፍርድ ቤት አሰራርና አገልግሎት ልዩ ትኩረት ለሚሹ የሕብረተሰብ ክፍሎች ያላቸውን ተደራሽነት ለማሳደግ የሚያስችሉ አደረጃጀቶችና ስርዓቶችን ማጠናከር<br>3.1.6. የተሟላ የቋንቋ ትርጉም አገልግሎት ስርዓት መዘርጋትና መተግበር፤ | | • የተከላካይ ጥብቅና አገልግሎት ተጠቃሚዎች ዕድገት በመቶኛ<br>• በፍርድ ቤት መር አስማሚነት እልባት ያገኙ ጉዳዮች ዕድገት በመቶኛ<br>• ልዩ ትኩረት ለሚሹ የማህበረሰብ ክፍሎች በተዘረጋ ስርዓት ተጠቃሚዎች ዕድገት በመቶኛ<br>• በተጠየቁ ቋንቋዎች የትርጉም አገልግሎት ያገኙ ተገልጋዮች ዕድገት በመቶኛ |
| 3.2. የፍርድ ቤቶችን አካላዊ ተደራሽነት ማሳደግ | 3.2.1. የሕዝብን ብዛት ታሳቢ ያደረገ የፍርድ ቤቶች አደረጃጀት ስርዓት ዘርግቶ መተግበር፤<br>3.2.2. በጥናት በተለዩ የክልል ከተሞች የፌደራል ፍርድ ቤቶችን ማደራጀት፤<br>3.2.3. ተዘዋዋሪ ችሎቶች በሰው ኃይል፣ በሎጅስቲክና በቅንጅታዊ አሰራር የሚጠናከሩበትን ስርዓት መዘርጋት፣ በሂደትም ቋሚ ችሎቶች ማደራጀት፣<br>3.2.4. የፍርድ ቤቶችን የስራ ቦታዎችና መገልገያዎች ለተገልጋዮች ተደራሽና ምቹ የሚያደርጉ የመሠረተ ልማት አውታሮችን ማጠናከር፤ | • የፌደራል ፍርድ ቤቶች አካላዊ ተደራሽነት ጎልብቷል | • የፌደራል ዳኝነት አገልግሎት ለመስጠት በክልል የተደራጁ ፍርድቤቶችና ማዕከላት ዕድገት በመቶኛ<br>• በተዘዋዋሪ ችሎቶች ዕልባት ያገኙ ጉዳዮች ዕድገት በመቶኛ፣<br>• የተደራጁ ቋሚ ችሎቶች ብዛት በቁጥር፣ |

## ቁልፍ የውጤት መስክ 4፡ ስትራቴጂያዊ አጋርነትና ውጤታማ ኮሚዩኒኬሽን

ፍርድ ቤቶች ተልኳቸውን ለማሳካት ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር የሚኖራቸውን ትብብርና ቅንጅት ማጠናከር ይጠበቅባቸዋል፡፡ ስትራቴጂያዊ አጋርነት እና የሕዝብ ግንኙነት ስራዎች ገጽታና ብቃትን ለመገንባት፣ ሀብት ለማሰባሰብ፣ የሕዝብ ግንዛቤንና ተሳትፎ ለማሳደግ፣ የመረጃ ለውውጥን ለማሻሻል፣ ተሞክሮ ለመቅሰም እና ለማስፋፋት የሚያግዙ በመሆናቸው በዕቅዱ ውስጥ ትኩረት ተሰጥቷቸዋል፡፡

| ስትራቴጂያዊ ግቦች | ስትራቴጂዎች | የግብ ውጤቶች (Out-comes) | አመልካቾች (Indi-cators) |
|---|---|---|---|
| 4.1. አገራዊና ዓለም አቀፋዊ አጋርነትና ድጋፍን ማሳደግ | 4.1.1. የፍርድ ቤቶችን ዓለም አቀፍ ግንኙነትና ትብብር ለማጠናከር የሚያስችል ስርዓት ዘርግቶ መተግበር ፤<br>4.1.2. ፍርድ ቤቶች ከተመረጡ የትምህርት፣ ሥልጠና እና ምርምር ተቋማት ጋር የሚኖራቸውን ትስስርና ትብብር ለማሳደግ የሚያግዝ ስርዓት ዘርግቶ መተግበር፤<br>4.1.3. ከፌደራል እና ከክልል የፍትህ አካላት ጋር በመርህ ላይ የተመሠረተ አጋርነትና ግንኙነት የሚያጠናክር ስርዓት ዘርግቶ መተግበር፤<br>4.1.4. የፌደራልና የክልል ፍ/ቤቶች ግንኙነት እና የአቅም ግንባታ ሥርዓትን ማጠናከር፤<br>4.1.5. ከህግ ባለሙያ/ጠበቆች ማህበሮች ጋር የሚኖር አጋርነትን ለማሳደግ የትብብርና የግንኙነት ሥርዓቶችን መዘርጋትና ማጠናከር | • ፍርድ ቤቶች ያገኟቸው የቴክኒክና ሌሎች የሃብት ድጋፎች ጨምረዋል፥<br>• ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር አድጓል | • ፍርድ ቤቶች ከባለድርሻ አካላት ጋር የፈጠሯቸው የትብብር ማዕቀፎች ዕድገት በመቶኛ<br>• የተገኘ የቴክኒክና ፋይናንስ ግብዓት ዕድገት በመቶኛ<br>• የማሻሻያ ስራዎች ብዛት በቁጥር |
| 4.2. የህዝብ ግንዛቤ እና ተሳትፎን ማሳደግ | 4.2.1. የኮሚዩኒኬሽን ሥራ ክፍሎችን አደረጃጀትና አሰራር ማጠናከር፤ | • ስለ ፍርድ ቤቶች አሰራር የህዝብ ግንዛቤ እና ተሳትፎ ተሻሽሏል፤ | • የህዝብ ግንዛቤና ተሳትፎ ለማሳደግ ታቅደው የተከናወኑ ተግባራት ዕድገት በመቶኛ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | 4.2.2. የፌደራል ፍርድ ቤቶች መለያዎችን ማዘጋጀትና ማስረጽ ፣<br>4.2.3. ህዝቡን ማዕከል ያደረጉ ቋሚ የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሐ-ግብሮች ማዘጋጀት እና መተግበር<br>4.2.4. የህዝብ አመለካከት/አስተያየት መዳሰስ የሚያስችል ስርዓት ዘርግቶ መተግበር | | |

## ቁልፍ የውጤት መስክ 5፦ ተቋማዊ ለውጥና ብቃት

የዕውቀት፣ ክህሎት፣ አመለካከት፣ የግብዓት፣ የአሠራር እና የአደረጃጀት ክፍተቶችን ለመሙላት የሰው ኃብት ልማት ማጠናከር፣ የፋይናንስና ንብረት አጠቃቀምን ማሻሻል፣ የተቀናጀና ተመጋጋቢ የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት፣ የአደረጃጀት ማሻሻያ ማድረግ፣ ምርጥ ተሞክሮን መሠረት ያደረገ ተቋማዊ የአገልግሎት ልህቀት ማምጣት... የሚያስችሉ ተግባራት በዕቅዱ ተካትተዋል።

| ስትራቴጂያዊ ግቦች | ስትራቴጂዎች | የግብ ውጤቶች (Outcomes) | አመልካቾች (Indicators) |
|---|---|---|---|
| 5.1. የመምራት እና የመፈጸም ብቃትን ማሳደግ | 5.1.1. ተቋማዊ የሰው ኃይል አደረጃጀትና አሰራር ስርዓት ማጠናከር፤<br>5.1.2. በፍርድ ቤቶቹ ፍላጎት ላይ የተመሠረተ የትምህርትና ሥልጠና ስርዓት ማጠናከር፤<br>5.1.3. የአመራሮችና ሠራተኞችን የስራ ተነሳሽነት ለማሳደግ የሚያስችል ስርዓት ዘርግቶ መተግበር፤<br>5.1.4. በፍርድ ቤቶች ፍላጎትና ግብ ላይ የተመሠረተ ተሞክሮዎችን መቅሰም እና ማስፋፋት፤<br>5.1.5. ተተኪ የሥራ መሪዎችን ማፍራት የሚያስችል ስርዓት መዘርጋትና መተግበር፣ | • የአፈጻጸም ለውጥ አድጓል፤<br>• የስራ ተነሳሽነት አድጓል፤<br>• ለአመራርነት ብቁ የሆኑ ሰራተኞች ቁጥር ጨምሯል፤ | • የፍርድ ቤቶች ስትራቴጂያዊ አፈጻጸም ውጤት እድገት በመቶኛ፤ |

| ስትራቴጂያዊ ግቦች | ስትራቴጂዎች | የግብ ውጤቶች (Outcomes) | አመልካቾች (Indicators) |
|---|---|---|---|
| 5.2. የፋይናንስ እና ንብረት ውጤታማነትን ማሳደግ | 5.2.1. ውጤታማ የኃብት አጠቃቀም ሥርዓት ዘርግቶ መተግበር፤<br>5.2.2. የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር አደረጃጀትን ማሻሻል፤<br>5.2.3. የክዋኔና ፋይናንስ ኦዲት ሥርዓትን አጠናክሮ ተጠያቂነትን ተግባራዊ ማድረግ፤ | • የበጀት አፈፃፀም ውጤታማነት አድጓል፤<br>• የግዥና ክፍያ ቅልጥፍና እና ጥራት ጨምሯል፤<br>• የኦዲት ግኝቶች ቀንሰዋል፤<br>• የንብረት አስተዳደር ውጤታማ ሆኗል፣ | • ውጤታማነት የበጀት አጠቃቀም ዕድገት በመቶኛ፤<br>• የአቅራቢዎችና የተገልጋዮች እርካታ ዕድገት በመቶኛ፤<br>• የቀነሰ የኢንስፔክሽን እና የኦዲት ግኝት በመቶኛ፤ |
| 5.3. የሴቶችን ተሳትፎ ማሳደግ | 5.3.1. የሴቶች ተሳትፎ ማሳደጊያ ፕሮግራም ቀርጾ መተግበር<br>5.3.2. ከስራ ጋር የተያያዙ የጾታዊ ትንኮሳ መንስዔዎችን ለይቶ መቀነስ | • የሴቶች ተሳትፎ አድጓል | • ያደገ የሴቶች ተሳትፎ በመቶኛ |

## ቁልፍ የውጤት መስክ 6፦ የላቀ የኢንፎርሜሽን ኮምዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀም

ቀደም ብሎ ከተዘጋጀው የፍርድ ቤቶች የኢኮቴ ማሻሻያ ፕሮግራም በመነሳት በኢንፎርሜሽን ኮምዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት ግንባታ፣ በሶፍትዌር ልማት እና ተጠቃሚነት አቅም ግንባታ ላይ ያተኮሩ ተግባራትን ለማከናወን ታቅዷል ።

| ስትራቴጂያዊ ግቦች | ስትራቴጂዎች | የግብ ውጤቶች (Out-comes) | አመልካቾች (Indi-cators) |
|---|---|---|---|
| 6.1 የኢኮቴ አጠቃቀም ውጤታማነት ማሳደግ | 6.1.1. የኢኮቴ መሠረተ ልማትን ማጎልበትና ማዘመን፤<br>6.1.2. የኢኮቴ መተግበሪያዎችን ዓይነት፣ ብዛት እና አጠቃቀም ማሳደግ፤<br>6.1.3. ግብዓቶችን ማሟላት፤<br>6.1.4. የኢኮቴ ፖሊሲና ስትራቴጂ ማዘጋጀትና ተግባራዊ ማድረግ<br>6.1.5. የሥራ ክፍሉን ማጠናከር | • ዋና ዋና የፍርድ ቤት ሂደቶችና አገልግሎቶች አውቶሜትድ ሆነዋል፤ | • አውቶሜትድ የሆኑ ሂደቶችና አገልግሎቶች ቁጥር ዕድገት በመቶኛ |
| 6.2. የኢኮቴ ዕውቀትና ክህሎትን ማሳደግ | 6.2.1 ለሠራተኞችና ሥራ መሪዎች በኢኮቴ አጠቃቀም ላይ ሥልጠና መስጠት<br>6.2.3. የኢኮቴ መገልገያዎች በውስጥ አቅም የመጠገን አቅምን ማሳደግ፤<br>6.2.4. የዳኞችና ሠራተኞችን የኢኮቴ ተጠቃሚነት ዕድገት ማረጋገጥ፣ | • የኢኮቴ ተጠቃሚነት አድጓል፤ | • የኢኮቴ ተጠቃሚነት ዕድገት በመቶኛ |

# ክፍል ሦስት

## 3 የትግበራ መርሐ - ግብር እና ስልቶች

የዚህ ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ውጤታማ አተገባበር የስራ ድርሻና ኃላፊነቶች ግልጽ መሆናቸውን፣ የስትራቴጂያዊ ዕቅዱን በሁሉም አካላት ባለቤትነት መተግበርን፣ እንዲሁም አግባብነት ያላቸው የሰው ኃይል፣ የፋይናንስና ሌሎች ግብዓቶች በበቂ ሁኔታ መመደባቸውና ጥቅም ላይ በአግባቡ መዋላቸውን ይጠይቃል። ይህም በሁሉም የፍርድ ቤቶች የአስተዳደር ደረጃዎች የስትራቴጂያዊ ዕቅዱን አተገባበር መምራትና ማስተባበር አስፈላጊ ይሆናል። እንዲሁም የስትራቴጂያዊ ዕቅዱን በሁሉም የፍርድ ቤት ደረጃዎች፣ ለስራ ክፍሎች እና ሠራተኞች ማውረድ (cascade) ያስፈልጋል። በተጨማሪም ስትራቴጂውን ለማስፈጸም የሚያስችል ድርጅታዊ መዋቅር፣ የሰው ኃይል ምደባ፣ የክትትልና የግምገማ ስርአት፣ ዕቅዱን የማስተዋወቅ ሥራ፣ እንዲሁም ውጤታማ የሆነ የኃብት ማሰባሰብና አጠቃቀም ይጠይቃል።

### 3.1. የስትራቴጂያዊ ዕቅድ አተገባበርን የመምራትና የማስተባበር ኃላፊነቶች

የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ስትራቴጂያዊ ዕቅዱ በሶስቱም ፍርድ ቤቶች የሚኖረውን አጠቃላይ አተገባበር ይመራሉ፤ ይከታተላሉ። በከፍተኛና በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች ደረጃ የሚኖረውን የስትራቴጂያዊ ዕቅድ አተገባበር በዋናነት የየፍርድ ቤቶቹ ፕሬዝዳንቶች ይመራሉ፤ ይከታተላሉ።

የስትራቴጂክ ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት የስትራቴጂያዊ ዕቅዱን የቀን ተቀን አተገባበር የማስተባበር ኃላፊነት ያለበት ሲሆን የስትራቴጂያዊ ዕቅዱን አፈፃጸም በተመለከተም መደበኛ የክትትል ተግባር ያከናውናል። ከዚህም በተጨማሪ የስትራቴጂያዊ ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት በሌሎች የፌደራል ፍርድ ቤቶች ከሚገኙ የዕቅድ ዝግጅት ክትትልና ግምገማ የሥራ ክፍሎች ጋር በመሆን ስትራቴጂውን ከማጽፈጸም አኳያ የማቀድ፣ የመከታተልና የመገምገም አቅም እንዲገነባ ያደርጋል። ዕቅዱን ለማስተግበር የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት የሚዘረጋ ከመሆኑም በላይ ሥርዓቱን የማጠናከር ስራ ያከናውናል።

### 3.2. ስትራቴጂያዊ ዕቅዱን ወደ እያንዳንዱ ፍርድ ቤትና የስራ ክፍል ማውረድ (cascading)

የጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከዚህ ስትራቴጂያዊ ዕቅድ የሚቀዳ ዓመታዊ ዕቅድ ያዘጋጃሉ። ዓመታዊ ዕቅዶች መነሻቸው ዓመታዊ ዒላማዎችና ዒላማዎቹን

ለማሳካት በዝርዝር የቀረቡት ቁልፍ ተግባራት ይሆናሉ። በተጨማሪም በሦስቱም ፍርድ ቤቶች ደረጃ ያሉ ሁሉም ችሎቶች፣ ዳይሬክቶሬቶችና ቡድኖች ከዚህ ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ጋር የተዛመደ የሥራ እቅድ እንዲያዘጋጁ ይደረጋል። እያንዳንዱ ዳኛና የአስተዳደር ሠራተኛም የየዕለት ሥራውን በአግባቡ ከስትራቴጂያዊ ዕቅዱ ጋር በማስተሳሰር ዓመታዊ ዕቅድ ይኖረዋል። በሁሉም ፈጻሚ ደረጃ ዓመታዊ ዕቅዶች በየሩብ ዓመቱ ተሸንሽነው የሚቀርቡ ይሆናል። በአጠቃላይ ስትራቴጂያዊ ዕቅዱን ወደታች ለማውረድና ከኦፕሬሽን ጋር ለማስተሳሰር እንዲረዳ በእያንዳንዱ ቁልፍ የውጤት መስክ ስር ዝርዝር የትግበራ መርሐ-ግብር ሰንጠራዥ አባሪ 1 ሆኖ ከዚህ ስትራቴጂ ጋር ተካትቷል ።

## 3.3. የፍርድ ቤቱን ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል ስምሪት ማሻሻል

የዚህ ስትራቴጂያዊ ዕቅድ የተሟላና ውጤታማ አተገባበር የተለያዩ የተቋማዊ አደረጃጀት ለውጦችን የግድ ይላል። በርግጥ የፌደራል ፍርድ ቤቶች ተቋማዊ አደረጃጀትን በመከለስ ከተሻሻለው የፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅና ከፍርድ ቤቶች የለውጥ ሂደቶች ጋር ለማጣጣም ሥራዎች ተጀምረዋል። በዚህም መሠረት የፌደራል ፍርድ ቤቶች የአስተዳደር ሰራተኞች አቅም፣ ተቋማዊ አደረጃጀት እና አሰራር የፈተሹና የተለዩ ክፍተቶችን ለመሙላት የሚያስችሉ የመፍትሄ ሃሳቦችን ያስቀመጠ ጥናት ተደርጓል። የተጀመረው የፍርድ ቤቶችን ተቋማዊ አደረጃጀት የመከለስና የማሻሻል ሥራ ይህን ስትራቴጂያዊ እቅድ በውጤታማነት ለማስፈጸም በሚያስችል መልኩ ሊከናወን ይገባዋል። የስትራቴጂው ውጤታማ አተገባበር ከአደረጃጀት ለውጥ በተጨማሪ ብቃትና አግባብነት ያለው የሰው ኃይል በየአንዳንዱ የስራ ክፍል መመደብ ይጠይቃል። በተለይም ለፍርድ ቤቶቹ የሚያስፈልገውን የዳኛ መጠን በወቅቱ እያጠኑ ፍርድ ቤቶቹ በተገቢው የዳኛ መጠን ስራቸውን እንዲያከናውኑ ማድረግም ያስፈልጋል።

## 3.4. የሀብት ማሰባሰብና ውጤታማ አጠቃቀም

ስትራቴጂውን ለማስፈጸም የሚያስፈልገውን የፋይናንስ ሀብት ማግኘት ለስትራቴጂው ውጤታማ አተገባበር ወሳኝ ነው። ከዚህ አንፃር የመጀመሪያ ስራ የሚሆነው ስትራቴጂውን የተሟላና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመተግበር የሚያስፈልገውን የሀብት መጠን ከግምት ባለፈ በጥናት ላይ ተመስርቶ መለየት ነው። ፍርድ ቤቱ የሚያስፈልገውን በጀት ለማግኘት ከተለያዩ አማራጭ ምንጮች የሀብት ማሰባሰቢያ ስትራቴጂ አውጥቶ ይተገብራል። ይህ ስትራቴጂ በሕገ መንግስቱ መሰረት በየጊዜው እየጨመረ የሚሄድ በጀት ማግኘትን፣ በቂ በጀት እንዲመደብ በየጊዜው መግባባት፣ መተግበርና የበጀት አጠቃቀምንም ውጤታማ ማድረግ ላይ ያተኩራል። ሌሎች ሃብቶችም ከመንግስታዊም ሆነ ሌሎች አጋሮች የሚገኙበትን ስትራቴጂ በመንደፍና በመተግበር በቂ የፋይናንስና የቴኪኒክ ድጋፍ መሳብ ትኩረት ይሰጠዋል።

## 3.5. ስትራቴጂያዊ ዕቅዱን ማስተዋወቅና ግንዛቤ መፍጠር

የውስጥና የውጭ ባለድርሻ አካላት ስለ ስትራቴጂያዊ ዕቅዱ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ፍርድ ቤቱ የተለያዩ ተግባራትን ያከናውናል። ከነዚህም ውስጥ ለዳኞችና የአስተዳደር ሰራተኞች በስትራቴጂያዊ ዕቅዱና የማስፈጸሚያ ስልቶቹ ላይ ስልጠናዎችን ያዘጋጃል። ወደፊት የሚቀጠሩ ሰራተኞች በስትራቴጂያዊ ዕቅዱ ላይ ማብራሪያ ይሰጣቸዋል። ፍርድ ቤቱ ይህን ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ጥራቱን በጠበቀና በበቂ ኮፒዎች በማሳተም ለውስጥና ለውጭ ባለድርሻ አካላት በሰፊው እንዲሰራጭ ያደርጋል። እንዲሁም ስትራቴጂያዊ ዕቅዱ በፍርድ ቤቱ ድረ-ገጽ በስፋት እንዲተዋወቅ ይደረጋል።

# ክፍል አራት

## 4 የክትትልና ግምገማ ዕቅድ

የስትራቴጂያዊ ዕቅድ ክትትልና ግምገማ የስትራቴጂያዊ ዕቅድ ሥራ አመራር ሥርዓት ካሉት ምሰሶዎች አንዱ ነው። የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ስትራቴጂያዊ ዕቅድ (2014 – 2018) የሚከተሉትን ይዟል ።

- ተልዕኮ፣ እሴቶችና ራዕይ
- ስድስት ቁልፍ የውጤት መስኮችና የየቁልፍ የውጤት መስኩ ውጤት
- ስትራቴጂያዊ ግቦች፣ የየግቡ ውጤት፣ የየግቡ ውጤት አመልካችና የየውጤት አመልካቹ ዒላማ
- በየግቡ ሥር የተቀመጡ ቁልፍ ተግባራት

ይህ የስትራቴጂያዊ ዕቅድ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ዕቅድ በዕቅድ ትግበራው ሂደት ማለትም፣

- በመንፈቅ ዓመት
- በዓመት
- በየሁለት ዓመት
- በአምስት ዓመት ማጠቃለያ

የታቀዱ የውጤት አመልካቾችና ዒላማዎች አፈጻጸም ደረጃን ለማወቅ በሚያስችል መልኩ የተዘጋጀ ነው። ከዚህም በተጨማሪ በዚህ ክፍል የስትራቴጂያዊ ዕቅድ ክትትልና ግምገማ አስፈላጊነትና የሥራው አደረጃጀትና አካሄድ ቀርቧል። በተጨማሪም በእያንዳንዱ የግብ ውጤትና ቁልፍ ተግባራት ስር ዝርዝር የክትትልና ግምገማ አካሄድ ተመልክቷል።

### 4.1. የስትራቴጂያዊ ዕቅድ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ዕቅድ ዓላማዎች

የስትራቴጂያዊ ዕቅድ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ የስትራቴጂያዊ ዕቅድ ሥራ አመራር አንድ አካል ሲሆን የሚከተሉት ሦስት ተደጋጋፊ ዓላማዎች አሉት።

- ሥራ መሪዎችና ሠራተኞች በየዕለት ሥራቸው ተጨባጭ የአፈጻጸም መረጃን መሠረት ያደረገ

ውሳኔ እንዲሰጡ ማስቻል፣

- ተቋማዊ መማማርንና ቀጣይነት ያለው የአፈጻጸም መሻሻልን ማረጋገጥ፣
- ስትራቴጂያዊ ዕቅድን በመተግበር ሂደት በፌደራል ፍርድ ቤቶች ተጠያቂነትን ማጠናከር ናቸው።

## 4.2. የስትራቴጂያዊ ዕቅድ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ መዋቅርና ኃላፊነት

የስትራቴጂያዊ ዕቅድ አፈጻጸም ክትትል ግምገማና ሪፓርት አቀራረብ በሥራ ክፍሎችና በየፍርድ ቤቶቹ የሥራ አመራር እና በጠቅላይ ፍርድ ቤት የሥራ አመራር ደረጃ የሚከናወን ይሆናል። በየፍርድ ቤቶቹ የሚገኙ የዕቅድ ክትትልና ግምገማ የሥራ ክፍሎች የዕቅድ ክትትልና ግምገማ ሥራዎችን የማስተባበርና ሥርዓት የመዘርጋት ኃላፊነት አለባቸው። ከዚህም በተጨማሪ የዕቅድ ክትትልና ግምገማ የስራ ክፍሎቹ የአፈጻጸም መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በማጠናቀርና ወቅታዊ ሪፓርት በማዘጋጀት ሂደት መሪ ተዋናይ ናቸው። በሌላ በኩል እነዚህ የስራ ክፍሎች ለሌሎች የሥራ ክፍሎች የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማን በተመለከተ ሙያዊ ድጋፍ የመስጠትና የአቅም ግንባታ ሥራዎችን የማስተባበር ኃላፊነት አለባቸው ።

## 4.3. የስትራቴጂያዊ ዕቅድ አፈጻጸም ክትትል ግምገማና ሪፓርት አደራረግ

**የአፈጻጸም ክትትል** (Monitoring)፣ የስትራቴጂያዊ ዕቅድ አፈጻጸም ትግበራ አዘውትሮ በሚከናወን ቁጥጥር፣ መረጃ መሰብሰብ፣ መረጃ ማደራጀት፣ ሪፓርቶችን ማቅረብና ሪፓርቶችን በመገምገምና የማሻሻያ እርምጃዎችን በመውሰድ ይከናወናል። ቀደም ብሎ እንደተመለከተው የዕቅድ ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ የሥራ ክፍሎች እነዚህን ተግባራት በማስተባበርና በመደገፍ ላይ አትኩረው ይሠራሉ። የሥራ ክፍሎች በተሰጣቸው ተግባርና ኃላፊነት መሠረት ከስትራቴጂያዊ ዕቅዱ በመነሳት ያዘጋጁትን ዓመታዊ ዕቅድ አፈጻጸም በመከታተል በሩብ ዓመት፣ በመንፈቅ ዓመትና በዓመት በየሥራ ክፍሎቻቸው ሠራተኞች የተገመገመ የአፈጻጸም ሪፓርት ያቀርባሉ።

የሥራ ክፍሎች የዕቅድ አፈጻጸማቸውን የሚገመግሙት አስቀድሞ ከተቀመጡና የአፈጻጸም ውል ከተገባባቸው መለኪያዎችና ዒላማዎች አኳያ ሲሆን የግምገማ ትኩረቱም ከታቀደው ውጤትና ዒላማ አንጻር የተደረሰበትን አፈጻጸም ማመልከት ነው። በመሆኑም የአፈጻጸም ክትትሉ ትኩረት ውጤት ላይ መሆን አለበት።

**ግምገማ:** - የስትራቴጂያዊ ዕቅዱ መካከለኛ ዘመን ግምገማ የሚካሄደው በዕቅዱ ሁለተኛ ዓመት ማጠናቀቂያ ነው። የግምገማው ዓላማም በሁለተኛ ዓመት ማጠናቀቂያ ከሚጠበቀው ውጤት አንጻር የተደረሰበትን የውጤት ደረጃ በጥልቀት መመርመር ነው። ግምገማው የስትራቴጂያዊ ግቦች፣ የግቦች አፈጻጸም አመልካቾች አፈጻጸምን በጥልቀት መመርመርና ተጨባጭ የአፈጻጸም መረጃን መሠረት

ያደረገ የማስተካከያ እርምጃዎችን ይወስዳል። በዚህ ደረጃ የሚደረግ ግምገማ የቀሪዎቹን ሦስት ዓመታት ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ለመከለስ ይረዳል። የስትራቴጂያዊ ዕቅዱ ትግበራ ማለቂያ ላይ የዕቅድ ዘመን ማጠቃለያ ግምገማ (end-term evaluation) ይደረጋል። የመካከለኛ ዘመንም ሆነ የዕቅድ ዘመን ማጠቃለያ ግምገማዎች የሚካሄዱት የሚከተሉትን መስፈርቶች መሠረት በማድረግ ነው ።

- አግባብነት
- ውጤታማነት
- ቅልጥፍና
- የፌደራል ፍርድ ቤቶች አገራዊ ወይም የሴክተር አስተዋጽዖ
- ቀጣይነት

**የአፈጻጸም ሪፖርት:-** (Reporting)፣ በሚከተለው ሰንጠረዥ የቀረበው የክትትልና ግምገማ ሪፖርት ቅርጽ የታቀዱ ተግባራት ትግበራ መቀጠልንና የሚጠበቁ ውጤቶች በምን ዓይነት የአፈጻጸም ደረጃ ላይ እንደሚገኙ ለመገምገም የሚያስችል መረጃ ለሚመለከታቸው ሁሉ እንደፍላጎታቸው ለማቅረብ ነው።

| ሪፖርት | የሚያዘጋጀው | የሚያደራጀው/አጠቃሎ የሚያቀርበው | የሚቀርብለት |
|---|---|---|---|
| ዓመታዊ ሪፖርት | ሁሉም ዳይሬክቶሬቶችና ፍርድ ቤቶች | የስትራቴጂክ ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት | ለየፍርድ ቤቶች ፕሬዝዳንቶች እና ለማኔጅመንት ኮሚቴ |
| የመካከለኛ ዘመን ግምገማ ሪፖርት | የስትራቴጂክ ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት | የስትራቴጂክ ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት | ለየፍርድ ቤቶች ፕሬዝዳንቶች እና ለማኔጅመንት ኮሚቴ |
| የዕቅድ ዘመን ማጠቃለያ ግምገማ ሪፖርት | የስትራቴጂክ ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት | የስትራቴጂክ ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት | ለየፍርድ ቤቶች ፕሬዝዳንቶች እና ለማኔጅመንት ኮሚቴ |

# አባሪ 1

## የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የ2014-2018 ስትቴጂያዊ ዕቅድ የትግበራ መርሃግብር ሰንጠረዥ

## አባሪ 1፡- የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የ2014 - 2018 ስትቴጂያዊ ዕቅድ የትግበራ መርሃግብር ሰንጠረዥ

| ስትራቴጂዎች | ዋና ዋና ተግባራት | ውጤት (out-put) | አመልካች | መነሻ/ baseline | ዒላማ Target | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | ፈጻሚ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. ቁልፍ የውጤት መስክ 1፦የዳኝነት ነፃነት፣ ገለልተኛነት፣ ግልጽነት እና ተጠያቂነት | | | | | | | | | | | |
| 1.1. ስትራቴጂያዊ ግብ ፡- የዳኝነት ነጻነት እና ገለልተኝነት አተገባበርን ማሻሻል | | | | | | | | | | | |
| 1.1.1. የዳኝነት ነጻነትን ለማረጋzጥ የሚያግዙ ህጎች እና አሰራሮች ማጠናከር፣ | • በምክር ቤቱ ህጎች ከመጽደቃቸው በፊት በዳኝነት ነጻነት እና ስልጣን ላይ ያላቸውን እንደምታ ለመለየት የሚያስችል የማሻሻያ ሃሳብ ማቅረብ፤<br>• ስለ ዳኝነት ነጻነት ለአስፈጻሚና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ግንዛቤ ለማዳበር የሚያስችል ሰነድ ማዘጋጀትና ስልጠና መስጠት፤ | የዳኝነት ነጻነት የሚሸረሽሩ ህጎች እና አሰራሮች ተሻሽለዋል፤ | የተደረጉ የማሻሻያ ጥናቶች ብዛት በቁጥር | 2 | 5 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ፣ ፕሬዝደንቶች፣ ህግ ድጋፍና ምርምር ዳይሬክቶሬት፣ |
| | | | የተሻሻሉ አሰራሮች ብዛት በቁጥር | - | 1 | | | | | | |

| ስትራቴጂዎች | ዋና ዋና ተግባራት | ውጤት (out-put) | አመልካች | መነሻ/ baseline | ዒላማ Target | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | ፈጻሚ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | • አዲስ የወጡ ሕጎችን አተገባበርና የዳኝት ነፃነትን ያገናዘበ ስልጠና መስጠት፤ | | | | | | | | | | |
| 1.1.2. በዳኝነት ነጻነት ግንዛቤ እና አተገባበር ላይ ዕንቅፋት የሆኑ ችግሮችን መፍትሄ እንዲያገኙ ማድረግ፣ | • የዳኝነት ነጻነት ሊሸረሽሩ ይችላሉ የሚባሉ የዳኞች ስጋቶችን በጥናት መለየት<br>• በጥናት ግኝቶች ላይ ለባለድርሻ አካላት ግንዛቤ ለመፍጠር የሚያስችሉ መድረኮች ማመቻቸት<br>• የፍርድ ቤት አስተዳደራዊ ስራዎች ከዳኝነት ነጻነት ጋር ስላላቸው መስተጋብር የጋራ ግንዛቤ መፍጠር<br>• በአመራሩና በዳኞች መካከል የጋራ የውይይት መድረኮች ማመቻቸት | በዳኝነት ነጻነት ግንዛቤ እና አተገባበር ላይ ዕንቅፋት የሆኑ ችግሮች መፍትሄ አግኝተዋል፤ | የተዘጋጀ የጥናት ሰነድ | - | 1 | 1 | | | | | የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ፣ ፕሬዝደንቶች፣ ህግ ድጋፍና ምርምር ዳይሬክቶሬት |
| | | | በአመራሩና በዳኞች መካከል የተዘጋጁ የጋራ መድረኮች ብዛት በቁጥር | 10 | 15 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ፣ፕሬዝደንቶች፣ ህግ ድጋፍና ምርምር፣ ኮምዩኒኬሽን ዳይሬክቶሬት፣ |
| | | | የባለድርሻ አካላትን ግንዛቤ ለመጨመር የዘጋጁ የጋራ መድረኮች ብዛት በቁጥር | - | 10 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | |

| ስትራቴጂዎች | ዋና ዋና ተግባራት | ውጤት (out-put) | አመልካች | መነሻ/ baseline | ዒላማ Target | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | ፈጻሚ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1.1.3. የበጀት አመዳደብ እና አስተዳደር ነጻነት እንዲኖር ማድረግ፣ | • በሕገ መንግስቱ መሰረት፡- <br>• የዳኝነት አገልግሎትን በተሻለ ሁኔታ ለመስጠት የሚያስችል <br>• የበጀት ዕቅድ አዘጋጅቶ በህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ማስጸደቅ፤ <br>• የተፈቀደለትን በጀት የሚያስተዳድርበትና የፋይናንስ መርሆዎችን የተከተለ ደንብ/መመሪያ አውጥቶ መተግበር፤ | የበጀት አስተዳደር ነጻነት ተከብሯል፤ | ተዘጋጅቶ ተግባራዊ የተደረገ የበጀት ዕቅድ ሰነድ | 1 | 5 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | ፕሬዝደንቶች፣ ኮርት ማነጀሮች፤ ፋይናስ ዳይሬክቶሬት፣ ስትራቴጂክ ዳይሬክቶሬት |
| | | | የወጣና ተግባራዊ የተደረገ የበጀት አስተዳደር ደንብ | - | 1 | | 1 | | | | |
| | | | | | | | | | | | |
| 1.1.4. የዳኞችን ሁለንተናዊ ደህንነት ማረጋገጥ፣ | • በጥናት ላይ የተመሰረተ የዳኞች ደመወዝና ጥቅማ ጥቅምን ማስጠበቅ የሚያስችል | የዳኞች ሁለንተናዊ ደህንነት ተረጋግጧል፤ | ተግባራዊ የተደረገ የጥቅማ ጥቅም ፓኬጅ ደህንነትን ለማስጠበቅ | 1 | 1 | | | | | | የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ፣ ፕሬዝደንቶች፣ ኮርት |

| ስትራቴጂዎች | ዋና ዋና ተግባራት | ውጤት (out-put) | አመልካች | መነሻ/ baseline | ግብ Target | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | ፈጻሚ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | • በመደበኛ የፍርድ ቤት ጥበቃ ኃይል ማደራጀት<br>• በደህንነትና በጥቅማ ጥቅም ጉዳዮች ላይ ለሚመለከታቸው አካላት የግንዛቤ ማዳበሪያ መድረኮችን ማመቻቸት፤ | | ተግባራዊ የተደረጉ መመሪያዎች ብዛት በቁጥር | 1 | 4 | 2 | 2 | | | | |
| | | | መደበኛ የፍርድ ቤት ጥበቃ ስርዓት መተግበር | - | 1 | | | | | | |
| | | | የተዘጋጁ የስልጠና መድረኮች ብዛት በቁጥር | | 6 | 3 | | 3 | | | |
| 1.1.5. የዳኝነት ስልጠና ስርዓት መዘርጋት እና መተግበር፣ | • የዳኝነት ትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ እና ማንዋል ማውጣት፤<br>• የስልጠና ሲለበስ እና ፕሮግራም ማዘጋጀት፤<br>• የዳኝነት ትምህርትና ስልጠና ማዕከል ማቋቋም፤ | የዳኝነት ስልጠና ስርዓት ተዘርግቶ ተተግ ሯል፤ | ተዘጋጅቶ የተተገበረ የስልጠና ፖሊሲ | - | 1 | | 1 | | | | የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ጽ/ቤት፣ ፕሬዝደንቶች፣ ጥናትና ምርምር ዳይሬክቶሬት፣ ትምህርትና ስልጠና ክፍሎች |
| | | | በአዳዲስ አስተምህሮ ሕጎች ላይ የተዘጋጁ የስልጠና መድረኮች ብዛት በቁጥር | - | 25 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | |

| ስትራቴጂዎች | ዋና ዋና ተግባራት | ውጤት (out-put) | አመልካች | መነሻ/ baseline | ግብ Target | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | ፈጻሚ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | • በአዳዲስ አስተምህሮ ሕጎች ላይ ለዳኞች ስልጠና መስጠት፤<br>• በፍርድ ቤት ውሳኔዎች ላይ በሁሉም ደረጃ ባሉ ፍርድ ቤቶች ኮንፈረንስ ማዘጋጀት፤<br>• ዓመታዊ የባለሙያዎች መናገሪያ መድረክ ማዘጋጀት<br>• የጉብኝትና የልምድ ልውውጥ ፕሮግራም ማካሄድ | | የተዘጋጁ የኮንፍረንስና የንግግር መድረኮች ብዛት በቁጥር | | 30 | 6 | 6 | 6 | 6 | 6 | |
| | | | ተግባራዊ የተደረጉ የልምድ ልውውጥና ጉብኝት መርሐ-ግብሮች ብዛት በቁጥር | | 10 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | |
| 1.1.6. የዳኝነት ገለልተኝነትን ማረጋገጥ፣ | • የዳኞችን የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም የሚመራ ማንዋል ማውጣት እና ለዳኞች ማስተዋወቅ፤ | የዳኝነት ገለልተኝነት ተረጋግጧል፤ | የተዘጋጁ የጥናት ሰነዶች ብዛት በቁጥር | - | 1 | | 1 | | | | ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ፣ ፕሬዝደንቶች፣ የየፍ/ቤቶቹ ኢንስፔክሽን ክፍሎች፣ |
| | | | የተከናወኑ የምክክር መድረኮች ብዛት በቁጥር | - | 10 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | |

| ስትራቴጂዎች | ዋና ዋና ተግባራት | ውጤት (out-put) | አመልካች | መነሻ/ baseline | ግብ Target | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | ፈጻሚ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | • የዳኝነት ስራ በገለልተኝነት እንዳይካሄድ እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ ጉዳዮችን በጥናት መለየት፤<br>• በጥናት ግኝቶች መሰረት ለገለልተኝነት እንቅፋት የሆኑ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል ስርዓት ዘርግቶ መተግበር፤<br>• በዳኝነት ገለልተኝነት ላይ የዳኞች ግንዛቤ ማጎልበቻ የውይይት መድረኮች ማዘጋጀት | | የተዘረጉ ስርዓቶች ብዛት በቁጥር | | 3 | | | 1 | 2 | | ሬጅስትራር፣ ችሎቶች፣ ኮሚዩኒኬሽን ዳይሬክቶሬት |
| 1.2. ስትራቴጂያዊ ግብ ፡- የዳኝነት ግልጽነት እና ተጠያቂነት ሥርዓትን ማጠናከር | | | | | | | | | | | |
| 1.2.1. የፍርድ ቤቶችን አሰራርና አገልግሎቶች | • የዳኞችን የስነምግባር ደንብ አሳትሞ ለዳኞች ማሰራጨት፣ | የፍርድ ቤቶች አሰራርና አገልግሎቶች | የተዘረጉ የግልጽ አሰራር ስርዓቶች ብዛት በቁጥር | 3 | 4 | 3 | | 4 | | | የምርምር እና ህግ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት፣ ኮምዩኒኬሽን |

| ስትራቴጂዎች | ዋና ዋና ተግባራት | ውጤት (out-put) | አመልካች | መነሻ/ baseline | ዒላማ Target | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | ፈጻሚ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ለሕዝብ ግልጽ ማድረግ፣ | ማስረጽ፤<br>• የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ከዳኞች እና ከሰራተኞች ጋር ግልጽ ውይይት የሚያደርግበትን ስርዓት ማመቻቸትና መተግበር፤<br>• በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የሚተገበር ግልጽ የጉዳዮች አደላደል ስታንዳርድ ማውጣት፤<br>• የተመረጡ የፍርድ ቤት ውሳኔዎችን ለሕዝብ ተደራሽ የሚደረግበትን ስርዓት መቅረጽና መተግበር፤ | ለሕዝብ ግልጽ ሆነዋል፤ | ለሕዝብ ግልጽ የተደረጉ የሰበር ውሳኔዎች ብዛት በመቶኛ | 3.2% | 100% | 20% | 40% | 60% | 80% | 100% | ዳይሬክቶሬት፣ ኢ.ኮቴ ዳይሬክቶሬት |

| ስትራቴጂዎች | ዋና ዋና ተግባራት | ውጤት (out-put) | አመልካች | መነሻ/ baseline | ግብ Target | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | ፈጻሚ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1.2.2. የግልጽ ችሎቶች አገልግሎቶችን ማጠናከር፣ | • የግልጽ ችሎት ስታንዳርድ ማውጣትና መተግበር<br>• በግልጽ ችሎት የዳኝነት አገልግሎት መስጠት፤ | የግልጽ ችሎቶት አገልግሎቶች ተጠናክረዋል፤ | በግልጽ ችሎት ለማስቻል ስታንዳርዳ ቸውን ጠብቀው የተዘጋጁ የችሎት አዳራሾች እና ችሎቶች ጥመርታ | 1:2 | 1:1 | 1:2 | 1:2 | 1:2 | 1:1 | 1:1 | ፕሬዝደንቶች፣ ችሎቶች፣ ኮርት ማነጀሮች፣ ሬጅስትራር፣ ችሎት አገልግሎት፤ |
| | | | በግልጽ ችሎት የተሰጡ ውሳኔዎች ብዛት በመቶኛ | - | 100% | 50% | 55% | 65% | 75% | 100% | |
| 1.2.3. የፍርድ ቤቶች የሪፖርት አቀራረብ ስርዓት ማሻሻል፣ | • የፋይናንስ እና ስራ አፈጻጸምሪፖርት ቅርጽ እና ይዘት የሚወስን ስታንዳርድ ማዘጋጀት<br>• የፌደራል ፍርድ ቤቶች በስታትስቲክስ | የፍርድ ቤቶች የሪፖርት አቀራረብ ስርዓት ተሻሽሏል፤ | የተዘጋጀ የሪፖርት ስታንዳርድ በቁጥር | - | 1 | 1 | | | | | ስትራቴጂክ ዳይሬክቶሬት |
| | | | የተዘጋጁ ሪፖርቶች ብዛት በቁጥር | 4 | 20 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | |
| | | | ሪፖርቶች የቀረቡባቸው መድረኮች ብዛት በቁጥር | 4 | 20 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | |

| ስትራቴጂዎች | ዋና ዋና ተግባራት | ውጤት (out-put) | አመልካች | መነሻ/ baseline | ግብ Target | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | ፈጻሚ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የተደገፉ የአፈጻጸም ሪፖርቶች ማዘጋጀት፣ ማሳተም እና ተደራሽ ማድረግ፤<br>• የፌደራል ፍርድ ቤቶች አመታዊ ሪፖርት (annual state of the judiciary report) መድረክ አዘጋጅቶ ለህዝቡ ይፋ ማድረግ፤ | | | | | | | | | | |
| 1.2.4. ግልጽ አሰራርን እና የስነምግባር መርሆዎችን መሠረት ያደረገ የዳኝነት | • ቀልጣፋ እና ውጤታማ የቅሬታ፣ ጥቆማ እና አቤቱታ አቀራረብ ስርዓት ማጠናከር፤<br>• በሁሉም ምድብ ችሎቶች በኢኮቴ | ግልጽ አሰራርን እና የስነምግባር መርሆዎችን የተከተለ የዳኝነት ተጠያቂነት | የተጠናከሩ ስርዓቶች ብዛት በቁጥር | 1 | 2 | 2 | | | | | የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ፣ ፕሬዝደንቶች፣ ኢንስፔክሽን፣ |

| ስትራቴጂዎች | ዋና ዋና ተግባራት | ውጤት (out-put) | አመልካች | መነሻ/ baseline | ዒላማ Target | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | ፈጻሚ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የታገዘ የተገልጋይ አስተያየት መቀበያ ስርዓት መዘርጋት፤<br>• በሁሉም ምድብ ችሎቶች የተገልጋይ እርካታ ሰርቬይ ማካሄድ፤<br>• የዳኞች የአፈጻጸም ምዘና ስርዓት ዘርግቶ መተግበር፤<br>• የድህረ ፍርድና ውሳኔ ምርመራን በቋሚነት መስራት፤ | | የተጠናከረ ኢንስፔክሽንና ፍርድ ምርመራ ክፍል፤ | 1 | 3 | | 3 | | | | |
| | | | የተሰሩ የፍርድና ውሳኔዎች ምርመራ ዕድገት በመቶኛ | 0.01% | 5% | 1% | 1% | 1% | 1% | 1% | |
| | | | ለኢንስፔክሽን ቀርበው እልባት ያገኙ ቅሬታና አቤቱታዎች እድገት በመቶኛ | 89.5% | 95% | 90% | 92% | 94% | 94% | 95% | |
| | | | ዳኞችን በተመለከተ ምላሽ ያገኙ የስነ- | 0.4% | 5% | 1% | 1.5% | 2% | 3% | 5% | |
| | | | ምግባር ጥሰት እና የዲሲፕሊን አቤቱታዎች ብዛት በመቶኛ | | | | | | | | |

2. ቁልፍ የውጤት መስክ ፦ የዳኝነት ቅልጥፍና እና ጥራት

2.1. ስትራቴጂያዊ ግብ ፡- የዳኝነት አገልግሎት ቅልጥፍና ማሳደግ

| ስትራቴጂዎች | ዋና ዋና ተግባራት | ውጤት (out-put) | አመልካች | መነሻ/ baseline | ግብ Target | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | ፈጻሚ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2.1.1. የሬጅስትራር አገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነትን ማሻሻል፤ | • የሬጂስትራርን አሰራር እና አደረጃጀት ማሻሻል፤<br>• የሬጂስትራር የአንድ መስኮት አገልግሎት ተግባራዊ ማድረግ፤<br>• የሬጂስትራር የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ አዘጋጅቶ መተግበር፤ | የሬጅስትራር አገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነት ተሻሽሏል፤ | የስነ-ስርዓት ህጎችና የአሰራር መመሪያዎችን ጠብቀው የተከፈቱ መዛግብት ዕድገት በመቶኛ | - | 95% | 80% | 85% | 90% | 90% | 95% | ሬጅስትራር ጽ/ቤት፣ጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት፣ ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት |
| | | | የውሳኔ፣ የትእዛዝ፣ የዕግድ፣ እና የብይን ግልባጭ በዕለቱ የመስጠት አገልግሎት ዕድገት በመቶኛ | - | 100% | 65% | 70% | 80% | 90% | 100% | |
| | | | በቀጠሮ ቀን የመልስ መልስ የማቀባበል ዕድገት በመቶኛ | - | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | | | በተጠየቀበት ዕለት የተሰጠ የመረጃ አገልግሎት ዕድገት በመቶኛ | | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |

| ስትራቴጂዎች | ዋና ዋና ተግባራት | ውጤት (out-put) | አመልካች | መነሻ/ baseline | ግብ Target | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | ፈጻሚ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2.1.2. የዳኞችን ትጋትና ውጤታማነት የሚጨምሩ ስርዓቶችን ማጠናከር፤ | • የዳኝነት አገልግሎት ለማሻሻል የተዘጋጀውን የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር መመሪያ ትግበራ አጠናክሮ መቀጠል፤<br>• የዳኞችና መዝገብት ጥምርታን መለየት የሚያስችል ጥናት ማካሄድ እና ተግባራዊ ማድረግ፤<br>• የማበረታቻ ማዕቀፍ ማዘጋጀት፣ መተግበር<br>• የረዳት ዳኞች ስራ ዝርዝር በግልጽ መለየት | የዳኞች ትጋትና ውጤታማነት ጨምሯል፤ | በመመሪያው በተቀመጠላቸው ጊዜ ዕልባት ያገኙ መዛግብት ዕድገት በመቶኛ | 87% | 95% | 88% | 90% | 92% | 94% | 95% | ችሎቶች<br>ፕሬዝደንቶች |
| | | | ያደገ የማጥራት አቅም በመቶኛ | 101.7% | ≥100% | ≥100% | ≥100% | ≥100% | ≥100% | ≥100% | |
| | | | ውሳኔ ያገኙ መዛግብት ብዛት በቁጥር | 171,276 | 246,27 | 186,91 | 201,27 | 216,27 | 231,27 | 246,27 | |
| | | | በዕቅድ መሰረት የተፈጸሙ መዛግብት ዕድገት በመቶኛ | 102.7% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | | | የተተገበረ የዳኞችና መዛግብት ጥምርታ ጥናት በቁጥር | - | 1 | | 1 | | | | |
| | | | ያደገ አማካይ የዳኞች የመዛግብት ስራ አፈጻጸም በመቶኛ | - | 95% | 80% | 90% | 92% | 94% | 95% | |

| ስትራቴጂዎች | ዋና ዋና ተግባራት | ውጤት (out-put) | አመልካች | መነሻ/ baseline | ግለግ Target | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | ፈጻሚ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2.1.3. የተፋጠነ እና አጭር ስነ-ስርዓት አተገባርን ማጠናከር | • ቀላል ሥነ ሥርዐት የሚፈጸምባቸውን ጉዳዮች በጥናት መለየት፤<br>• በጥናቱ ግኝት መሰረት ማሻሻያ የሚያስፈልጋቸው የሥነ ሥርዓት ህግ ድንጋጌዎችን ለይቶ ለሚመለከታቸው አካላት ማሳወቅ፤<br>• ከክስ መስማት በፊት ጉዳዮች የሚቋጩበትን ስርአት መዘርጋትና መተግበር | የተፋጠነ እና አጭር ስነ-ስርዓት አተገባር ተጠናክሯል | በተፋጠነ እና አጭር ስነስርዓት እልባት ያገኙ መዛግብት እድገት በመቶኛ | - | 50 | 30 | 35 | 40 | 45 | 50 | ፕረዝደንቶች፤ ዳኞች፣ ሬጂስትራሮች፣ |
| | | | ተሸሽሎ የተተገበረ የተፋጠነ እና ቀላል ስነስርዓት | | 1 | | | 1 | | | |
| 2.1.4. የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር ስርዓት በተሟላ መልኩ መዘርጋትና መተግበር፤ | • የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር ዳይሬክቶሬትን ማዋቀር እና ማጠናከር፤<br>• በመመሪያ መሰረት የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር ላይ | የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር ስርዓት በተሟላ መልኩ ተተግብሯል፤ | የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደርን ጨምሮ ተዘጋጅተው/ ተከልሰው የተተገበሩ መመሪያዎች ብዛት በቁጥር | 1 | 3 | 1 | | 2 | 4 | 4 | ፕሬዝደንቶች ፣ ሬጅስትራር ጽ/ ቤት፣ የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት |

| ስትራቴጂዎች | ዋና ዋና ተግባራት | ውጤት (out-put) | አመልካች | መነሻ/ baseline | ግብ Target | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | ፈጻሚ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | • የወንጀል ጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር መመሪያ አዘጋጅቶ መተግበር፤<br>• የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር መመሪያን በየወቅቱ መከለስ፤<br>• በጉዳይ አመራር ላይ ስልጠና መስጠት | | በጉዳዮች ፍሰት አተገባበር ላይ የተደረጉ ክትትልና ድጋፎች ብዛት በቁጥር | | 20 | 4 | 4 | 4 | | | |
| | | | የተሞሉ ክፍተቶች በመቶኛ | 50 | 100 | 50 | 60 | 70 | 80 | 100 | |
| 2.1.5. ውዝፍ መዛግብትን መቀነስ የሚያስችል ስልት ዘርግቶ መተግበር፤ | • የውዝፍ መዝገብ የማጥራት ስርዓት ዘርግቶ መተግበር<br>• በየሩብ አመቱ የውዝፍ መዝገቦች ቆጠራ ማካሄድ<br>• ከሥነ ስርአት ሕጉ ውጪ እየተተገበሩ ያሉ ልማዳዊ አሰራሮችን መለየት የሚያችል ጥናት ማካሄድና በግኝቱ መሰረት ማስተካከያዎችን ማድረግ፤ | ውዝፍ መዛግብት ቀንሰዋል፤ | ውዝፍ መዛግብትን ለመቀነስ እና የተጓደሉ ችሎቶችን ለማሟላት የተተገበረ ስርዓት | | 1 | | 1 | | | | የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ፣ ፕሬዝደንቶች፣ ችሎቶች፣ ጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር ዳ/ት |
| | | | የቀነሰ የክምችት ምጣኔ | 0.21 | 0 | 0.20 | 0.15 | 0.12 | 0.10 | 0 | |

| ስትራቴጂዎች | ዋና ዋና ተግባራት | ውጤት (out-put) | አመልካች | መነሻ/ baseline | ዒላማ Target | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | ፈጻሚ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2.1.6. የፍርድ አፈጻጸም ውጤታማነት የሚያጎለብቱ የአሰራር፤ አደረጃጀት እና የሰው ኃይል አቅምን ማጠናከር፤ | • የአደረጃጀት እና የአሰራር ማሻሻያ ጥናት ማካሄድና ተግባራዊ ማድረግ<br>• የፍርድ አፈጻጸም የሚያጓትቱ የስነ ስርዓት ህግ ድንጋጌዎችን መለየት የሚያስችል ጥናት ማካሄድ እና ማሻሻያ ሃሳቦችን ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ፤<br>• ፍርድ አፈጻጸም ስርዓት መመሪያ አዘጋጅቶ መተግበር፤<br>• ለፍርድ አፈጻጸም መዘግየት አስተዋጽኦ ላላቸው ባለድርሻ አካላት የውይይት መድረክ ማዘጋጀትና የጋራ ስምምነት መፍጠር፤ | የፍርድ አፈጻጸም ውጤታማነት ጨምሯል፤ | እንደ ፍርዱ የተፈጸሙ መዝገብት ዕድገት በመቶኛ | 86.3% | 97.2% | 86.3% | 88.8% | 91.6% | 94.4% | 97.2% | ፕሬዝደንቶች፣<br>ፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት፣<br>ኮርት ማነጀሮች፤ |
| | | | የፍርድ አፈጻጸም ውጤታማነት ለማሳደግ የተደረጉ ማሻሻያዎች ብዛት በቁጥር | | 3 | 1 | 2 | | | | |
| | | | ከቁልፍ ባለድርሻ አካላት ለመስራት የተደረጉ ስምምነቶች ብዛት በቁጥር | | 10 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | |

| ስትራቴጂዎች | ዋና ዋና ተግባራት | ውጤት (out-put) | አመልካች | መነሻ/ baseline | ዒላማ Target | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | ፈጻሚ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2.2. ስትራቴጂያዊ ግብ ፡- የዳኝነት ጥራት ማጎልበት | | | | | | | | | | | |
| 2.2.1. አሳታፊና ግልጽ አሰራርን የተከተለ የሬጅስትራር፣ የዳኝነት እና የፍርድ አፈጻጸም አገልግሎት ጥራት ደረጃ አዘጋጅቶ መተግበር፤ | • የዳኝነት አገልግሎት ጥራት ስታንደርድ ማዘጋጀት<br>• የሬጂስትራር አገልግሎት ጥራት ስታንደርድ ማዘጋጀት፤<br>• የፍርድ አፈጻጸም አገልግሎት ጥራት ስታንደርድ ማዘጋጀት፤<br>• በጥራት ስታንዳርድ አፈጻጸም ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መስጠት፤ | አሳታፊና ግልጽ አሰራርን የተከተለ የአገልግሎት ጥራት ደረጃ ተዘጋጅቷል፤ | የተተገበረ የአገልግሎት ጥራት ስታንዳርድ ብዛት በቁጥር | | 3 | | 3 | | | | ፕሬዝደንቶች ሬጅስትራር፣ የምርምር እና ህግ ጉዳዮች ዳ/ት፣ |
| | | | የተሰጠ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ብዛት በቁጥር | - | 3 | | 3 | | | | |
| 2.2.2. ውጤታማ የችሎት አደረጃጀት ሥርዓት መዘርጋትና መተግበር ፤ | • የችሎቶችን ውጤታማነት የሚያሳድግ አደረጃጀት ጥናት ማካሄድ፤ | በጥናት መሰረት የተደራጁ ውጤታማ ችሎቶች ተጠናክረዋል፤ | የተተገበረ የችሎት አደረጃጀት ጥናት | | 1 | | 1 | | | | የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ጽ/ቤት ፣ፕሬዝደንቶች ፣ ፣ጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር ዳ/ት |
| | | | የተሰጡ ስልጠናዎች ብዛት በቁጥር | | 10 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | |

| ስትራቴጂዎች | ዋና ዋና ተግባራት | ውጤት (out-put) | አመልካች | መነሻ/ baseline | ግብ Target | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | ፈጻሚ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | • በጥናት ግኝቶች መሰረት የችሎቶች አደረጃጀት መመሪያ አዘጋጅቶ መተግበር፤<br>• ዳኞች የተመደቡበትን ችሎት ባህሪ መሰረት ያደረገ ስልጠና መስጠት፤ | | በጥናቱ መሰረት የተደራጁ ችሎቶች ዕድገት በመቶኛ | | 100 | 50 | 65 | 80 | 90 | 100 | |
| 2.2.3. በሰበር ችሎቶች አደረጃጀት፣ አሰራር፣ በዳኞች አሰያየም... ላይ ማሻሻያዎ ችን ማድረግ፤ | • የሰበር ችሎት አደረጃጀት፣ አሰራርና የዳኞች አሰያየም ጥናት ማካሄድ፤<br>• በጥናት ግኙት መሰረት የአደረጃጀትና የአሰራር ማሻሻያዎችን ማድረግ፤<br>• የሰበር ችሎት አሰራር ስርዓት ማኑዋል ማዘጋጀት፣ | በሰበር ችሎቶች አደረጃጀት፣ አሰራር እና የዳኞች አሰያየም ላይ ማሻሻያዎች ተደርገዋል፤ | ተግባራዊ የተደረገ የሰበር ችሎት ማሻሻያ መመሪያ | | 1 | 1 | | | | | ፕሬዝደንቶች፣ የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ፣ የምርምር እና ህግ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት፣ |
| | | | የተተገበረ የሕግ አተረጓጎም መመሪያ | | 1 | 1 | | | | | |

| ስትራቴጂዎች | ዋና ዋና ተግባራት | ውጤት (out-put) | አመልካች | መነሻ/ baseline | ግብ Target | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | ፈጻሚ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | • ወጥ የሕግ አተረጓጎም ስርዓት መመሪያ ማዘጋጀት፤ | | | | | | | | | | |
| 2.2.4.የውሳኔዎችን ምክንያታዊነት ማሳደግ፤ | • የውሳኔ አጻጻፍ ማንዋል ማዘጋጀት፤<br>• የፍርዶችን ፋይዳ ማጥናትና የማሻሻያ እርምጃ መውሰድ፤<br>• በናሙና ፍርዶች ይዘት እና ቅርጽ ላይ የትምህርታዊ ጉባዔ ሰነድ ማዘጋጀት፤<br>• ትምህርታዊ ጉባዔ ማካሄድ፤ | የውሳኔዎች ምክንያታዊነት አድጓል፤ | ተግባራዊ የተደረገ የውሳኔ አጻጻፍ ማንዋል | | 1 | | 1 | | | | ፕሬዝደንቶች፣ ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ፣ የምርምር እና ህግ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት፣ |
| | | | የፍርዶችን ፋይዳ መለየት ያስቻለ ጥናት፤ | | 5 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | |
| | | | በፍርዶች ይዘት እና ቅርጽ ላይ የተዘጋጁ ትምህርታዊ ጉባዔዎች ብዛት በቁጥር፤ | | 10 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | |
| 2.2.5 የባለጉዳዮች አያያዝ ስርዓት ዘርግቶ መተግበር፤ | • የተገልጋይ አያያዝ ማንዋል ማዘጋጀት<br>• በተገልጋዮች አያያዝ ላይ ዳኞች እና የሬጂስትራር ሰራተኞች የሚሳተፉበት የጋራ መድረክ ማመቻቸት፤ | የባለጉዳዮች አያያዝ ስርዓት ተተግብሯል፤ | የተዘጋጀ የተገልጋይ አያያዝ ማኑዋል | | 1 | 1 | | | | | ፕሬዝደንቶች፣ ኮርት ማኔጀሮች፣ ስትራቴጂክ ዳ/ት፣ |
| | | | በተገልጋይ አያያዝ ላይ ማሻሻያ ለማድረግ የተካሄዱ የምክክር | | 10 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | |

| ስትራቴጂዎች | ዋና ዋና ተግባራት | ውጤት (out-put) | አመልካች | መነሻ/ baseline | ዒላማ Target | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | ፈጻሚ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | • የተገልጋይ አስተያየት ማሰባሰቢያ ስርዓትን ማጠናከር፤<br>• በተሰጡ አስተያየቶች መሰረት የማሻሻያ እርምጃዎች መውሰድ፤ | | መድረኮች ብዛት በቁጥር | | | | | | | | |
| | | | የተተገበረ የተገልጋይ አስተያየት ማስተናገጃ ስርዓት | | 1 | 1 | | | | | ሬጅስትራር ጽ/ቤት፣ ችሎት አገልግሎት |
| | | | የጨመረ የተገልጋይ ዕርካታ ዕድገት በመቶኛ | 51 | 80 | 60 | 65 | 70 | 75 | 80 | ሁሉም ችሎቶች እና ስራ ክፍሎች |
| 3. ቁልፍ የውጤት መስክ ፡ የዳኝነት ተደራሽነት | | | | | | | | | | | |
| 3.1. ስትራቴጂያዊ ግብ፡- የፍርድ ቤቶች የአገልግሎቶች ተደራሽነት ማሳደግ | | | | | | | | | | | |
| 3.1.1. ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም የዳኝነት አገልግሎት ተደራሽነትን ማሳደግ፤ | • በቪዲዮ ኮንፈረንስ የሚሰጡ የዳኝነት አገልግሎቶችን ማጠናከር፤<br>• የኢ-ፋይሊንግ ማዕከላትን በሰው ሃይል፣ አደረጃጀትና አሰራር ስርዓት ማጠናከር፤ | ዘመናዊ ቴክኖሎጂን በመጠቀም ተደራሽነትን ማሳደግ ተችሏል፤ | በቪዲዮ ኮንፍረንስ ተደራሽ የሆኑ መዛግብት ዕድገት በቁጥር፤ | 5,900 | 7,000 | 5,000 | 5500 | 6000 | 6500 | 7000 | ፕሬዝደንቶች፣ ኮርት ማነጀሮች፣ ኢ.ኮቴ ዳ/ት |

| ስትራቴጂዎች | ዋና ዋና ተግባራት | ውጤት (out-put) | አመልካች | መነሻ/ baseline | ግብ Target | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | ፈጻሚ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | • የችሎት ፤ ትዕዛዝ፤ ብይን፣ እግድ፣ ውሳኔ... በኢ-ፋይሊንግ ስርዓት ለተገልጋዮች ማድረስ፤ | | በኢ-ፋይሊንግ የተከፈቱ መዛግብት ዕድገት በቁጥር፤ | 1,737 | 9,500 | 2,500 | 3500 | 5000 | 7000 | 9500 | |
| | | | በኢ-ፋይሊንግ ተደራሽ የተደረጉ የችሎት ትዕዛዝ፤ ብይን፣ እግድ፣ ውሳኔ... ብዛት በቁጥር | 1,737 | 9,500 | 2,500 | 3500 | 5000 | 7000 | 9500 | |
| 3.1.2. የዳኝነት አገልግሎት መረጃዎችን ተደራሽነት ማሳደግ | • የፍርድ ቤት መረጃዎችን በአጭር የጽሑፍ መልዕክት ተደራሽ ማድረግ፤ • የመረጃ አሰጣጥ ስርዓትን ማዘመን የሚያስችል ስታንዳርድ አዘጋጅቶ መተግበር፤ • መረጃ ለሚሰጡ ሰራተኞች ስልጠና መስጠት፤ | የመረጃ ተደራሽነት ማሳደግ ተችሏል | በአጭር የጽሑፍ መልዕክት የተሰጠ መረጃ ብዛት በቁጥር | 3600 | 6000 | 4000 | 4500 | 5000 | 5500 | 6000 | |
| | | | የተተገበረ ዘመናዊ የመረጃ አሰጣጥ ስታንዳርድ፤ | - | 1 | 1 | | | | | |

| ስትራቴጂዎች | ዋና ዋና ተግባራት | ውጤት (out-put) | አመልካቾች | መነሻ/ baseline | ግለማ Target | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | ፈጻሚ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | • መረጃ በተለያዩ ቋንቋዎች መተርጎም<br>• የመዛግብት መረጃዎች በድረ-ገጽ ተደራሽ የሚሆኑበትን አሰራር ማጠናከር<br>• ናሙና ክሶችንና ልዩ ልዩ የአቤቱታ ቅጾችን በማዘጋጀትና በድረ ገጾች ጭምር ተደራሽ በማድረግ | | | | | | | | | | |
| 3.1.3. የተከላካይ ጠበቆች ጽ/ቤት አደረጃጀትና አሰራር ስርዓት ማሻሻልና አገልግሎት አሰጣጥን ማጠናከር፤ | • በመዋቅር በተቀመጠው መሰረት የተከላካይ ጠበቆች ጽ/ቤት አደረጃጀት ዘላቂ የሆነ መፍትሄ በሚሰጥ መልኩ ማሻሻል፣ | የተዘጋጀውን የተቋም መዋቅር ተከትሎ የተከላካይ ጠበቆች ጽ/ቤት አደረጃጀት፣ | የተከላካይ ጥብቅና አገልግሎት የተሰጠባቸው መዛግብት ዕድገት በቁጥር | 12,023 | 17,000 | 13,000 | 14,000 | 15,000 | 16,000 | 17,000 | ፕሬዝደንቶች፣ ተከላካይ ጠበቆች ጽ/ቤት፣ የምርምር እና ህግ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት፣ |

| ስትራቴጂዎች | ዋና ዋና ተግባራት | ውጤት (out-put) | አመልካች | መነሻ/ baseline | ግብ Target | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | ፈጻሚ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | የተከላካይ ጥብቅና አገልግሎት ተጠቃሚዎች ዕድገት በመቶኛ | 29,923 | 44,200 | 33,800 | 36,400 | 39,000 | 41,600 | 44,200 | |
| | | | የተቋሙን መዋቅር ተከትሎ የተሸሻለ የክፍሉ አደረጃጀት፣ | | 1 | 1 | | | | | |
| | | | ተዘጋጅቶ የተተገበረ የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ ሰነድ በቁጥር | | 1 | | 1 | | | | |
| | | | ለተከላካይ ጠበቆች የተሰጠ ስልጠና ብዛት በቁጥር | 4 | 25 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | |
| 3.1.4. የፍርድ ቤት መር አስማሚነት ስርዓትን ማጠናከር፤ | • የፍርድ ቤት መር አስማሚነት መመሪያን በማውጣት በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፍርድ ቤት | የፍርድ ቤት መር አስማሚነት ስርዓት ተጠናክሯል፤ | የተደራጁ የአስማሚነት ችሎቶች ዕድገት በቁጥር | 6 | 16 | 10 | 12 | 14 | 15 | 16 | ፕሬዝዳንቶች፣ ኮርት ማነጀሮች፤ |
| | | | የአስማሚነት ውጤታማነት ዕድገት በመቶኛ | 34.37 | 90 | 55 | 65 | 75 | 85 | 90 | ፕሬዝዳንቶች፣ ኮርት ማነጀሮች፤ |

| ስትራቴጂዎች | ዋና ዋና ተግባራት | ውጤት (out-put) | አመልካች | መነሻ/ baseline | ግብ Target | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | ፈጻሚ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | መር አስማሚነት መተግበር<br>• ብቁ አስማሚዎችን መመልመል፣ መቅጠር፣ ስልጠና መስጠት | | በፍርድ ቤት መር አስማሚነት እልባት ያገኙ ጉዳዮች ዕድገት በመቶኛ | 643 | 1286 | 900 | 900 | 1157 | 1157 | 1286 | |
| 3.1.5. የተሟላ የትርጉም አገልግሎት ስርዓት መዘርጋትና መተግበር፤ | • የትርጉም አገልግሎት የሚሰጡ ባለሙያዎች (የምልክት ቋንቋን ጨምሮ) የብቃት ደረጃ ማውጣት፣ ሰርቲፊኬት መስጠት፣ በሮስተር አካቶ መጠቀም<br>• የትርጉም አገልግሎት የሚጠናከርበት ስርዓት መዘርጋትና መተግበር<br>• ማየት የተሳናቸው ባለጉዳዮች የውሳኔ ግልባጮችን በብሬል ማግኘት ስለሚችሉበት ሁኔታ ተግባራዊ ማድረግ፤ | የተሟላ የትርጉም አገልግሎት ስርዓት ተጠናክሯል፤ | በተጠየቁ ቋንቋዎች ትርጉም አገልግሎት ያገኙ ተገልጋዮች ዕድገት በመቶኛ | - | 100% | 80% | 85% | 90% | 95% | 100% | የችሎት አገልግሎት፣ ሬጅስትራር ጽ/ቤት፣ ተከላካይ ጠበቆች ጽ/ቤት |
| 3.2. ስትራቴጂያዊ ግብ፡- የፍርድ ቤቶችን አካላዊ ተደራሽነት ማሳደግ | | | | | | | | | | | |

| ስትራቴጂዎች | ዋና ዋና ተግባራት | ውጤት (out-put) | አመልካች | መነሻ/ baseline | ግብ Target | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | ፈጻሚ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 3.2.1. በጥናት የተለዩ ቦታዎች የፌደራል ፍርድ ቤቶችን አደረጃጀት ስርዓት ዘርግቶ መተግበር፤ | • ፍርድ ቤቶች በየትኛው አካባቢ መቋቋም እንዳለባቸው የሚያሳይ የአደረጃጀት ጥናት ማድረግ (judi-cial map-ping)<br>• የፍርድ ቤቶች፣ ዳኞች፣ ሕብረተሰቡ ጥመርታን የሚያሳይ መለኪያ ማውጣት | በጥናት በተለዩ ቦታዎች የፌደራል ፍርድ ቤቶች ተደራጅተዋል | የተተገበረ የፌ/ፍ/ቤቶች አደረጃጀት ስርዓት | - | 1 | 1 | | | | | ፕሬዝደንቶች፣ ኮርት ማኔጀሮች ፣ የሰው ኃብት ልማት ዳ/ት፣ የምርምር እና ህግ ጉዳዮች ዳ/ት |
| 3.2.2. በጥናት በተለዩ የክልል ከተሞች የፌደራል ፍርድ ቤቶችን ማደራጀት፤ | • ውክልናቸው በተነሳባቸው ክልሎች የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማደራጀት<br>• የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም በክልሎች ስለሚደራጅበት ሁኔታ ጥናት ማድረግ | የፌደራል ዳኝነት አገልግሎት የሚሰጡ ፍርድ ቤቶች ተደራጅተዋል፤ | የፌደራል ዳኝነት አገልግሎት ለመስጠት የተደራጁ ፍርድ ቤቶችና ማዕከላት ዕድገት በመቶኛ | 1 | 5 | 2 | 1 | 2 | | | የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ፣ ፕሬዝደንቶች፣ ኮርት ማኔጀሮች ፣ የምርምር እና ህግ ጉዳዮች ዳ/ት፣ ሬጅስትራር ፣ የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር ዳ/ት፤ |

| ስትራቴጂዎች | ዋና ዋና ተግባራት | ውጤት (out-put) | አመልካች | መነሻ/ baseline | ግብ Target | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | ፈጻሚ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | • ውክልና ባልተነሳባቸው ክልሎች የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የመጀመሪያ ፍርድ ቤቶች ውክልና ስለሚነሳበት አግባብ የምክክር መድረኮች ማዘጋጀት፣ ህግ እንዲወጣ (initiate) ግፊት ማድረግ<br>• በወጣው ህግ መሰረት የከፍተኛና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች በሁሉም ክልሎች ማደራጀት | | | | | | | | | | |
| 3.2.3. ተዘዋዋሪ ችሎቶች በሰው ኃይል፣ በሎጅስቲክና በቅንጅታዊ አሰራር ማሻሻል፤ | • ተዘዋዋሪ ችሎቶችን በአስፈላጊው የሪሶርስ አቅርቦት ማጠናከር | የተዘዋዋሪ ችሎቶች አሰራርና አደረጃጀት ተሻሽሏል | የተሻሻለ ተዘዋዋሪ ችሎት አሰራርና አደረጃጀት ዕድገት በመቶኛ | | 100 | 50 | 60 | 80 | 90 | 100 | ፕሬዝዳንቶች፣ የተዘዋዋሪ ችሎት ዳኞች፣ ኮርት ማነጀሮች፣ ሬጅስትራሮች |

| ስትራቴጂዎች | ዋና ዋና ተግባራት | ውጤት (out-put) | አመልካች | መነሻ/ baseline | ግብ Target | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | ፈጻሚ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር መመሪያ መሰረት በተዘዋዋሪ ችሎቶች ዕልባት ያገኙ ጉዳዮች ዕድገት በቁጥር | 285 | 380 | 300 | 320 | 340 | 360 | 380 | |
| 3.2.4. የፍርድ ቤቶችን የስራ ቦታዎችና መገልገያዎች ለተገልጋዮች ተደራሽና ምቹ የሚያደርጉ የመሠረተ ልማት አውታሮችን ማጠናከር፤ | • የመሰረተ ልማት ማስተር ፕላን ጥናት ማድረግና ማዘጋጀት<br>• የተጀመሩና አዲስ የፍርድ ቤት ህንፃዎችን መገንባት<br>• በክልሎች የቪዲዮ ኮንፈረንስ ችሎትን ማጠናከር<br>• በማረሚያ ቤቶች የቪዲዮ ኮንፈረንስ ችሎትን ማጠናከር<br>• የሳይበር ፍትህ፣ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ በፍርድ ቤት ውስጥ | የፍርድ ቤቶችን የስራ ቦታዎችና መገልገያዎች ለተገልጋዮች ተደራሽና ምቹ ሆነዋል፤ | የፍርድ ቤቶችን የስራ ቦታዎችና መገልገያዎች ለተገልጋዮች ተደራሽና ምቹ ለማድረግ የተዘጋጀ ማስተር ፕላን ብዛት በቁጥር | | 1 | 1 | | | | | ፕሬዝደንቶች፣ ኮርት ማኔጀሮች ፣ ሕንጻ አስተዳደርና ጥገና አገልግሎት ዳ/ት |
| | | | የተገነቡ የፍርድ ቤት ሕንጻዎች ብዛት በቁጥር | | 4 | | | 2 | | 4 | ፕሬዝደንቶች፣ ኮርት ማኔጀሮች ፣ ሕንጻ አስተዳደርና ጥገና አገልግሎት ዳ/ት |

| ስትራቴጂዎች | ዋና ዋና ተግባራት | ውጤት (out-put) | አመልካች | መነሻ/ baseline | ግብ Target | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | ፈጻሚ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ሊተገበሩ የሚችሉበትን አግባብ የያዘ የፍርድ ቤቶች የማስተር ፕላን ማዘጋጀትና መተግበር | | | | | | | | | | |
| 4. ቁልፍ የውጤት መስክ፡- ስትራቴጂያዊ አጋርነትና ውጤታማ ኮሙኒኬሽን | | | | | | | | | | | |
| 4.1. ስትራቴጂያዊ ግብ፡- አገራዊና ዓለም አቀፋዊ አጋርነትና ድጋፍን ማሳደግ | | | | | | | | | | | |
| 4.1.1. የፍርድ ቤቶችን ዓለም አቀፍ ግንኙነትና ትብብር ለማጠናከር የሚያስችል ስርዓት ዘርግቶ መተግበር ፤ | • የዓለም አቀፍ ግንኙነትና ትብብር ለማጠናከር ጥናት በማድረግ ፖሊሲና ስትራቴጂ ማዘጋጀትና መተግበር<br>• አለም አቀፍ የዳኝነት ኮንፍረንሶች ላይ መሳተፍ | የፍርድ ቤቶች ዓለም አቀፍ ግንኙነትና ትብብር ተጠናክሯል፤ | የነጻነትና ገለልተኝነት መርህን በጠበቀ መልኩ ትብብርና ድጋፍ የሚያደርጉ ተቋማት ብዛት በቁጥር | 7 | 11 | 9 | 9 | 10 | 10 | 11 | የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ጽ/ቤት ፣ ፕሬዝደንቶች ፣ ኮርት ማነጀሮች ፣ ተከላካይ ጠበቆች ጽ/ቤት፣ የህጻናት ፍትህ ፕሮጀክት ጽ/ቤት፣ ኮምዩኒኬሽን ዳ/ት፣ |
| | | በዓለም አቀፍ የህግ/የዳኝነት ኮንፍረንሶች ላይ መሳተፍ ተችሏል፤ | ተሳትፎ የተደረገባቸው ኮንፍረንሶች ብዛት በቁጥር | - | 15 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | |

| ስትራቴጂዎች | ዋና ዋና ተግባራት | ውጤት (out-put) | አመልካች | መነሻ/ baseline | ግብ/ Target | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | ፈጻሚ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 4.1.2. ፍርድ ቤቶች ከተመረጡ የትምህርት፣ ሥልጠና እና ምርምር ተቋማት ጋር የሚኖራቸውን ትስስርና ትብብር ለማሳደግ የሚያግዝ ስርዓት ዘርግቶ መተግበር፤ | • ከተመረጡ የህግ፣ ሥልጠናና ምርምር ተቋማት ጋር የሥልጠና፣ የምርምርና የስርጸት የጋራ ፕሮጀክቶች በማዘጋጀት መተግበር | ፍርድ ቤቶች ከተመረጡ የትምህርት፣ ሥልጠና እና ምርምር ተቋማት ጋር ያላቸው ትስስር ተጠናክሯል፤ | ተግባራዊ የተደረገ የትብብርና ትስስር ስርዓት፤ | 3 | 5 | 3 | 3 | 4 | 4 | 5 | የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ጽ/ቤት፣ ፕሬዝደንቶች ፣ ኮርት ማናጀሮች ፣ የህጻናት ፍትህ ፕሮጀክት ጽ/ቤት፣ ኮምዩኒኬሽን ዳ/ት፣ |
| | | የጋራ ፕሮጀክቶች ጥናቶች ተካሂደዋል፤ | ተግባራዊ የተደረጉ የፕሮጀክት ጥናቶች ብዛት በቁጥር፤ | 1 | 5 | 1 | 1 | 1 | 1 | | |
| 4.1.3. ከፌደራል እና ከክልል የፍትህ አካላት ጋር በመርህ ላይ የተመሠረተ አጋርነትና ግንኙነት የሚያጠናክር ስርዓት ዘርግቶ መተግበር፤ | • በጋራ መድረክ አደረጃጀት ላይ ጥናት በማድረግ የአደረጃጀትና የአሰራር መመሪያ ማውጣት<br>• የጋራ መድረኮችን ማዘጋጀት | ከፌደራል እና ከክልል የፍትህ አካላት ጋር በመርህ ላይ የተመሠረተ አጋርነትና ግንኙነት የሚያጠናክር ስርዓት ተዘርግቷል፤ | ስርዓቱን ለመተግበር የተዘጋጀ መመሪያ | | 1 | 1 | | | | | የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ፣ ፕሬዝደንቶች፣ ኮርት ማናጀሮች ፣ኮምዩኒኬሽን ዳ/ት፣ የተከላካይ ጠበቆች ጽ/ቤት |
| | | | የተዘጋጁ የጋራ መድረኮች ብዛት በቁጥር | | 20 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | |

| ስትራቴጂዎች | ዋና ዋና ተግባራት | ውጤት (out-put) | አመልካች | መነሻ/ baseline | ግብ Target | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | ፈጻሚ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 4.1.4. የፌደራልና የክልል ፍ/ቤቶች ግንኙነት እና የአቅም ግንባታ ሥርዓትን ማጠናከር፤ | • የፌደራልና የክልል ፍ/ቤቶች የጋራ መድረክ አደረጃጀት ላይ ጥናት በማድረግ የአደረጃጀትና የአሰራር መመሪያና ዕቅድ ማውጣት<br>• የፌደራልና የክልል ፍ/ቤቶች የጋራ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት መዘርጋት<br>• ለክልል ፍ/ቤቶች የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች ማዘጋጀት<br>• ለክልል ፍ/ቤቶች የበጀት ድጎማ ቀመር ማዘጋጀትና ድጎማ ማድረግ | የግንኙነት እና የአቅም ግንባታ ስራዎች ተጠናክረዋል፤ | የተዘጋጁ የስልጠና መድረኮች ብዛት በቁጥር | 1 | 10 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ፣ ፕሬዝደንቶች ፣ ኮርት ማናጀሮች ፣ ኮምዩኒኬሽን ዳ/ት፣ |
| | | | የተካሄዱ የጋራ መድረኮች ብዛት በቁጥር | 1 | 5 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | |
| 4.1.5. ከህግ ባለሙያ/ ጠበቆች ማህበሮች ጋር የሚኖር አጋርነትን | • የዳኝነት ቅልጥፍና፤ ጥራትና ተደራሽነት ላይ የጠበቆችን ሚና ለማጎልበት ከማህበሩ ጋር የጋራ | ከህግ ባለሙያ/ ጠበቆች ማህበሮች ጋር የሚኖር አጋርነትን | ተዘጋጅተው የተተገበሩ የጋራ መድረኮች ብዛት በቁጥር፤ | | 5 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | ፕሬዝደንቶች፣ ኮርት ማናጀሮች፣ ኮምዩኒኬሽን ዳ/ት፣ |

| ስትራቴጂዎች | ዋና ዋና ተግባራት | ውጤት (out-put) | አመልካች | መነሻ/ baseline | ዒላማ Target | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | ፈጻሚ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ለማሳደግ የትብብርና የግንኙነት ሥርዓቶችን መዘርጋትና ማጠናከር | ፕሮጀክት አዘጋጅቶ መተግበር | ለማሳደግ የሚያስችሉ የትብብርና የግንኙነት ሥርዓቶች ተጠናክረዋል፤ | | - | | | | | | | |
| 4.2. ስትቴጂያዊ ግብ፡- የህዝብ ግንዛቤ እና ተሳትፎን ማሳደግ4.2. | | | | | | | | | | | |
| 4.2.1. የኮሚዩኒኬሽን ክፍሎችን አደረጃጀትና አሰራር ማጠናከር፤ | • የኮሚኒኬሽን ስትራቴጂ ማዘጋጀት<br>• የሚዲያ አዘጋገብ መመሪያ ማዘጋጀት እና መተግበር<br>• ስለ ኮሙኒኬሽንና ገጽታ ግንባታ ለሚመለከታቸው ለዚሁ ስራ ለተመደቡ ባለሙያዎች እና ዳኞች ስልጠናዎችን መስጠት<br>• የፍርድ ቤቶችን ስራ አዘጋገብ | የኮሙኒኬሽን ክፍሎች አደረጃጀትና አሰራር ተጠናክሯል | የተጠናከሩ የኮምዩኒኬሽን ስራ ክፍሎች በቁጥር፤ | 1 | 3 | | 2 | 3 | | | ፕሬዝደንቶች፣ ከርት ማናጀሮች ፣ ኮምዩኒኬሽን ዳ/ት፣ |
| | | | የተተገበሩ የኮምዩኒኬሽን ስትራቴጂና መመሪያዎች | - | 2 | 1 | 1 | | | | |
| | | | የተዘጋጁ የስልጠና መድረኮች ብዛት በቁጥር | 1 | 8 | 2 | 3 | | 2 | | |

| ስትራቴጂዎች | ዋና ዋና ተግባራት | ውጤት (out-put) | አመልካች | መነሻ/ baseline | ግብ/ Target | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | ፈጻሚ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
